# የዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት በአዝማሪ አንደበት

መስፍን መሰለ

## አኅጽሮተ ጥናት

*በኢትዮጵያ የአዝማሪና የቤተ መንግሥት ቅርርብ መቼ እንደ ተጀመረና ምን ሚና እንደ ነበረው አይታወቅም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከጎንደር ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ጀምሮ የአዝማሪንና የቤተ መንግሥትን ቅርርብ በጥቂት የታሪክ ሰነዶች ተገልጾ እናገኛለን፡፡ አዝማሪ ጣፋጭ ከደጅ አዝማች ጎሹ፤ አዝማሪ አብተው ከዐፄ ቴዎድሮስ፤ ሐሰን አማኑ መጀመሪያ ከዐፄ ዮሐንስ በኋላ ከራስ (በኋላ ንጉሥ) ሚካኤል፤ ሊቀ መኳስ  መርሻ ከራስ ኃይሉ፤ እሸቴ ጎቤ፣ ከራስ መኰንን፤ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ፣ ከልጅ ኢያሱ፤ ምስጋናው አዱኛ ከራስ ጉግሳ ወሌ፣ ወዘተረፈ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው፡፡ ከደጅ አዝማች ካሣ (በኋላ ዐፄ ቴዎድሮስ) ጋር የጠበቀ ቅርርብ የነበረው አዝማሪ፣ በመሰንቆ ግርፍና ዜማ፣ በግብር፣ በዘመቻ፣ በክብረ በዓል፣ በሰርግ፣ በክርስትናና በሌሎችም የተዝናኖት ጊዜያቶች፣ የጀግንነት ግጥሞችን እየደረደረ፣ ጌታውንና ታዳሚዎቹን ያዝናናል፡፡ ያማረ ቀርቦ ግብር በሚበላበት፣ ጥሩ በሚጠጣበት ጊዜም፣ አዝማሪው የዘለሰኛና የመዲና ግጥሞችን በማዜም በማዜም የታዳሚዎችን ስሜት ይቆጣጠራል፤ ያስደምማል፡፡ የሙገሳ ግጥሞችን በመደርደር የታዳሚዎችን ቀልብ ወደ ተፈጸሙ ድርጊቶች በሐሳብ ይወስዳል፡፡ በሕይወት ያሉትንና የሌሉትን የጌታውን የቅርብ ዘመዶች፣ ጓደኞች እንዲሁም የራሱን ወዳጆች ስምና መልካም ተግባራት እየዘረዘረ ያሞግሳል፤ ይዘክራል፡፡ የጌታውን ተቀናቃኞች በሌሉበት ያኰስሳል፤ ይሰድባል፤ ይወቅሳል፡፡ ታዳሚዎቹም የአዝማሪው ሙገሳ እውነትነቱን ለማረጋገጥ “እውነት እውነት ብለሃል” በማለት ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡ በስሜት ተገፋፍተውም በመፎከር ድባቡን ያደምቁታል፡፡ ግጭት ሲፈጠርም፣ የጌታውንና የነፍጠኞቹን ጀግንነት ከፍ ከፍ እያደረገ፤ የጌታውን ተቀናቃኝ ደግሞ ያኰስሳል፤ ይሰድባል፡፡ ግጭቱ ጠንክሮ ጦር ወደ መማዘዝ ካመራም ለፍልሚያ ያነሣሣል፡፡ ፍልሚያው ወደሚካኼድበት ቦታ ከጌታው ጋር በመዝመትም፣ ደፋሮችን ያሞግሳል፣ ወላዋዮችን ያበረታታል፤ ፈሪዎችን ይነቅፋል፤ ይሰድባል፡፡ የፍልሚያው የቅስቀሳ ክፍል ኾኖ ይሠራል፡፡ በፍልሚያው ማን የጀግንነት ተግባር እንደፈጸመና ማን ጊዜው የሚጠይቀውን ግዴታ እንዳልተወጣ ይመለከታል፡፡ ግዳይ እየጣሉ የሚፎክሩትን የጌታው አሽከሮች ተግባር በአእምሮው ይመዘግባል፡፡ ከፍልሚያው በኋላ በሚፈጠሩ ልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ለምሳሌ በግብር፣ የጀግንነት ተግባር የፈጸሙ ነፍጠኞችን ባሉበት ወይም በሌሉበት ሥራቸውን እየጠቀሰ ያሞግሳል፤ ፈሪዎችን ደግሞ ያኮስሳል፡፡ በቤተ መንግሥትና በአዝማሪ መካከከል የጠበቀ ግንኙነት መኖሩን የሚገልጹ የታሪክ ሰነዶች ቢኖሩም፣ የተመራማሪዎችን ትኩረት ግን አላገኙም፡፡ በጽሑፍ የተመዘገበውን ወይም በቃል የሚነገረውን መነሻ በማድረግ በአዝማሪዎችና በአገረ ገዢዎች ግንኙነት ላይ የተካኼደ ጥናት ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይኽ ጥናት በተመራማሪዎች ብዙም ትኩረት ያልተደረገበትን የደጅ አዝማች ካሣ (የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ) ጀግንነነት በአዝማሪ አንደበት እንዴት እንደ ተሞገሱ መርምሯል፡፡ መረጃዎችም ከተለያዩ ጽሑፎች የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ አብዛኞዎቹ ከገሪማ ታፈረ መጽሐፍ ተሰብስበዋል፡፡ ጥቂት የዐዝማሪ ቃለ ግጥሞች የቃል መረጃ ከሰጡ ሰዎች ለማግኘት ተችሏል፡፡*

## ፩. መግቢያ

አዝማሪዎች በዐማራ፣ በትግራይና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት በገጠርና በከተማ፣ አዲስ አበባን ጨምሮ ከሌላው ሕዝብ ጋር ተቀላቅለው ይኖራሉ፡፡ በገጠር የሚኖሩ አዝማሪዎች የመኖሪያ መንደራቸውን ከሌላው ለይተው በመመሥረት ያርሳሉ፣ ከብት፣ ፍየልና ሌሎች እንስሳትንም ያረባሉ፡፡ በበጋ ወቅትም በአካባቢያቸውና ከአካባቢያቸው ርቀው በመኼድ በሰርግ፣ በክርስትና፣ በታቦት ንግሥ፣ በክብረ በዓል፣ በተዝካር አጋጣሚዎችና በመሸታ ቤቶች በመገኘት ግጥም እየደረደሩ በማዜም ገንዘብ ይቀበላሉ፡፡ በገጠር የሚኖሩ አዝማሪዎች ሕይወታቸው የተመሠረተውም አዝምረው በሚያገኙት ገንዘብና በግብርና ነው፡፡ በከተሞች የሚኖሩ አዝማሪዎች ደግሞ፣ ኑሯቸው ሙሉ በሙሉ የተመሠረተው፣ በሰርግ፣ በክርስትናና በሌሎችም ድግሶች ላይ በመገኘትና ታዳሚዎችን በማዝናናት በሚያገኙት ሽልማት ነው፡፡ አንዳንዶቹ ሰርግ እንዲያጅቡ ይጋበዛሉ፡፡ ለአጀቡበትም ገንዘብ ይከፈላሉ፡፡ በትልልቅ ከተሞች መስፋፋት ምክንያት በተፈጠሩ ጭፈራ ቤቶች ማታ ማታ ገንዘብ እየተከፈላቸው የሚሠሩም አሉ፡፡ የተወሰኑት ደግሞ፣ የራሳቸውን የምሽት ጭፈራ ቤቶች በመክፈት መተዳደሪያቸውን ይመሠርታሉ፡፡

አዝማሪነት ሙያ ከቤተሰብ የሚማሩት ነው፡፡ የዚኽም ምክንያቱ በኅብረተ ሰቡ ዘንድ አዝማሪነት የሚዝናኑበት እንጂ የሚያከብሩትና የሚኮሩበት ሙያ አይደለም፡፡ የሙያው ዝቅ ተደርጎ መታየቱም የአዝማሪዎቹ ማኅበራዊ ደረጃ ዝቅ ተደርጎና ተንቆ እንዲታይ አድርጓል፡፡ የሙያው ባለቤቶች መናቃቸው ሙያውም እንዲናቅ አድርጎት ኖሯል፡፡ በዘር አዝማሪ ያልኾነ ሰው የተናቁት ወገን ተደርጎ ላለመቆጠር አዝማሪነትን ለመማር አይፈልግም፡፡

የራሳቸውን መንደር የመሥረቱትም ኾኑ ከሌላው ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩት አዝማሪዎች አብረው የሚኖሩትን ሕዝብ ደስታም ኾነ ኀዘን ይካፈላሉ፡፡ አብሯቸው የሚኖረው ሕዝብም በደስታቸውና በኀዘናቸው ይታደማል፡፡ የጋብቻ ባህላቸው፣ ቋንቋቸውና እምነታቸው አብረው ከሚኖሩት ሕዝብ ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ግን አዝማሪዎች የራሳቸው የምስጢር ቋንቋ አላቸው (Leslau, 1952; Abraham, 2015)፡፡ አብዛኛዎቹ አዝማሪዎች የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና፣ ጥቂቶቹ ደግሞ፣ የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ አዝማሪዎች ጋብቻ የሚፈጽሙት እርስ በእርሳቸው ነው፡፡ በተጋቢዎቹ አዝማሪዎች መካከል ያለው ዝምድና ርቀት ሲቆጠር እንደሚኖሩበት ኅብረተሰብ ኹሉ ሰባት ቤት (ትውልድ) መድረስ አለበት፡፡

የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ የደጅ አዝማች (በኋላ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ) ጀግንነታቸው በአዝማሪዎች እንዴት እንደ ተሞገሱ መመርመር ነው፡፡ አዝማሪዎች ደጅ አዝማች ካሣ ዐምጸው ሸፍተው ሊወጋቸው የዘመተባቸውን ጦር ድል በማድረጋቸው፣ ከነገሡ በኋላም ተቀናቃኞቻቸውን ድል በማድረጋቸውና በቅርብና በሩቅ ያሉ ቦታዎችን ነፃ ለማውጣት የነበራቸውን ምኞት መሠረት ያደረጉ የሙገሳ ግጥሞች ተመርምረዋል፤ ተተርጉመዋል፡፡ ጥናቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃልና በጽሑፍ በተላለፉ ጥቂት ቃለ ግጥሞች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

በጽሑፍ የተገኙት በአዝማሪ የተዜሙ የተባሉት ቃለ ግጥሞች ዐፄ ቴዎድሮስ በሥልጣን ዘመናቸው የፈጸሟቸውንና ለመፈጸም የተመኟቸውን ኹሉንም ድርጊቶች ስለ መግለጻቸው ለማወቅ አስቸጋሪ ይኾናል፡፡ በዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንነት ከሚገልጹት ቃለ ግጥሞች መካከል በጽሑፍና በቃል የተላለፉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ያልተመዘገቡትና የተረሱት ብዙ ሊኾኑ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

አዝማሪዎች ለዐፄ ቴዎድሮስ የደረደሯቸውን የሙገሳ ግጥሞች ማጥናት የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ይኸውም፣ የአዝማሪዎችን ቃለ ግጥም አደራረስ፣ የሚደርሷቸውን ቃለ ግጥሞች ተለዋዋጭነት፣ የዐፄ ቴዎድሮስ ባሕርይና የፈጸሟቸውን ድርጊቶች፣ በዘመኑ የነበረውን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ኹኔታዎች፣ በጦርነት ጊዜ በአጥቂውና በተጠቂው ላይ የሚፈጠሩ ስሜቶችን እናውቅባቸዋለን፡፡ ቃለ ግጥሞቹ በታሪክ መረጃነት ማገልገላቸውን እንረዳለን፡፡ በመረጃ ምንጭነት ባገለገሉት መጻሕፍት ቃለ ግጥሞች ለታሪኩ ውበት፣ ተነባቢነት፣ ጭብጥ መጉላት፣ አይረሴነት ያደረጉትን አስተዋጽኦ እንገነዘብባቸዋለን፡፡ ሌሎች ተመራማሪዎች ለሚያካኺዱት ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ጥናት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

ለዚኽ ጥናት አስፈላጊ የኾኑት መረጃዎች የተሰበሰቡት ከተለያዩ መጻሕፍት ነው፡፡ መጻሕፍቱ የተመረጡት በንባብ መረጃ እንዳላቸው በመረጋገጡ ኾን ተብሎ ነው፡፡ መጻሕፍቱም፣ አማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው (ማኅተመ ሥላሴ፣፲፱፻፷፭፣ ዝክረ ነገር (ማኅተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፷፩)፣ አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ (ገሪማ፣ ፲፱፻፺፯)፣ የኢትዮጵያ ታሪክ (ተክለ ኢየሱስ፣ 2008)፣ ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት (ተክለጻዲቅ፣ 1981) እና በተለያዩ ጊዜያት የታተሙ የዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕሎች ናቸው፡፡[1] ይሁን እንጂ፣ ለዚኽ ጥናት በመረጃነት ያገለገሉት የሙገሳ ግጥሞች አብዛኛዎቹ የተገኙት በገሪማ (፲፱፻፺፯) ከተዘጋጀው አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ ከሚለው መጻሐፍ ነው፡፡

የዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንነት የሚገልጹ በርካታ ቃለ ግጥሞች በተለያዩ የታሪክና የግጥም መጻሕፍት ተመዝግበዋል፡፡ ኾኖም፣ የዚኽ ጥናት ትኩረት በአዝማሪ በተዜሙት ላይ በመኾኑ፣ በአዝማሪ ተገጠሙ በተባሉት ላይ ብቻ ትኩረት አድርጓል፡፡ ከዚኽም በላይ፣ በአዝማሪ የተዜሙ ናቸው የሚባሉትም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን በሚያሞግሱት ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጓል፡፡ ቃለ ግጥሞች ከመጻሕፍት የተወሰዱት ጥናቱ ትኩረት ላደረገበት ርእሰ ጉዳይ በመረጃነት ባላቸው ጠቀሜታ ነው፡፡ የንጉሡን ታሪክ የጻፉ ሰዎች ከተለያዩ ምንጮች (ከመጻሕፍትም በቃል መረጃ ከሰጡ ሰዎችም) ያገኟቸውን በአዝማሪ የተገጠሙ ቃለ ግጥሞች በታሪክ ድርሰቶቻቸው መዝግበዋል፡፡

---

[1]በዚኽ ዝርዝር ወስጥ ያልተካተቱ በአዝማሪ የተደረደሩ ጥቂት ቃለ ግጥሞች የተገኙባቸውን *ሥራዎችን* በምንጭነት ተጠቅሜአለኹ፡፡ ከዚኽ ሌላ፣ አንዳንዶቹ ጸሐፊዎች ከእነሱ ቀድመው ከታተሙ ሌሎች *ሥራዎች* ያገኟቸውን ቃለ ግጥሞች፣ በአዝማሪ የተደረደሩትንም ጭምር፣ በመቅዳት እንዳቀረቡ ከመረጃ ምንጮቻቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ በተክለ ጻድቅ (1981) *ሥራ* ውስጥ የተጠቀሱት ቃለ ግጥሞች አብዛኛዎቹ እሳቸው በመረጃ ምንጭነት ከተገለገሉባቸው *ሥራዎች* የተቀዱ ናቸው፡፡

ደጅ አዝማች ካሣን (ዐፄ ቴዎድሮስን) የሚያኮስሱ፣ ባሕርያቸውን የሚገልጹ፣ ከሞቱ በኋላም በኀዘን እንጉርጉሮነት በአዝማሪ የተዜሙ ቃለ ግጥሞች በዚኽ ጥናት ትኩረት አልተደረገባቸውም፡፡ የጥናቱ ትኩረት በሙገሳ ግጥሞች ላይ ብቻ የተገደበ ነው፡፡

በተጠቀሱት መጻሕፍት የተመዘገቡት ቃል ግጥሞች በመረጃነት የተወሰዱት በአዝማሪ መቅረባቸውን ጽሑፎቹን የደረሱት ሰዎች ምስክርነት በመስጠታቸው ነው፡፡ ከደራሲዎቹ ምስክርነት በተጨማሪ አዝማሪዎች በኅብረተ ሰቡ ውስጥ በማንኛውም አጋጣሚ ሲከወኑ የሰሟቸውን ቃለ ግጥሞች እነሱ ለሚፈልጉት አገልግሎት ለመጠቀም ባህሉ የሚፈቅድላቸው መኾኑን በመገንዘብ ነው፡፡ የአዝማሪዎች ቃለ ግጥም ድረሳና ድርደራ ባህል የሰሙትን ቃለ ግጥም ለሚፈልጉት አገልግሎት የመጠቀም መብት ይሰጣል፡፡ በተመረጡት መጻሕፍትም የዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንነት የሚያሞግሱ ቃለ ግጥሞች በአዝማሪ እንደሚደረደሩ ቢታመንም የመጻሕፍቱ ደራሲዎች ምስክርነት ካልሰጡ በመረጃነት አልተወሰዱም፡፡

በታሪክ መጻሕፍትና ቃለ ግጥሞችን ሰብስበው ባሳተሙ ሰዎች የተመዘገቡት የሙገሳ ግጥሞች በአዝማሪዎች መደርደራቸውን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡ ፡ ለዚኽ የተአማኒነት ጥያቄ አዝማሪዎች የሚደረድሯቸውን ቃለ ግጥሞች እንዴት እንደሚደርሱና ከየት እንደሚያገኙ መረዳት መልስ ይሰጣል፡፡ አዝማሪዎች አንድም፣ አንድን አጋጣሚ መነሻ በማድረግ ዐዳዲስ ቃለ ግጥሞችን በመድረስ ይደረድራሉ፡፡ አንድም፣ በኅብረተ ሰቡ ውስጥ በማንኛውም ሰው፣ በማንኛውም አጋጣሚ ላይ (በግብር፣ በሰርግ፣ በክርስትና፣ በለቅሶ፣ በሥራ ወዘተረፈ) ሲደረደሩ የሰሟቸውን ቃለ ግጥሞች ሳይለውጡ ያዜማሉ፡፡ አንድም፣ ቀድመው የሚያውቋቸውን ወይም የሰሟቸውን ቃለ ግጥሞች ለውጠው (አሻሽለው) እና ለአጋጣሚው እንዲስማሙ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ ይኽን ማድረግ አዝማሪዎች በሚኖሩበት የዐማራ ኅብረተ ሰብ ባህል ይፈቅዳል፡፡ እናም፣ በኅብረተ ሰቡ ከሚደረደሩ ልዩ ልዩ ቃለ ግጥሞች አብዛኛዎቹ በአዝማሪዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ ይዜማሉ፡፡ ስለዚኽ መረጃ በሰበሰብኩባቸው መጻሕፍት በአዝማሪዎች የተደረደሩ ቃለ ግጥሞች እንደኾኑ ደራሲዎቹ የሰጡት ምስክርነት እውነት መኾኑን አምኖ ለመቀበል አዝማሪዎች ግጥም የሚደርሱበትና የሚያቀርቡበት ባህል ይፈቅዳል፡፡

አንዳንዶቹ ደራሲዎች የመዘገቧቸው ግጥሞች ማንነቱ ባልታወቀ አዝማሪ መደርደራቸውን ወይም በመሰንቆ ታጅበው መቅረባቸውን ገልጻሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ግጥሙን የደረደረውን አዝማሪ ስምና የማን አዝማሪ እንደ ነበር ገልጸው ጽፈዋል፡፡ ኹሉም ጸሐፊዎች የአዝማሪ ግጥም በምን አጋጣሚ፣ ለምንና እንዴት እንደተነገረ ያስረዳሉ፡፡

አዝማሪዎች ደጅ አዝማች ካሣን (በኋላ ዐፄ ቴዎድሮስ) ያሞገሱባቸውን ቃለ ግጥሞች የታሪክ ጸሐፊዎች በተከወኑባቸው አጋጣሚዎች ላይ ተገኝተው አልመዘገቡም፡፡ አብዛኛዎቹ ቃለ ግጥሞችም በዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋእሎች አይገኙም፡፡ ጸሐፊዎቹ "በአዝማሪ የተዜሙ" ያሏቸውን ቃለ ግጥሞች የመዘገቡት የተከወኑበት አጋጣሚ ወይም ድርጊት ከተፈጸመ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው፡፡ ለዚኽም ማስረጃው፣ ታሪክ ጽሐፊዎቹ ነገሥታቱ ከሞቱ በርካታ ዓመታት በኋላ ቃለ ግጥሞቹን መመዝገባቸው ነው፡፡ ጸሐፊዎቹ የሙገሳ ግጥሞቹን፡- አንድም፣ ዐፄ ቴዎድሮስ

በሕይወት በነበሩበት ዘመን የተደረደሩትን የሰሙ ሰዎች ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ሲያስተላልፉ ያገኟቸው ናቸው፡፡ አንድም፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ዓላማቸውንና ጅግንነታቸውን የሚያውቁ አዝማሪዎች ወይም ሌሎች ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት ሲደረደሩ የሰሟቸው ናቸው፡፡ ቃለ ግጥሞቹም በመጀመሪያ ከቀረቡበት ተለውጠው ወይም ተሻሽለው እንደ ተላለፉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተለዋዋጭነት የቃለ ግጥም ድረሳ ባሕርይ መኾኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት አዝማሪዎች የደረደሯቸው የሙገሳ ግጥሞች አብዛኛዎቹ በሰምና ወርቅ የተነገሩ ናቸው፡፡ ሰሙ በግጥሙ የተላለፈውን መልእክት መሸፈኛና ቀድሞ ለአእምሯችን ግልጽ የሚኾነው ፍቺ ነው፡፡ የአዝማሪው ዋና መልእክት የተላለፈው (የተገለጸው) ግን በወርቁ ነው፡፡ የትንተናው ትኩረት በወርቁ በተላለፈው መልእክት ላይ በመኾኑ ለወርቁ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ በወርቁ የተላለፈውን መልእክት ለመረዳት ግጥሙን ደጋግሞ ማንበብና መመርመር ጠይቋል፡፡ የወርቅ አፈታት ስልትን በመከተል ፍቺውን ለማግኘት ጥረት ተደርጓል፡፡ በይዘት ትንተናው የየቃለ ግጥሞቹን ሰምና ወርቅ ስልትን ተከትያለኹ፡፡ ኹለቱም (ሰምና ወርቅ) እንዴት እንደተገለጹ ማስረዳት የግጥሙ ባህል በመጠየቁ የተፈጸመ ነው፡፡

## ፪. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የተለያዩ ሰዎች በአዝማሪዎች ላይ የተለያዩ ጥናቶችን አካኺደዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ አዝማሪዎች ቃለ ግጥሞች ላይ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ያቀረቡት፣ አልማዝ (1974)፣ ኑርሁሴን (1986)፣ መንገሻ (1992) እና አንለይ (1995) ናቸው፡፡ አዳነች (2001)፣ አበበ (2002)፣ ሐረገ ወይን (2004)፣ ቤተልሔም (2005)፣ Kefyalew (1998)፣ Mesganaw (2010) እና Tigist (2010) ለኹለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶቻቸውን አቅርበዋል፡፡ ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ በአዝማሪ ላይ ጥናታቸውን ያደረጉት ደግሞ Kimberlin (1976), Kawase (2005) እና አስቴር (2007) ናቸው፡፡ እንዲሁም አዝማሪዎች በሚደረድሯቸው ግጥሞች፣ በሙዚቃቸው፣ በአከዋወን ስልታቸውና በሙያቸው በሚታየው ተከታታይነትና ለውጥ ላይ ትኩረት ያደረጉ የታተሙና ያልታተሙ ጥናቶችን ያቀረቡ ኢትዮጵያውያንና የውጭ ሀገር ሰዎች በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ Leslau (1952, 2001)፣ Pankurst (1959)፣ Ashenafi (1971, 1976)፣ Pankhurst and Asfaw (1985)፣ Timkehet (2009)፣ Girma (2014) ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚኽም በላይ፣ በታሪክ፣ በሙዚቃ፣ በፎክሎርና በሥነ ጽሑፍ ሥራዎች፣ እንዲሁም በጉዞ ማስታዎሻዎች የአዝማሪዎች ቃለ ግጥሞችና ተግባራቸው ተጠቅሰዋል፡፡ በዐፄ ቴዎድሮስ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የታሪክ ምርምሮች ከጥናቱ ወሰን ውጭ በመኾናቸው እነሱን መመልከት አስፈላጊ ኾኖ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም፣ በአዝማሪ ላይ ትኩረት ያደረጉ አብዛኛዎቹ ጥናቶች ለዚኽ ጥናትሌላቸው ጠቀሜታ አነስተኛ በመኾኑ አልተቃኙም፡፡ ከዚኽ ጥናት ጋር በቀጥታና በተዘመዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸው ጥቂት ጥናቶች ብቻ ተቃኝተዋል፡፡ የተለያዩ ሰዎች በጥናቶቻቸውና በጉዞ ማስታዎሻዎቻቸው ስለ አዝማሪ ወይም ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ የዘገቧቸውን

እንደ አስፈላጊነቱ በትንተናው ውስጥ ለመጠቀም ጥረት ተደርጓል፡፡ ቀጥለን ጥቂት ሥራዎች ላይ የተደረገውን ቅኝት እንመለከታለን፡፡

ከዚኽ ሥራ ጋር በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያለው የአዳነች (2001) ጥናት በሰባት የታሪክ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ የፍክሎር ዓይነቶች ለምን ተግባር እንደገቡ ያሳያል፡፡ ከመጻሕፍቱ የሰበሰበቿው የፎክሎር ዓይነቶች ሥነ ቃል፣ ከሥነ ቃልም ቃለ ግጥሞች እንደሚበዙ ገልጸዋል፡፡ የሥነ ቃል ዓይነቶችንም በጥናታቸው መጨረሻ በአባሪነት አያይዘው አቅርበዋል፡፡ ከመጻሕፍቱ በሰበሰቧቸው የፎክሎር ቅረጾች ላይ ትንተና አድርገዋል፡፡ ከተሰበሰቡት ቃለ ግጥሞች መካከል ጥቂቶቹ በአዝማሪ የተዜሙ ናቸው፡፡ ትንተናቸው በተወሰኑት ግጥሞች ላይ ብቻ ከመኾኑም በላይ የዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት በአዝማሪ አንደበት እንዴት እንደ ተገለጸ አያሳይም፡፡ የፎክሎር ዓይነቶችን ከሰበሰቡባቸው ሰባት መጻሕፍት፣ ኹለቱ የዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ መሠረት አድርገው የተጻፉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ የዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉ የተለያዩ ሰዎች ባሳተሟቸው መጻሕፍት በርካታ የፍክሎር ዓይነቶች የሚገኙ በመኾኑ የአዳነች ጥናት ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ ከተገጠሙት ውስጥ በጣም ጥቂቱን የተመለከተ ነው፡፡ በዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ በሚያተኩሩ የተለያዩ መጻሕፍት በርካታ ቃል ግጥሞች ቢኖሩም የእሳቸው ጥናት ትኩረት አልኾኑም፡፡ የአዳነች መረጃዎች በተለያዩ ጊዜያት በነገሡ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚያተኩሩ በመኾኑ እያንዳንዳቸው ታሪካዊ ዐውዳቸውን መሠረት በማድረግ በጥልቀት ሊመረመሩ የሚገባቸው ናቸው፡፡ የአዳነች ጥናት፣ በዐፄ ቴዎድሮስ፣ በዐፄ ዮሐንስ፣ በዐፄ ምኒልክ፣ በልጅ ኢያሱና በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እንዲሁም በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ታሪክ ላይ የሚያተኩሩ የፎክሎር ዓይነቶችን በመሰብሰብ ትንተና ለመስጠት መሞከራቸው የጥናታቸው ትኩረት የላላ እዲኾን አድርጎታል፡፡ ይኽም ኾኖ፣ የውጭ ምንጮችን በመጥቀስ በተበታተነ መልክ ፎክሎር ለታሪክ ጥናት ያለውን ጠቀሜታ የገለጹት ለዚኽ ጥናት በግብዓትነት አገልግሏል፡፡

Ashenafi (1975) ባቀረቡት አዝማሪነት የመደብ ክፍፍል ባለበት ከፍተኛ የመሳፍንትና የመኳንንት አመራር ተግባራዊ በሚደረግበት የባላባት ሥርዓት በሰፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚያብብ ሙያ መኾኑን ገልጸዋል፡፡ በኢትዮጵያ ዓለማዊው የአዝማሪ ሙያ ምን ያኽል ጊዜ እንደኾነው የሚገልጽ ማስረጃ አለመኖሩን ጠቁመው፣ ኢትዮጵያ ክርስትናን ከመቀበሏ ከምዕተ ዓመታት በፊት ሙያው ነበር ማለቱ ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ Ashenafi እንደሚሉት፣ ዓለማዊ የኾነው የአዝማሪ ሙዚቃ ከመንፈሳዊ መንጭቶና ተሻሽሎ የቀረበ ነው፡፡ አዝማሪው በአደባባይ የማይነገሩትን ለስሜት ቅርበት ያላቸውን ርእሰ ጉዳዮች ለምሳሌ፣ የመሳፍንቱን ያለ አግባብ ሥልጣንን መጠቀም፣ የሰፈር ላይ ቅሌቶችን፣ የቀሳውስቱን መንፈሳዊ አገልግሎት ማጓደልን ትኩረት አድርጎ ይተቻል፡፡

Ashenafi (1975) እንደሚሉት ኹልጊዜም ከወንድ አዝማሪዎች ጋር የማይለዩት ገጣሚና ሙዚቀኞቹ ሴት አዝማሪዎች የወንዶቹ ፍቅረኞች ወይም ሚስቶች ናቸው፡፡ ሙያውን የሚማሩት በሥራው ላይ ኾነው ወይም የተለየ ችሎታ ያላቸው በኺደት ከወንዶቹ ጋር አብረው በመሥራት ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ ወንዶችም ሴቶችም መደበኛ ሥልጠና ሳይኖራቸው ተፈጥሮ

ያደላቸውን የሙዚቃ ችሎታና መልካም ድምፅ ተጠቅመው በሰፈራቸው ከዚያም አልፎ በሰፊ አካባቢዎች ዕውቅናን ያገኛሉ፡፡ ሴቷም ወንዱም በአዝማሪነት የሚሰማሩት ሙያውን ስለ ሚወዱት ወይም በመዝፈን በሚያገኙት ገንዘብ ተጠቃሚ በመኾናቸው ወይም አድማጭ ስለሚያደንቃቸው አይደለም፡፡ አዝማሪ የኾኑት በኑሮ ስለ አልተሳካላቸውና ከዚኽ የተሻለ ሥራ መሥራት ባለመቻላቸው እንጂ፡፡ ሙያውን ባይወዱትም ቤተሰብ ያስተዳድሩበታል፡፡ ሕዝቡ ለአዝማሪነት ሙያ ያለው አመለካከት አሉታዊ  በመኾኑ ሙያው ዝቅተኛ ማኅበራዊ ቦታ በተሰጠው ሰው በተለምዶ የሚከናወን ነው፡፡ በአሉታዊ አመለካከት ምክንያት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወላጅ ልጁ አዝማሪ እንድትኾን/እንዲኾን አይፈልግም፡፡ ከአዝማሪ ጋርም ጋብቻ አይፈጽምም፡፡

አዝማሪዎች ከአንድ ቤት ወደ ሌላ ቤት፣ ከአንድ ሰፈር ወደ ሌላ ሰፈር፣ ከአንድ ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ፣ ከአንድ አውራጃ ወደ ሌላ አውራጃ በመዘዋወር በድግስ ላይ (በሰርግ፣ በክርስትና)፣ በጠጅ ቤት ይዘፍናሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ በመሳፍንት የመቀጠር ዕድል በማግኘት በበቅሎ ወይም በፈረስ በሚደረግ አድካሚ ጉዞ ከኋላ ከሌሎች አሽከሮች ጋር በእግራቸው ይኳትናሉ፡፡ በምግብ ሰዓት፣ ከምግብ በኋላ ወይም በሚታደርበት ቦታ የቀጠራቸውን ጌታቸውን ያዝናናሉ፡፡ በማዝናናቱ ኺደት  አድናቆትን ያገኙ (ያተረፉ) አዝማሪዎች ከጌታቸው ትራፊ ጉርሻ ይላከላቸዋል፡፡

ብዙዎቹ አዝማሪዎች የተለየ የምልከታና የቋንቋ ችሎታ አላቸው፡፡ ግጥሞቻቸው ድርጊቶችን ወይም ኹኔታዎችን፣ የሰዎችን ባሕርይና ችግሮችን ሰርስሮ የመግለጽ አቅም አላቸው፡፡ አዝማሪዎች ከማዝናናት በተጨማሪ ሌሎች ሙያዎች አሏቸው፡፡ በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ዜና ዘጋቢዎች ናቸው፤ ማኅበራዊ ትችት አቅቢዎች ናቸው፤ ተራቢዎች (አስቂኝ ተዋናይ) ናቸው፤ የጉዞ ጓደኛ ናቸው፤ የፖለቲካ ቀስቃሽ ናቸው፤ የተሐድሶ እምነት አራማጆች ናቸው፤  ዱርዬ ናቸው፤ ገጣሚ ናቸው፤ አሽከር ናቸው፤ አሞጋሽ ናቸው፤ ግለሰብን ተችዎች ናቸው፡፡ መሳፍንቱንም ይተቻሉ፡፡ በብሔራዊ በዓላት ላይ በመገኘት በግጥሞቻቸው በዓሉን ያስተዋውቃሉ፡፡

Ashenafi እንደሚሉት አዝማሪዎች ቀደም ሲል ኑሮውን በግብርና ላይ መሥርቶ ሕይወቱን ይመራ ለነበረው ኅብረተ ሰብና ባላባታዊው ሥርዓት የሙዚቃ ፍላጎቱን አሟልተው ኖረዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ አሁን ያለው ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ እውነታ የሚፈልገው የሙዚቃ ስልት ይዘቱ፣ ሚናው እና ተግባሩ በአዝማሪ ከሚቀርበው ባህላዊ ሙዚቃ የተለየ ነው፡፡ Ashenafi ጥናታቸውን የቋጩት እንደ ኢትዮጵያ ያለ ረጅም ታሪክ ያለው ሀገር ባህላዊ ቅርሳቸውን ትተው በባህል ከአደጉት መዋስ ለምን አስፈለገ? ለሚለው የአንባቢ ጥያቄ መልስ እንዲሰጥ በመጋበዝ ነው፡፡

Kimberlin (1976) በአዝማሪ የሙዚቃ ቅኝት ላይ ትኩረት አድርገው በሠሩት ጥናት የአዝማሪን ምንነት፣ ማኅበራዊ ደረጃ፣ የምሥጢር ቋንቋ፣ የግጥም ትኩረት፣ የሙያ ለመዳ፣ የሚኖሩባቸውን ኅብረተ ሰቦችና ጠቅላይ ግዛቶች፣ የግጥም አውዶችንና የኢኮኖሚ ምንጫቸውን አስረድተዋል፡፡ እሳቸው እንደሚሉት ከሙቶ ዓመታት በፊት አዝማሪ የሚታወቀው በአሞጋሽነት

ነው፡፡ በዚኽ ባሕርይ እንዲታወቅ ያደረገው በጦርነት ቅስቀሳና መልካም ተግባሮችን ለሌሎች በግጥም የማስረዳት ችሎታው በመሳፍቱ ይቀጠር ስለ ነበር ነው፡፡ በኺደትም አዝማሪ ለጌታው የሙገሳ ግጥም ደርዳሪ ብቻ ሳይኾን ጌታውንም ኾነ ጓደኞቹንና ጠላቶቹን የሚተች ኾነ፡፡ እየቆየም አዝማሪ ማለት ተቺና ስም አጥፊ ተደርጎ ተቆጠረ፡፡ አዝማሪ ዘፋኝ፣ ተዋናይ፣ ዓለም አጫዋች፣ ተሳዳቢ የሚሉ ተጨማሪ ባሕርያት ተሰጠው ሲሉ ይገልጸጻሉ፡፡ የKimberlin (1976) ዋና ትኩረት በቅኝት ላይ በመኾኑ ለሙገሳ ግጥሞች ትኩረት አልሰጠም፡፡

Tigist (2010) ባቀረቡት የኹለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት በጎንደር ከተማ የሚኖሩ አዝማሪዎችን ግጥሞች ይዘትና የከዋኔ ስልቶች ይመረምራል፡፡ በጎንደር የሚኖሩ አዝማሪዎች በአካባቢው ከሚኖረው አዝማሪ ካልኾነው ሕዝብ የሚለዩባቸው ገጽታዎች አሏቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ አብረው ከሚኖሩት ሕዝብ ጋር ተመሳሳይ ታሪክ፣ ባህል፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እውነታዎችን ይጋራሉ፡፡ በግጥሞቻቸው የሚነገሩ ይዘቶች በአካባቢው የሚኖረውን ሕዝብ ይገልጻሉ፡፡ በግጥሞቻቸው ውበትን፣ ጀግናንና ጀግንነትን፣ ቦታዎችን፣ ማኅበረሰብንና መልካም ጓደኝነትን ያሞግሳሉ፡፡ በሌላ በኩል፣ ተገቢ ያልኾነን ባሕርይ፣ ትክክል አይደለም የሚሏቸውን የአድማጭ ድርጊቶችና ትውልድን ይተቻሉ ብለዋል፡፡

የTigist ጥናት በበቂ መረጃ ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ አዝማሪ በሚያዜማቸው ግጥሞች የሚነገሩትን ይዘቶች ለይቶ ለመረዳት አያስችልም፡፡ በአዝማሪ የሚደረደሩ የሙገሳ ግጥሞች ምን ምን ጉዳይ ላይ እንደሚያተኩር ጥናቱ አያወሳም፡፡ የአዝማሪ የግጥም ስልት አብሮ ከሚኖረው ኅብረተ ሰብ የተለየ እንዳለውና እንደሌለው ለይቶ አያስረዳም፡፡

አስቴር (2007) ትኩረት በወሎ አዝማሪዎች በተለይም የኑሮና የዘፈን ልምድ ያለውን ተከታታይነትና ለውጥ በመመርመር ላይ ነው፡፡ ጥናቱ በተጠቀሰው አካባቢ የአዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ልምድ ያለውን ተከታታይነት፣ የተከሰቱ ለውጦችን የለውጥ ምክንያቶችንና የአዝማሪዎችን ወቅታዊ አኗኗር መምረዋል፡፡ ለጥናታቸው መረጃዎችን ከቀዳማይና ከካልአይ የመረጃ ምንጮች ሰብስበዋል፡፡ በዘፈን ለመዳና ተስተላልፎ፣ በአከዋወን ሥርዓት በመከወኛ ቦታ፣ በገቢ ምንጭ፣ በዘፈን አከዋወን ደንብ፣ በዘፈን መከወኛ ዐውዶች ላይ ለውጥ መከሰቱን አስረድተዋል፡፡ የመንግሥት ርዕዮተ ዓለም ለውጥ፣ የአካባባው ኅብረተ ሰብ ለአዝማሪነት ያለው አመለካከትና የኤሌክትሮኒክስ የሙዚቃ መሣሪያዎች ወደ አካባቢው መግባት ለወሎ አዝማሪዎች ልምድ መቀየር ምክንያት መኾናቸው ተገልጹዋል፡፡ አብዛኞዎቹ የወሎ አዝማሪዎች ከዘፈን የሚያገኙት ገቢ ለኑሮ የማይበቃቸው በመኾኑ ቀስ በቀስ ራሳቸውን ከዘፈን ሥራ እያላቃቁ ሌላው የአካባቢው ነዋሪ በተሠማራባቸው ሌሎች ተግባራት ላይ ተሠማሩ ብለዋል (አስቴር፣ 2007፤ xii)፡፡

አዝማሪዎች ዘፈንን በተለያዩ አውዶች እየከወኑ የገቢ ምንጫቸው አድርገው ለዘመናት የኖሩ ናቸው፡፡ እንደዛሬው የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑት ቴፐሪከርደርና ቴሌቪዥን ወደ ሀገራችን ከመምጣታቸው አስቀድሞ፣ እንዲሁም ዘመናዊ የሙዚቃ ባንድ በሀገራችን ከመቋቋሙ በፊት ሰርግ፣ ክርስትናና የመሳሰሉት ማኅበራዊ የደስታ መሰባሰቦች ያለ አዝማሪ የዘፈን አጀብ

አይታሰብም፡፡ በዓሉን የማድመቅና ታዳሚውን በዘፈን የማስደሰት ሥራ ለአዝማሪ የተተወ ጉዳይ እንደ ነበር Ashenafiን (1975) እና Mesganawን (2010) በመጥቀስ አስረድተዋል።

ጥናቶቹ እንደሚያመለክቱት የአዝማሪዎች አገልግሎት በማኅበራዊ ሕይወት ላይ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፡፡ አዝማሪዎች ዘፈንን በመከን ሰውን ከማዝናናታቸው ባሻገር በኢትዮጵያ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሥፍራ ነበራቸው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ Kimberlin (1976) እንደሚገልጹት ዘፈን ከኢትዮጵያ ሕዝብ አኗኗር ይትባሃልና ሕይወት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው መኾኑ ነው፡፡ እንደ Ashenafi (1975) እና Teclehaimanot (1986) ትንታኔ አዝማሪዎች ዋና ሥራቸው ማዝናናት ቢኾንም በተጨማሪ ግን ዜናና ታሪክ ነጋሪዎች፣ ተችዎች፣ የፖለቲካ ተንታኞች፣ መዝጋቢዎችና አዝማቾች ኾነው አገልግለዋል፡፡ ይኹንና ማኅበረ ሰቡ የአዝማሪዎችን አገልግሎት ይፈልግ እንጂ እነሱን ንቆ እንደሚመለከታቸው "አዝማሪ" የሚለውን ስማቸውን ሳይቀር ለስድብነት (አስቴር፣ 2007፤ 2) ሲጠቀምበት እንደ ኖረ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይኽ በኹለት ቡድኖች መካከል ያለው የማኅበራዊ ደረጃ ልዩነት አዝማሪዎችን በተገለሉ መንደሮች እስከ መኖር እንዳደረሳቸው Kawase (2005)፣ አበበ (2002) እና Mesganaw (2010) በጥናቶቻቸው ገልጸዋል፡፡ (ገጽ 3)

የአዝማሪ ግጥም መከወኛ አውዶች ገበያ፣ የተለያዩ ድግሶች (ግብር፣ ሰርግ፣ ክርስትና፣ ክብረ በዓላት)፣ የታቦት ንግሥ፣ መጠጥ ቤቶች፣ ጦርነት፣ የታቦት ንግሥ ናቸው፡፡ የተዘረዘሩት አውዶች የየራሳቸው ባሕርይ ያላቸው መሆኑን የሚገልጹት አዝማሪዎች በእያንዳንዱ አውድ የሚከውኑት ዘፈን የተለያየ መልክ አለው (አስቴር፣ 2007፤ 188)፡፡

ግብር ቀደም ባለው የኢትዮጵያ መንግሥት አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ ንጉሡ ወይም አስተዳዳሪው ለቤተ መንግሥት ባለሟሎች የሚያደርገው ግብዣ ነው፡፡ ግብር የሚከወነው በአስተዳዳሪው ቅጥር ግቢ ወይም ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ አዳራሽ ወስጥ ነው፡፡

የግብር ዋና ታዳሚዎቹ ሹማምንት ናቸው፡፡ እነዚኽ ሹማምንት ወደ አዳራሹ ከገቡ በኋላ በሥልጣን ተዋረድ ይቀመጣሉ፡፡ የምግብ አቀማመጡ መስተንግዶው የራሱ ሥርዓት አለው፡፡ የአዝማሪ ዘፈን ክወና የሥርዓቱ አካል ነው፡፡ በግብር ሥርዓት ውስጥ ተራ ከሚባለው ማኅበረሰብ ውስጥ ያለምንም ከልካይ መግባት የሚችለው አዝማሪ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው "ከጥንት ጀምሮ መጋረጃ ገልጠህ፣ ዙፋን ረግጠህ ግባ" የሚባል ምርቃን ስላለን ነው ይላሉ፡፡ በዚኽ ምክንያት ቁጥራቸው ምንም ያኽል ቢኾን ወደ ግብር ቦታ በመኼድ ዘፈንን ከውነው ግብሩን በልተው፣ ሽልማት ተቀብለው ይወጣሉ (አስቴር፣ 2007፤ 189)፡፡

የአስቴር ጥናት ትኩረት በወሎ በተወሰኑ ቀበሌዎች በሚኖሩ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ያለውን ተከታታይነትና ለውጥ ላይ በመኾኑ የሙገሳ ግጥሞቻቸውን አልመረመረም፡፡ ይኽም ኾኖ አዝማሪዎች ግጥሞቻቸውን የሚከውኑባቸውን አውዶች ለማስረዳት የተደረገው ጥረት ለዚኽ ጥናት ግባት በመኾን አገልግሏል፡፡ በተለይም ግጥም የሚደረድሩባቸው

ኢጋጣሚዎች ግብርና ጦርነት መኾናቸውን ማስረዳታቸው፤ እንዲሁም ምንጭ ጠቅሰው ስለ አዝማሪዎች ተግባር የገለጹት በግባትነት ተወስደዋል፡፡

### ፫. የአዝማሪ ተግባር በኅብረተ ሰቡ፣ በመሳፍንቱና በነገሥታቱ

አዝማሪዎች በተለያዩ ኢጋጣሚዎች ላይ ግጥሞችን ይደረድራሉ፡፡ በመግቢያው ላይ እንደ ተገለጸው አዝማሪዎች በግብር፣ በሰርግ፣ በክርስትና፣ በክብረ በዓል፣ በተዝካር ኢጋጣሚዎች ላይ በመገኘት ግጥም እየደረደሩ በማዜም ገንዘብ ያገኛሉ፡፡ በትልልቅ ከተሞች የሚኖሩ አዝማሪዎች የሰርግና የድግስ ታዳሚዎችን በማዝናናት ይሸለማሉ፡፡ አንዳንዶቹ ሰርግ እንዲያጅቡ ይጋበዛሉ፡፡ ለአጀቡበትም ገንዘብ ይከፈላሉ፡፡ ዛሬ ዛሬ በምሽት የጭፈራ ቤቶች ገንዘብ እየተከፈላቸው የሚዘፍኑም አሉ፡፡ የተወሰኑት ደግሞ የራሳቸውን የምሽት ጭፈራ ቤቶች በመከፈት ደንበኞቻቸውን እያዝናኑ በሚያገኙት ገቢ ሕይወታቸውን ይመራሉ፡፡

አዝማሪዎች በግጥሞቻቸው የታዳሚውን ቀልብ ለመሳብ፣ ለፈጣሪውም ምስጋና ለማቅረብ የመዲናና ዘለሰኛ ግጥሞችን በመደርደር ይጀምራሉ፡፡

“ብሩ የወታደሮቹን ታማኝነት ለማግኘትና ኃይሉን ለማጠናከር በማከታተል ግብር እያገባ፣ በጮማና በጠጅ ሲያንበሸብሻቸው ከረመ፡፡ በአዳራሹ አዝማሪ ያቆምና በቅርቡ ደጃች ውቤን እንደሚገጥም ግጥም እያስነገረ ሲያስፎክር ሰንብቷል፡፡ ደጃች ውቤ የራስ ዐሊ ጠላት መሆናቸውን ሁሉም ያውቃልና ይሄ ሁሉ እሳቸው ጆሮ እንደሚደርስ ያውቅ ነበር፡፡”

“ራስ ዐሊ በበኩላቸው በግብር ላይ አዝማሪ እያቆሙ ብሩን የሚያሞግስ ግጥም ያስገጥማሉ፡፡ ዘፋፎቻቸው ብሩ የዐሊ ዋርሳ፣ ብሩ የየውብ ዳር ባል፣ የውብ ዳር የዐሊ ተወዳጅ እህት እያሉ ለማነሳሳት የምስጋናና የአድናቆት ግጥሞችን እያዥጎደጎዱላቸው ይዘፍናሉ፡፡” (ገነት አየለ አንበሴ፣ 2009፤ 354)

አዝማሪዎች በግብር፣ በዘመቻ፣ በግዳይ መጣል፣ በሰርግ፣ በክርስትና፣ በታቦት ንግሥ፣ በክብረ በዓል፣ በተዝካር ኢጋጣሚዎች የምስጋና፣ የሙገሳ፣ የኩሰሳ፣ የቅስቀሳ፣ የምክርና የኀዘን እጉርጉሮ ግጥሞችን ያዜማሉ፡፡ የነገሥታቱ፣ የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ግብር የሚቀርበው በአዝማሪ ታጅቦ ነበር፡፡ ይኽንን በተመለከተ ገነት አየለ አንበሴ (2009፤ 248) “ግብር የሚገባ ቀን ሙሉ ቤት አዛዡ ረጂም ዘንጉን ይዞ ካባውን ደርቦ ተከታዮቹ ለግብር አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ ተሸክመው ይከተሉታል፡፡ ሥራዬ ቤቶች ጭሱ የሚትጎለጎል ትኩስ ወጥ የያዙ ድስቶቻቸውን ይዘው፣ እንጀራ ቤቶች፣ ጠጅ ቤቶች መሶብና ገምቧቸውን ተሸክመው እንቢልታ እየተነፋ መሰንቆ እየተመታ ተከታትለው ወደ ግብሩ አደዳራሽ ይገባሉ፡፡” (አጽንኦት የተጨመረ)

“ምሳ ሰዓት ሲደርስ ግብር እንዲገባ ተነገረና ከአጋፋሪዎቹ አንዱ ወጣ ብሎ አሽከሮችን አስገባ፡፡ መጀመሪያ የገባው ከወገቡ በላይ ልብስ ሳይለብስ ግማሽ እርቃኑን የሆነ አሽከር ሲሆን ሰውየው በራሱ ላይ ቀይ ቀለም ያለው ዘርፋፋ ጨርቅ የለበሰ የእንጀራ መሶብ ተሸክሟል፡፡

ከኋላው የእንጀራ ቤቱ፣ አንድ አዝማሪና ሁለት አሽከሮች ተከተሉት፡፡ አሽከሮቹ እንፋሎቱ እየተትጎለጎለ የሚወጣ ትኩስ ወጥ ያለባቸው ሁለት ድስቶችን ይዘዋል" (ገነት አየለ አንበሴ፣ 2009፤ 349 - 350)፡፡

"በግብሩ ሂደት መካከል አጫዋቾችና ጨዋታ አሳማሪዎች ቀልዳቸውን ይጀምራሉ፡፡ ሴት አዝማሪዎች ረጃጅም ሹርባቸውን ትከሻቸው ላይ ነስንሰው አንገታቸውን በመነቅነቅ ሲጫወቱ ግራ ቀኝ እያዘናፈሉት መረዋ ድምፃቸውን በማሰማት ይዘፍናሉ፡፡ ሲዝፍኑ የዐንገታቸው ደም ሥር ተገታትሮ እጃቸውን በአቅራቢያቸው ካለው አንዱ ወታደር ትከሻ ላይ ጣል አድርገው ሲዘፍኑ በግጥሞቻቸው እኔ ነኝ ያለውን የተመሠከረለት ጀግና እያጣጣሉ ወይም እያሞገሱ ይዘፍናሉ፡፡"

"ወዲው በመጠኑ ጋብ ብሎ የነበረው ጨዋታ እንደገና ተጀመረና ሁለት አዝማሪዎች መሰንቆ እየተጫወቱ ደጃዝማች የዋሉባቸውን የጦር ሜዳዎችና ድሎቻቸውን እንዲሁም የታወቁ ጀግኖቻቸው የሠሩትን ጀብድ እያነሳሱ ያሞካሿቸዋል"(ገነት አየለ አንበሴ፣ 2009፤ 308 - 309)፡፡

"አዝማሪዎች በአዘቦት ቀን ሁሉ ይገኛሉ" (ገነት አየለ አንበሴ፣ 2009፤ 265)፡፡ "አንዳንዴ የምሳ ወይም የእራት ሰዓታችን በጨዋታ ተራዝሞ ቀኑ እስኪዋገድ ምሽቱ ወደ ሌሊት እስኪቀየር የምንቆይበት ጊዜ አለ፡፡ ጠጅ እየተጠጣ ጨዋታው ይደራል፡፡ አዝማሪው ቀርቦ በጣዕመ ዜማውና በግጥሙ እያዋዛ ያዝናናናል" (ገነት አየለ አንበሴ፣ 2009፤ 352)፡፡

[ጠበሉ በቆዩበት ጊዜ] "ደጃዝማች የዕለት ተዕለት ፀሎታቸውን ለጊዜው አቋርጠዋል፡፡ እንዳሁኑ ከፀሎቴ ተስተጓጉዬ አላውቅም ይላሉ፡፡ አራት አዝማሪዎችና ሁለት አጫዋቾች እኛን ለማጨዎትና ለማዝናናት ተመድበዋል፡፡ ዘፈን ብቻ ሳይሆን ፉከራና ሽለላም አለ፡፡ በዚህ ሁሉ መሐል አልፎ አልፎ ከፋ ማለት አይቀርምና ከአዝማሪዎቹ አንዱ አንጀት በሚባሉ እንጉርጉሮዎቹ የታወቀ ኖሮ ልብ የሚነካ ዜማውን ባማረ ድምፁ ይለቀዋል" (ገነት አየለ አንበሴ፣ 2009፤ 340)፡፡

ደጅ አዝማች መንገሻ ከዘመቻ ተመልሰውና አብረዋቸው የዘመቱትን አብዛኞዎቹን አሰናብተው ወደ አንድ መንደር ሲቃረቡ እያጀበ የሚከተላቸው "ሰው እየበዛ ይመጣል፡፡ አቤቱታ አቅራቢው፣ ስጦታ ያመጣው ሀብታም ነጋዴ፣ ባለመሬቱ፣ ሽማግሌና ባልቴቱ፣ ለማኙ፣ ቄሱ፣ ዘፋኙ ምኑ ቅጡ ሁሉም እየተንጋጋ ይመጣና "ደጃዝማችን እንኳን ደህና መጡ" እያለ ይቀበላቸዋል፡፡ ...ከአጎራባች መንደር ያሉ ካህናት ሳይቀሩ ልብሰ ተክህኗቸውን ለብሰው ወረብ እየወረቡ ይቀበላሉ፡፡ ወጣቱ ገበሬ ደረትና ትከሻውን ገላልጦ እየጨፈረ፣ ቆነጃጅት በአንገታቸው እስክስታ እየወረዱ እናቶቻቸው እያጨበጨቡና እልል እያሉ ጭፈራና ዘፈኑን ያስነኩታል፡፡ በከራርና በእምቢልታ በማሲንቆና በከበሮ እየታጀበ የሚቀልጠውን ዘፈንና ጨዋታ እያየን እንገባለን" (ገነት፣ 2009፤ 236)፡፡

"በዚህ ዓይነት ከፊታችን የተዘረጋውን ሜዳ እያቆራረጥን ወደ ፊት ቀጠልን፡፡ ፈረሰኞች እርስ በእርሳቸው በመጨዋወት ዘና ብለው ሲጓዙ እግረኛው ከእግሩ ነጠቅ ነጠቅ እያለ በፈጣን

እርምጃ ይገሰግሳል፡፡ ጉዟችን በፀጥታ ሳይሆን በልዩ ልዩ ሙዚቃ እየታጀብን ነው፡፡ አብሮን የሚጓዘው ታምቡርና ነጋሪት ገብር… ገብር… እያለ እምቢልታው እየተነፋ አዝማሪው መሰንቆን እየመታ አልፎ አልፎ የነሸጠው እየሸለለና እያቅራራ ነበር፡፡ በቀረርቶ በሽለላ የደጃዝማች ስም ይነሳል፡፡ የጀግኖች ስም ይወደሳል፡፡ ደጃዝማች ረጋ ብላ በምትሰግረው በቅሏቸው ላይ በግርማ ተቀምጠው ሲጓዙ ላያቸው በግዛታቸው ያለውን ሰው ሁሉ ክተት ብለው የሚሄዱ ይመስላል፡፡" (ገነት፣ 2009፤ 183)

"ትንሽ ራቅ ብሎ ከስድስት እስከ ሰባት መቶ የሚጠጉ ባለጋሻዎች ወደ ፍልሚያው ጎራ ለመግባት የመጨረሻውን ዝግጅት እያደረጉ ነው፡፡ ከዚያም ፍልሚያው ወዳለበት እየተንጎማለሉ ሄዱ፡፡ አንድ አዝማሪ ባማረ ድምፁ የሚያነቃቃ የጀግንነት ግጥም እየገጠመና እየዘፈነ ከፊት ከፊታቸው ይሄዳል፡፡" (ገነት፣ 2009፤ 314)፡፡

ሴት አዝማሪዎች እነዚህን አስፈሪ ተዋጊዎች በስም እየጠሩ በእጆቻቸው መታ እያደረጉ እያሞካሹ በዘፈን ፍቅር በተሞላው አበረታች ግጥም ይሸኟቸዋል፡፡

"አካሌዋ! የአይኔ ብሌን" ትላለች አንደኛዋ ሴት "በፍቅርህ ብሞት ምንም አይጨንቀኝ! ጉልበቴ ቢደክም ዘፈኔ ቢያልቅ ምን ይጨንቀኛል፡፡ ብቻ በቸር ተመለስ!" (ገነት፣ 2009፤ 315

ወይንም ፈረሱን ታሞግሳለች

"ሂድ የኔ ንስር አሞራ! ብረር ጌታዬ! ፈጣሪ ክንፍህን ያጠንክርልህ!"

ሌላዋ ደግሞ

"የጦሩ ጌታ! ቅደም እዚህ እጠብቅሃለሁ፡፡ እዚህ የቆምኩት ጀግኖችን ለማየት፣ ሙያቸውን ለመቁጠር ነው" ትላለች

እዚያ የቆመቺው ደግሞ ጀግናዋን ትከሻውን ጠበቅ አድርጋ መታ መታ እያደረገች "እኔ እኮ እህትህም ነኝ፡፡ የኔ ነብር! አስፈራኸኝ እኮ!! ጦርህን እንዳላየው ከጠላትህ ጎን ቀብቅበኸው ናልኝ" ትለዋለች፡፡

አዝማሪው ጮክ ብሎ

"ገለል በልና ገለል አርጋቸው

ወደ መጡበት ወዳገራቸው" አለና "ወደኋላ! ወንድና ሴቱ የሚለይበት ሰዓት ደረሰ! የሴት ልጅ ሁላ! ወደኋላ! ዕቃውን ጠብቁ! ወንድና ሴቱ ሊለይ ነው፡፡ ድስትና ገምቦውን ተውት ወዲያ፡፡ የአሞራ ሠርግና ምላሽ ሊሆን እኮ ነው! የአሞራውን ድግሱን አታበላሹ! እውነተኛዎቹ ወንዶች ደረሱ፡፡ እሰይ ጦር ወርዋሪዎቹ እሰይ ባለክንፍ ፈረሰኞቹ! ለጌታችን ለንጉሥ ጎሹ መንገዱን

አስለቅቁ፡፡ ይህን ቡከን ሁላ ረጋግጦ መሄድ ይፈልጋል ጌታችን፡፡ በርቱ ጮማው ለናንተ ነው፡፡ ጠጁ ለናንተ ነው፡፡ ሂዱ አንበሶቼ" እያለ ሸኛቸው፡፡

ከወዲያ ካሉት ወታደሮች አንዳንዶቹ መለሱለት "ሰማህ ወይ ወንድም! ስንመለስ ዕድሜ ልክ ለምትዘምርበት ግጥም የሚበቃ ድል ይዘንልህ እንመጣለን!" ሌሎች ደግሞ "በቃ በቃ ወሬ በቃ! ውጊያው ይጀመር፡፡ እኛ ሙያ እንሥራ እዚህ ቀረህ አሽከሮችን ጠብቅ"

ደጃዝማች ገና አልዘመቱም፡፡ ከድንኳናቸው በር ድንክ አልጋቸው ላይ ቁጭ እንዳሉ ነው፡፡ (ገነት፤ 2009፤ 316)

ምጽዋ የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል ኬምሮን ከንግሥት ቢክቶሪያ የተላኩትን መልእክት ለማድረስ ወደ ዐፄ ቴዎድሮስ ጎንደር መጡ፡፡ ኬምሮን ከሃማሴን ጀምረው ጎንደር ሲደርሱ ግሩም ድንቅ አቀባበል ተደረገላቸው፡፡ ለቆንሱ ክብር በአዳራሽ በተዘጋጀው ግብዣ ንጉሡ ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰውና ዘውዳቸውን በራሳቸው ደፍተው ተገኙ፡፡ ሊቀ መኳሶች፣ ራሶችና ደጅ አዝማቾች የክብር ልብሳቸውን ለብሰው ታደሙ፤ የንጉሡ ጋሻ ጃግሮችም በሚያስፈራ ግርማቸው የተማገረ ግድግዳ መስለው ቆሙ፡፡ የተዘጋጀው ግብር ወደ አዳራሹ መጥቶ ምግቡ እየተበላ (ለቆንስሉ በፈረንጆች ወጥ ተሠቶላቸውና ማለፍያ ጥብስም ቀርቦላቸው) የወይን ጠጅም የማር ጠጅም እየተማረጠ እየተጠጣ፣ አስተርጓሚ ቀርቦ፣ ማለፍያ ማለፍያውን እተጫወቱ እያሉ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ በግብሩ አደዳራሽ የተገኘውን አዝማሪ "አጫውተን" እያሉ ይጋብዙታል፡፡ እሱም ልዩ ልዩ ግጥሞችን እየደረደረ ያስቃቸዋል፡፡[2] "መልካሙን ጨዋታ እየተጫወቱ ቆዩ፡፡ ለቆንስሉ የተደረገው ሙሉ ግብር ስለ ነበር "ሲበላ ሲጠጣ አዝማሪዎችም ሽለሌ እያሉ ተጫውተው ታበቁ ወድያው ግብር ምላሽ ሆነና ቆንሱልም ወደ ታዘዘላቸው ስፍራ ሔዱ" (Fusella, 1959፡ 64 - 65)፡፡

በአዝማሪ የቀረቡትን ቃለ ግጥሞች መልእክት ቀጥለው በሚቀርቡት ንዑሳን ርእሶች እንመለከታለን፡፡ የደጅ አዝማች ካሣን (በኋላ ዐፄ ቴዎድሮስን) የደረደሯቸውን የሙገሳ ግጥሞች እንመለከታለን፡፡

## ፩. ስለ ደጅ አዝማች ካሣ (ዐፄ ቴዎድሮስ) ጀግንነትሙገሳ በአዝማሪ የተዜሙ ግጥሞች

ሙገሳ የሚለው ቃል ምስጋና፣ አድናቆትና ውዳሴ ማለትን ይገልጻል፡፡ በዚኽ ንዑስ ርእስ የምንመለከተው አዝማሪዎች የዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንነት፣ የዘር ሐረግ፣ ዓላማና ሰብእና በግጥሞቻቸው እንዴት እንዳሞገሱና ታሪካዊና ባህላዊ እውነታውን እንዴት እንደገለጹ ነው፡፡

---

[2] የሚያጫውታቸው አዝማሪ ዐፄ ቴዎድሮስ ሲስቁለት በስሜት ተገፋፍቶ ንጉሡን ያስቆጣል፡፡ ነገር እንደ አዳጠው "አጤ ቴዎድሮስ እንደ እሳት ቡልጭ" ይሉበታል፡፡ ቁጣቸው ያስደነገጠው አዝማሪም ቶሎ ብሎ፡-

"ፍቅሩን ጨርሶ ጠቡን ሲያመጣው
ሞላጫ ገደል ዝንጀሮ አይወጣው፡፡

በማለት ገጠመላቸውና "ሳቁለት ይላሉ" (Fusella, 1959፡ 64 - 65)፡፡

የሙገሳ ግጥሞቹን በዘመን ቅደም ተከተል ወይም በታሪክ ኺደት ወደ ኋላና ወደ ፊት ተመልክተናል፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹም በሦስት ንዑስ ርእሶች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው ንዑስ ርእስ ትኩረት ደጅ አዝማች ካሣ በመሳፍንቱ ላይ አምጸው በነበረበት ጊዜ ባገኟቸው ወታደራዊ ድሎች በተሞገሱባቸው ቃል ግጥሞች ላይ ነው፡፡ ኹለተኛው ንዑስ ርእስ የመሳፍንቱን ግዛቶች ነጥቀው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተብለው ከነገሡ በኋላ በየጊዜው የተነሡባቸውን ተቃዋሚዎቻቸውን ድል በማድረጋቸው በተሞገሱባቸው ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ሦስተኛው በንዑስ ርእስ ከመሳፍንቱ ግዛቶች ውጭ የነበሩ ቦታዎችን ነፃ ለማውጣት የነበራቸውን ምኞት በሚያሞግሱ ቃለ ግጥሞች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ የሙገሳ ግጥም ምርመራችን ደጅ አዝማች ካሣ በማመጻቸው ምክንያት በተለያዩ ጊዜያቶች የዘመተባቸውን ጦር ድል በማድረጋቸው በተሞገሱባቸው ግጥሞች እንጀምራለን፡፡

### ፩. ፩. ደጅ አዝማች ካሣ በማመጻቸውና ወታደራዊ ድል በማግኘታቸው መሞገሳቸው

ለደጅ አዝማች ካሣ የተደረደሩት የሙገሳ ግጥሞች ወደ ሥልጣን ለመምጣት ካደረጉት አመጽና ትግል ይጀምራሉ፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ወደ ሥልጣን ባደረጉት ትግል፣ በተለያዩ ቦታዎች ባካኼዷቸው ጦርነቶችና በተቀናቃኞቻቸው ላይ በተቀዳጁዋቸው ድሎች በአዝማሪዎች ተሞግሰዋል፡፡ የደጅ አዝማች ካሣ ኃይሉ አመጽ የጀመረው በጎንደር ቤተ መንግሥት ነው፡፡ በቤተ መንግሥት ለእቴጌ መነን አክብሮት አልሰጥም፣ "እንቢ" ብለው ማመፃቸው ማለታቸው ተገቢ መኾኑን አዝማሪ፡-

> ለቴዬ መነን ሙላው ሲነሣ፤
> አንፈራጠጠ እምቢ አለ ካሣ፡፡ (Mitgeteilt, 33)

ብሎ አሞግሷቸዋል፡፡

በግጥሙ የደጅ አዝማች ካሣ አመጽ የተገለጸው ለእቴጌ መነን አክብሮት ለመስጠት ከተቀመጡበት ለመነሣት ፈቃደኛ ባለመኾን ነው፡፡ በግጥሙ እንደ ተገለጸው ደጅ አዝማች ካሣ አንፈራጠው ተቀምጠው አለመነሣታቸው ለእቴጌይቱ የሚገባቸውን ክብር አለመስጠታቸውን ይገልጻል፡፡[3] በግጥሙ እንደ ተገለጸው በአመፃቸው ከቤተ መንግሥት ሥርዓት ውጭ የኾነ ድርጊት ፈጽመዋል፡፡ ድርጊታቸው፣ "አልታዘዝም"፤ "እምቢ"፣ "አሻፈረኝ" ማለታቸው የተገለጸው፣ እግርን አንፈራጦ በመቀመጥ ነው፡፡ አንፈራጠጠ የሚለው ቃል በትእቢትና በኩራት እንቢ ብሎ እግርን ከፊት አድርጎና ቦታ አስፍቶ መቀመጥ ወይም መቆም ማለትን ይገልጻል፡፡ ደጅ አዝማች

[3]በባህል ታናሽ ለታላቅ፣ ልጅ ለወላጅ፣ ንስሐ ልጅ ለንስሐ አባት፣ ሚስት ለባል፣ ሎሌ ለጌታው፣ ያለውን አክብሮት ከሚገልጽባቸው መንገዶች አንዱ፣ ከተቀመጠበት መነሣት ነው፡፡ አክባሪው ወደ ተቀመጠበት ቦታ (ቤት ውስጥም ይኹን ከቤት ውጭ)፣ ተከባሪው በሚኼድበት ጊዜ አክብሮትን ለመግለጽ ከተቀመጠበት/ ከተቀመጠችበት ይነሣል/ትነሣለች፡፡ ይኽ ዓይነቱ አክብሮት በቤተ መንግሥትም የተለመደ ነው፡፡ በባህሉ ሊከበር ለሚገባው ሰው ከተቀመጡበት በመነሣት አክብሮት አለመስጠት በኹለቱ ሰዎች መካከል አለመግባባት መኖሩን ይጠቁማል፡፡ ይኽ ዓይነቱ አክብሮት በቤተ መንግሥትም የተለመደ ነው፡፡

ካሣ አንፈራጠው መቀመጣቸው ለቤተ መንግሥቱ ተገቢውን ክብር አለመስጠታቸውን፣ ትእቢት፣ ኩራት፣ ንቀትና እምቢታ ማሳየታቸው ያስረዳል፡፡ ከዚኽም በላይ፣ አንፈራጠው በመቀመጣቸው ቦታ አስፍተው መያዛቸውንና ለሌላ ሰው በአጠገባቸው እንዳይቀመጥ መከልከላቸው ማመጻቸውን ይገልጻል፡፡

አንፈራጠው መቀመጣቸውና ለእቴጌይቱ ክብር አለመስጠታቸው የእቴጌይቱን ቁጣ ቀስቅሷል፡፡ ቁጣውም ውግዘትን አስከትሏል፡፡ በፈጸሙት ድርጎት "ቅጣት ይደርስብኛል" በሚል ሥጋትም ደጅ አዝማች ካሣ ከቤተ- መንግሥት ሸሽተውና ርቀው ኼደዋል፡፡ ሸሽተው መኼዳቸው የተቃጣባቸውን ጥቃት ከመከላከልና ከመጋፈጥ እንዳልታደጋቸው ታሪካቸው ያስረዳል፡፡[4] ደጅ አዝማች ካሣ ከእቴጌ መነን የተላከባቸውን ጦር ለመከላከልና ለመመከት የሚያስችል ዝግጅት አደረጉ፡፡ ማንፈራጠጣቸው ሰፊ ቦታ ይዘው ኃይላቸውን አደርጅተውና ለጦርነት ተዘጋጅተው መጠበቃቸውን ይገልጻል፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ አንፈራጠው መቆማቸው በቀላሉ ተገፍተው እንዳይወድቁ፣ እንዳይማረኩ፣ እንዳይያዙ አድርጓቸዋል፡፡ መጀመሪያ በእቴጌ መነን የታዘዘውንና በወንድይራድ የተመራውን፣ በኋላም በእቴጌይቱ በራሳቸው መሪነት የዘመተባቸውን ጦር ገጥመው ድል አደረጉ (ተክለ ኢየሱስ፣ 2008፤ 205)፡፡ ይኽም የማንፈራጠጣቸው ውጤት ነው፡፡

ራስ ዓሊ እናታቸው እቴጌ መነን በደጅ አዝማች ካሣ መማረካቸውን ሲሰሙ የጎጃምን ጦር በደጅ አዝማች ጎሹ እግር (መሪነት) እንዲዘምት አዘዙ፡፡ ደጅ አዝማች ጎሹና ደጅ አዝማች ካሣ ጉራምባ ላይ ተዋጉ፡፡ ከኹለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ፡፡ ደጅ አዝማች ጎሹ በጦርነቱ ሞቱ፡፡ ከጦራቸው ብዙው ተማረከ፤ የተረፈውም ሸሸ፡፡ ድሉ የደጅ አዝማች ካሣ ኾነ፡፡ በጦርነቱ ባለቀው ሰው ሬሳ የመገጭ ወንዝ መሺጋገሪያ ሞላ፡፡ መገጭ ወንዝ መሺጋገሪያ ላይ የተደረደረው አስከሬን የማንኛው ወገን እንደ ኾነ ባይታወቅም ድል አድራጊው ደጅ አዝማች ካሣ በመኾናቸው በአዝማሪ አብተው አስሞግሷቸዋል፡፡ በገሪማ (፲፱፻፺፮፣ ፻፫) የተመዘገቡት የሙገሳ ግጥሞች የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩) ጋላ [አሮሞ] ባባ ሄደ ሊገባ አገሩን፣
እያመሰገነ ደጅ አዝማች ካሣን፡፡

፪) መሺጋገሪያውን እንዲያ ስንፈራው፣
ካሣ ደለደለው መገጭን በሰው፡፡

በመጀመሪያው ቃለ ግጥም በቀጥታ የሚነገረው ፊታውራሪ ባባ የተባለው የራስ ዓሊ ጦር መሪ ደጅ አዝማች ካሣን ማመስገኑ ነው፡፡ ፊታውራሪ ባባ ከደጅ አዝማች ጎሹ ጦር ጋር

[4]ልጅ ካሣ ተብለው የእቴጌ መነንን የልጅ ልጅ ተዋበችን ካገቡ በኋላ፣ "በቤተ መንግሥት ክብር አልተሰጠኝም" በማለት ከጎንደር ቤተ መንግሥት ሸሽተው ወደ ቋራ ወርደው አመጹ፡፡ በግዛታቸው እንደሚገኙት ምስለኔዎች ለመታዘዝ ፈቃደኛ አለመኾናቸው እቴጌ መነንን አስቆጣ፡፡ በድርጊቱ የተቆጡት እቴጌ መነን ልጅ ካሣን የሚወጋ ጦር ላኩ፡፡ የላኩት ጦር ግን በልጅ ካሣ ጦር ድል ኾነ፡፡ በላኩት ጦር መሸነፍ የተበሳጩት መነን ራሳቸው ጦር መርተው ልጅ ካሣን ለመውጋት ዘመቱ፡፡ እሳቸውም ድል ኾነው ተማረኩ (ተክለ ኢየሱስ፣ 2008፤ 205)፡፡

በመተባበር ደጅ አዝማች ካሣን ለመውጋት ዘምቶ በደጅ አዝማች ካሣ ጦር በመሸነፉ፣ ሸሽቶ ወደ አገሩ ለመግባት መገጭ ወንዝን የተሻገረው የተደረደረን አስከሬን ረግጦ ነው፡፡ ከተከናወነው ታሪካዊ ድርጊት መረዳት እንደሚቻለው ፊታውራሪ ባባ ይመራው የነበረውን ጦር ያጠቃበትንና እሱን የሚያሳድዱት ደጅ አዝማች ካሣን ሊጠላቸውና ሊረግማቸው እንጂ ሊወዳቸውና ሊያመሰግናቸው አይችልም፡፡ በቃለ ግጥሙ የተነገረው ምፀትም በቀጥታ ከተነገረው ምስጋና በተቃራኒ ርግማን እንደኾነ ከታሪካዊ ዐውዱ መረዳት ይቻላል፡፡ ፊታውራሪ ባባ መርገሙ ደጅ አዝማች ካሣን እንዴት ያስሞግሳቸዋል? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ርግማኑ ደጅ አዝማች ካሣ ፊታውራሪ ባባንና ደጅ አዝማች ጎሹን በማሸነፋቸው ምክንያት ነው፡፡ በወታደራዊ አቅማቸው በደጅ አዝማች ጎሹና በፊታውራሪ ባባ ከሚመራው ጦር ያንሳል ተብሎ የተገመተው የደጅ አዝማች ካሣ ጦር ያልተገመተ ወታደራዊ ድል በማግኘታቸው ለመሞገሳቸው ምክንያት ነው፡፡ በደጅ አዝማች ካሣ ጦር ከፉኛ የተጠቃው ፊታውራሪ ባባ፣ ይመራው የነበረው ጦር ጥቃት ያደረሰበትን ደጅ አዝማች ካሣን እየረገመና እየሰደበ ከጥቃቱ ተርፎ መሸሹን ግጥሙ ያስረዳል፡፡

በኹለተኛው ቃለ ግጥም እንደ ተገለጸው አስፈሪ የነበረው የመገጭ ወንዝ መሸጋገሪያ በደጅ አዝማች ካሣ ጦር በተገደለው በደጅ አዝማች ጎሹና በፊታውራሪ ባባ በሚመሩት ጦር አስከሬን በመሙላቱ ቀድሞ የነበረውን አስፈሪነት አጥቷል፡፡ ወንዙን የሞላው አስከሬንም እንደ ድልድይ በማገልገሉ ቀድሞ ድልድይ ባለመኖሩ/ባለመሠራቱ ምክንያት ለመሻገር ያስቸግር የነበረው የመገጭ ወንዝ አስከሬን ረግጦ መሻገር የሚቻልበት ኹኔታ በመፈጠሩ አስቸጋሪነቱ ቀርቷል ማለትን ይገልጻል፡፡ ይኽም በጦርነቱ ያለቀውን ሰው ብዛት ያስረዳል፡፡ አዝማሪ አብተው በጦርነቱ ያለቀውን ሰው የደጅ አዝማች ካሣ የጀግንነት ውጤት መኾኑን ገልጾበታል፡፡

ራስ ዓሊ ደጅ አዝማች ካሣ ማሸነፋቸውን እንደሰሙ "በዓቢይ ጾም የካቲት ፰ ቀን ፬ ደጃዝማቾችን ያዘውን፣ በለውን፣ አብዬን፣ ብሩ አሊጋዝን አድርጎ ወደ ደጅ አዝማች ካሣ ሰደደ፡፡ ደጅ አዝማች ውቤንም ፫ አምበል ጦር[5] ከሰሜን ጨመረላቸው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ግን ፯ቱን ነጋሪት ሁሉንም ተቀብሎ ፈጃቸው" (ተክለ ኢየሱስ፣ 2008፤ 206)፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ በስም የተጠቀሱትን ዐምሥት ደጅ አዝማቾችና በስም ያልተጠቀሱትን ኹለት ደጅ አዝማቾች ድል አደረጓቸው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ድል በማድረጋቸውም በአዝማሪ አብተው በሚከተለው ግጥም መሞገሳቸውን ገሪማ (፲፱፻፶፯፤ ፻፭) ገልጸዋል፡፡

ሰባቱ ደጅ አዝማች ስምንተኛው ካሣ፣
ምርት አደረጋቸው ወቅቷቸው ተነሣ፡፡

አዝማሪ አብተው ደጅ አዝማች ካሣን ያሞገሰው፣ ብቻቸውን ከእሳቸው ጦር እጅግ የሚበዛውንና በሰባት ደጅ አዝማች የሚመራውን ጦር ከባድ ጥቃት በማድረስ ማሸነፋቸው ነው፡፡

---

[5]አምበል (አንበል) የሚለው ስም መሪ፣ አለቃ፣ አዛዥ፣ አዝማች ማለት ሲኾን፣ ደጅ አዝማች ካሣን እንዲወጉ ከደጅ አዝማች ውቤ ጋር እንዲዘምቱ የተደረጉት አምበሎች የኹለቱ ስማቸው ባይገለጽም የደጅ አዝማችነት ማዕረግ ነበራቸው፡፡ በእቴጌ መነን መሪነት ደጅ አዝማች ካሣን ለመውጋት በሰኔ ወር የዘመቱት ደጅ አዝማቾች ብዛት ሰባት እንደ ነበር ደብተራ ዘነብ ጽፈውት በሊትማን (፲፱፻፬፤ ፲፫) በታተመው የዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ተገልጿል፡፡

ትልቅ የእኽል ክምር በአንድ አውድማ በአንድ ገበሬ እንደሚወቃው ኹሉ፣ የሰባቱ ደጃዝማቾች ጦር በአንድ ደጅ አዝማች ካሣ ጦር በአንድ የጦርነት ቦታ ድል ኾኗል፡፡ አሸናፊነታቸው ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ መኾኑን "ምርት አደረጋቸው ወቅቷቸው ተነሣ" በሚለው ስንኝ ተገልጿል፡፡ "ምርት አደረጋቸው" የሚለው ለዋጭ ዘይቤ በደጅ አዝማች ካሣ ጦር የተገደሉትን የሰባቱን ደጅ አዝማቾች ነፍጥ አንጋቾች ብዛትና አስከሬናቸው በአንድ ቦታ መከመሩን ያስረዳል፡፡ "ወቃቸው" የሚለውም በኃይል መመታታቸውን፣ መደብደባቸውንና መጠቃታቸው ይነግራል፡፡ ዐውድማ ላይ የሚወቃ እኽል በበሬ እንደሚረገጠው ወይም  በበትር እንደሚደበደበው ኹሉ፣ በጦርነቱ የተሸናፊዎቹ ሰባት ደጅ አዝማቾች ነፍጠኞች ተጠቂና የሚደርስባቸውን ከባድ ጥቃት ተገደው ተቀባዮች እንጂ ራሳቸውን የሚከላከሉ፣ ጠላታቸውን የሚመክቱ እንዳልነበሩ የሙገሳ ግጥሙ ይገልጻል፡፡ "ወቅቷቸው ተነሣ" የሚለው ሐረግም የደጅ አዝማች ካሣን ጦር አሸናፊነት የጠላቶቹን ተሸናፊነትና መደምሰስ ስለ ማረጋገጡ፣ የደጅ አዝማች ካሣ ጦር ጥቃት መሰንዘሩን የተወው በራሱ ፈቃድ ጠላቶቹ መሸነፋቸውን በማረጋገጡ ስለ መኾኑ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

ጎጃምን ይገዙ የነበሩት የደጅ አዝማች ጎሹ በራስ ዓሊ ታዘው ደጅ አዝማች ካሣን ለመውጋት ሲዘምቱ፣ የጦራቸው ብዛትና ጥንካሬ ሲገመገም በደጅ አዝማች ካሣ ይሸነፋል ተብሎ አልተገመተም፡፡ ይልቁንም፣ ጦራቸወው በንቀትና በአሸናፊነት እምነት እንደ ነበር አዝማሪ ጣፋጭ ደጅ አዝማች ካሣን ያኰሰሰበት ግጥም ያስረዳል፡፡[6] ነገር ግን፣ "ናቂ ወዳቂ" እንደሚባለው በኹለቱ መካከል ጦርነቱ ሲካኼድ ትልቁ ጀግና ደጅ አዝማች ጎሹ በጦርነቱ ተሸንፈው ወደቁ፡፡ ድል የደጅ አዝማች ካሣ ኾነ፡፡ በድሉም የደጅ አዝማች ካሣ ጀግንነትና ስም ገኖ ወጣ፡፡ በቅርብም በሩቅም የሚገኙ መሳፍንት ራስ ዓሊም ጭምር የደጅ አዝማች ካሣን አሸናፊነት በፍርሐትና በሥጋት ሰሙት፡፡ ራስ ዓሊ ከደጅ አዝማች ካሣ ጋር ጦርነት ለመግጠም ባለመፈለግ፣ በእሳቸው ታዘው በመዝመት በደጅ አዝማች ጎሹ ላይ የተፈጸመውን ግድያ ወደ ጎን ትተው ግዛት አስፍቶ በመስጠት ደጅ አዝማች ካሣን ለመደለል ሞከሩ፤ አልተሳካላቸውም፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ራስ ዓሊ ያዘመቱባቸውን ሰባት ደጅ አዝማቾች ድል በማድረግ የራሳቸውንና የሠራዊታቸውን የአሸናፊነት ስሜት በመገንባታቸው ከራስ ዓሊ የቀረበላቸውን የግዛት ማባባያ በመቀበል ጥቃት ከመሰንዘር ለመታቀብ ፈቃደኛ ሳይኾኑ ቀሩ፡፡

---

[6]ደጅ አዝማች ጎሹም ዠግንነት ከኀይል ጋር የሚሰማቸውና የጦር ሠራዊታቸው አያሌ ስለ ነበረ ደጅ አዝማች ካሣ ወደ አሉበት ቦታ ይዘምታሉ፡፡ በእሳቸው እየተመራ የዘመተው ጦር ፍልሚያ ከመጀመሩ በፊት አዝማሪያቸው ጣፋጭ በሠራዊቱ መካከል ኾኖ የደጅ አዝማች ካሣን የውጊያ አቅም አኮስሶ ይሰድባል፡፡ የደጅ አዝማች ጎሹን ጦር ደግሞ ውጊያውን እንዲጀምር ይቀሰቅሳል፡፡ በተክለ ኢየሱስ (2008፤ 205) የተመዘገበው ቃለ ግጥም የሚከተለው ነው፡፡

> አያችኹት ቢያ የኛን ዕብድ፣
> ዐሥር ጋሞች ይዞ ጉር አምባ ሲወርድ፡፡
> ያንጓብባል እንጂ፣  መች ይዋጋል ካሣ፣
> ወርደኽ ጥመድበት፣ በሸንብራው ማሳ፡፡
> ወዶ ወዶ፣
> በሴቶቹ በነጉንጭት ለምዶ፡፡

አዝማሪ ጣፋጭ በቅስቀሳ ግጥሙ የደጅ አዝማች ካሣን ጦር ቁጥር የደጅ አዝማች ጎሹን ጦር ለመዋጋት ያለውን አቅም አሳንሶ፣ አኰስሶና ፣ በተዘዋዋሪ መንገድ የደጅ አዝማች ጎሹን ጦር አብዝቶ የመዋጋት አቅሙን አጎልብቶና አግዝፎ ገልጿል፡፡

ምንም እንኳን የደጅ አዝማች ካሣ አሸናፊነትና ጀግንነት ቢናኘም፣ በዘመኑ የበላይነት የነበራቸውን ራስ ዓሊን ከላያቸው አስቀምጠው ዓላማቸውን እንደማያሳኩ የተገነዘቡት ደጅ አዝማች ካሣ ፊታቸውን ወደ ራስ ዓሊ አዞሩ፡፡ ራስ ዓሊን ለመውጋት ወስነው የዛቻ ቃል ላኩባቸው፡፡ ተቀናቃኞቹን ድል በማድረግ የሥነ ልቦና መነቃቃት የነበረውን ጦራቸውን ይዘው ራስ ዓሊ ወደሚገኙበት ወደ ጎጃም ዘመቱ፡፡ በደጅ አዝማች ካሣ ድርጊት "እንዴት ተደፈርኹ" ማለት ያልቻሉት ራስ ዓሊ ከሰዎቻቸው ጋር መከሩ፤ ጦርነት ለመግጠምም ወሰኑ፡፡ የፍልሚያ ሜዳቸውን አይሻል ላይ አደረጉ፡፡ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፰፻፵፭ ዓ. ም. አይሻል ሜዳ[7] ላይ ባካኼዱት ጦርነት ድሉ የደጅ አዝማች ካሣ ኾነ፡፡ ተሸናፊው ራስ ዓሊ ሸሹ፡፡ የራስ ዓሊ የበላይነት አከተመ፡፡ የደጅ አዝማች ካሣ ጀግንነትና የበላይነት የማሳረጊያ ምዕራፍ ተጀመረ፡፡ ቀሪውን የሥልጣን ጉዟቸውን የቁልቁለት መንገድ አደረገው፡፡

ደጅ አዝማች ካሣን አዝማሪ አብተው ማሞገሱን ገሪማ (፲፱፻፺፮፤ ፵፯) ገልጸዋል፡፡ የሙገሳ ቃለ ግጥሙም የሚከተለው ነው፡፡

ዓሊን አይሻል ላይ ጎሹንም ጎርጎራ፤
ታግሎ የጣላቸው ሁሉንም በየተራ
ለኢትዮጵያ ቢሆን ነው ከአምላክ ባላደራ፡፡

የሙገሳ ግጥሙ ደጅ አዝማች ካሣ ድል ካደረጓቸው መሳፍንት መካከል ኹለቱን ይጠቅሳል፡፡ በግጥሙ የተጠቀሱት ድሎች ደጅ አዝማች ካሣ ወደ ሥልጣን በሚያደርጉት ትግል ወሳኝ ነበሩ፡፡ በግጥሙ ከተጠቀሱት ድሎች የሚቀድመው ጎርጎራ [ጉር ዐምባ] ላይ ደጅ አዝማች ጎሹን ያሸነፉበት ጦርነት ነው፡፡ ራስ ዓሊን ድል ማድረጋቸው በግጥሙ ቀድሞ መገለጹ ለደጅ አዝማች ካሣ የትግልና የአሸናፊነት ርምጃ የነበረውን ወሳኝነት ይገልጻል፡፡ ከደጅ አዝማች ጎሹ በፊት መጀመሪያ በእቴጌ መነን የታዘዘውንና በፊታውራሪ ወንድይራድ የተመራውን፣ በኋላም በእቴጌ መነን በራሳቸው መሪነት የዘመተባቸውን ጦር ቢያሸንፉም፣ ራስ ዓሊም ኾኑ ደጅ አዝማች ጎሹ ጀግንነታቸውንና አሸናፊነታቸውን አምነው አልተቀበሉም፣ አሸናፊነታቸውን አላመኑላቸውም ነበር፡፡ አዝማሪው ደጅ አዝማች ካሣ ቀድመው ያገኟቸውን ድሎች ጉር ዐምባ ላይ ደጅ አዝማች ጎሹን፣ አይሻል ላይ ደግሞ ራስ ዓሊን ወግተው ካገኟቸው ድሎች ጋር በእኩል ደረጃ አልተመለከታቸውም፡፡

ለኢትዮጵያ ባለ አደራ ኾነው ከአምላክ መላካቸው የሚገልጸው ስንኝ፣ የደጅ አዝማች ካሣ ዓላማ በዘመኑ ከነበሩት መሳፍንት በተሻለ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠቅማል ተብሎ መታመኑን ይገልጻል፡፡ የደጅ አዝማች ካሣ ፍላጎት በኢትዮጵያ የዘመነ መሳፍንት አውራ የነበሩትን ራስ ዓሊን አሸንፎ ግዛታቸውን ጠቅልሎ በመያዝ በሥራቸው የነበሩትን በማስገበር የተገደበ አልነበረም፡፡ ከራስ ዓሊ ግዛት የሰፋና ኢትዮጵያ የምትባል አገርን መምራት እንደ ነበር የሙገሳ ግጥሙ ያስረዳል፡፡

[7]አይሻል ሜዳ ከደብረ ማርቆስ ከተማ በስተ ምሥራቅ በሙጋና በበጨት ወንዞች መካከል የሚገኝ ሜዳ ነው (Girma Getahun, 2014: 295 )፡፡

ከግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው የደጅ አዝማች ካሣ ድሎች በፈቃደ እግዚአብሔር የተገኙ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ አዝማሪ አብተው እንደ ገለጸው፣ ደጅ አዝማች ካሣ ከእሳቸው የበለጠ ጉልበት የነበራቸውን መሳፍንት ያሸነፉት፣ ኢትዮጵያን እንዲታደጉ፣ እንዲጠብቁ አምላክ ፈቅዶ ስለ ላካቸውም ነው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ አምላክ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እረኛ፣ መሪ፣ አሳዳሪ እንዲኾኑ በመፍቀዱ በግጥሙ በፈቃደ እግዚአብሔር ተመርተው ለጠላቶቻቸው እሳትና ስለት፣ ለወዳጆቻቸው ደግሞ፣ ሹመትና ሽልማት ሰጡ፡፡ የተገለጸው መልእክት "እግዚአብሔር ሥልጣንን፣ ሹመትን ለመረጠው ይሰጣል"[8] ከሚለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት አስተምሕሮ ጋር ይጣጣማል፡፡ ምዕመናኑ የሚቀበሉትና በዘመኑ የነበረውን እውነታ የገለጹ ሰዎች የሚጋሩት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ለዐፄ ቴዎድሮስ ክርቶስ ኃይሉን እንደ ሰጣቸው ተክለ ኢየሱስ (2008፤ 214) "ከአጼ ኢዮአስ[9] ወዲህ ሐበሻ ተዋርዶ የነበረውን በጉልበትና በስም አኰራት፡፡ ከፍ ከፍ አደረጋት፡፡ ክርስቶስም ውርደትዋን በቃ ሲል ኃይሉን ለአጼ ቴዎድሮስ ሰጠ፡፡ በቀኝ በግራ የነበረውን ሁሉ መሳፍንት እየቀጠቀጠ አስታጠቀው፡፡" በማለት ገልጸውታል፡፡

አዝማሪ አብተው ደጅ አዝማች ካሣ ኢትዮጵያን እንዲመሩ፣ እንዲያስተዳድሩ ከአምላክ አደራ ተሰጥተዋል ለማለት ያስቻለው አንድም፣ በተደጋጋሚ ያገኟቸውን ወታደራዊ ድሎች በመገንዘብ ነው፡፡ አንድም፣ ቀድሞ መለኩሴ የተናገረውን ትንቢት በመስማቱና በማወቁ ይኾናል፡ ፡ ደጅ አዝማች ካሣ ኢትዮጵያን እንደሚመሩ ለአባታቸው የተነገራቸው ከመወለዳቸው በፊት እንደ ነበር Fusella (1958፡ 69) "ወልደ ጊዮርጊስ ኀይሉ ወይዘሮ አትጠገብን በጎንደር አገቡዋቸውና አጤ ቴዎድሮስን አረገዙ ገና ተረግዘው ሳሉ አንድ መለኩሴ ለወልደ ጊዮርጊስ እንዲህ ብሎ ነገራቸው፡፡ ይህ ተረግዞ ያለ ወንድ ልጅ ነው ታላቅ ንጉሥ ነው የሚሆን ነገር ግን ብዙ ሰውና ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ይጠፋል [ያጠፋል] ብሎ ነግሮአቸው ነበር ይላሉ፡፡ ከዚህ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ በጎንደር ተወለዱ፡፡" በማለት ከገለጹት መረዳት ይቻላል፡፡ መለኩሴ ስለ እሳቸው የተነበየውን ደጅ አዝማች ካሣ ራሳቸው መስማታቸውን (Fusella, 1958፡ 70) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

ልጅ ካሳ ከወንድማቸው ከደጃች ክንፉ ጋር ተቀምጠው ሳሉ ደጃች ክንፉ ይወድዋቸው ነበር፡፡ በኋላ ፩ መለኩሴ መጥቶ ለደጃች ክንፉ እንዲህ አላቸው ልጅ ካሳ ሊገዛ ነው የርሰዎ ልጆች ግን አይረቡም ብሎ ነገራቸው፡፡ ከዝያ ወድያ ደጃች ክንፉ እንደ ቅናት አርገው ልጅ ካሳን ጠሉዋቸው በመልካም ዓይን ትተው በክፉ ዓይን አይዋቸው የደጃች ክንፉ ልጆች ልጅ መኰንን እና ክንፉ ጋረድ ይባሉ ነበርና ግዛት ለልጆቻቸው ስለ ፈለጉ ነው፡፡

---

[8]መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ከምዕራፍ ፱ እስከ ፲፡፡

[9]በስመ መንግሥታቸው አድያም ሰገድ በመባል የሚታወቁትን የኢዮአስ ቀዳማዊን ዘመነ መንግሥት ይጠቅሳል፡፡ የእሳቸው ሥልጣነ መንግሥትም ከ፲፯፻፵፯ እስከ ፲፯፻፷፫ ዓ. ም. ነበር፡፡ ከእሳቸው በኋላ የመጡት ነገሥታት በስም እንጂ ሃይል ኖሯቸው የሚያዙ የሚናዙ አልነበሩም፡፡ ከኢዮአስ በኋላ የነገሡት የነገሥታት ሥልጣን በተለያዩ ቦታዎች በነበሩ መሳፍንት ወሳኝነት ሥር ነበር፡፡ የነገሥታቱ ስም ዝርዝርና የነገሡበት ጊዜ በተክለ ኢየሱስ (2008፤ 92) ሥርግው ገላው በሰጡት ሐተታ ተዘግቧል፡፡ ከኢዮአስ በኋላ የነገሡት የነገሥታት ሥልጣል በተለያዩ ቦታዎች በነበሩ መሳፍንት ወሳኝነት ሥር ነበር፡፡

ልጅ ካሳ ግን ይህ ነገር ሁሉ አያውቁም ወንድሜ ይወዱኛል ይሉ ነበር፡፡ አንድ ቀን ደጅያች ክንፉ አዳራሽ በተገኙ ቀን ልጅ ካሳ ሥጋ ሊያስቆርጡ እንደ የቤት አሽከር ሁነው ከደጃች ክንፉ ቀረቡ ደጃች ክንፉ ቆረጡ እና ይበሉ ጀመሩ፡፡ ዘፈን ጨወታ ሲጀመር ግን ልጅ ካሳ የሚጫወቱትን ስለ ማየት ፊታቸው ዘወር ብሎ ሳለ፡፡ ደጃች ክንፉ የቆረጡት[ን] ጨርሰው መልሰው ለመቁረጥ አቅርብ ቢልዋቸው ሳይሰሙ ቀርተው ዘገዩ በኋላ ደጃች ክንፉ ሆዳቸውን በካራ ሊቀዱዋቸው ሲቃጡ ልጅ ካሳ ወደ ደጅ ሽሹ ሌላ አስቆራጭ አሽከር መጥቶ ቆመ፡፡

ልጅ ካሳም ከደጅ ሰላም መተላለፊያ ሒደው ከዝያው ተኙ ከዝያ ወድያ ከደጀ ሰላም ተተከናንበው [ተከናንበው] ተኝተው ሳሉ መኳንንቶች ሲወጡ፡፡ እንዲህ ብለው ተናገሩ ደጃች ክንፉ ዛሬ የወንድማቸውን ልጅ[10] በካራ ሆዱን ቀደውት ነበሩ ተባባሉ አንዱ ይገዛል እያልዋቸው ቀንተው ነው አለ፡፡ አንዱ ደግሞ እውነት ይገዛ ይሆን አለ፡፡ ሌሎችም ርግጥ ነው ከብዙ ሰምተናል አሉ ይህነን ሲናገሩ ልጅ ካሳ የተኙ መስለው ሰሙ እና ሌሊቱን ከድተው አደሩ፡፡

ልጅ ካሣ ወንድማቸውን ከድተው ወደ ደጅ አዝማች ጎሹ ይኺዱ እንጂ ወደፊት ኢትዮጵያን ለመምራት ፈቃደ እግዚአብሔር ከእሳቸው ጋር መኾኑን በልባቸው ሰንቀዋል፡፡ በደጅ አዝማች ጎሹ ቤት በቆዩባቸው ጥቂት ዓመታት የተመሰገኑበትን የጀግንነት ተግባር ለመፈጸም ከተፈጥሯዊ ባሕርያቸው በተጨማሪ የነገ ሕልማቸው ብርታትንና ድፈረትን እንደሰጣቸው ይታመናል፡፡ ከደጅ አዝማች ጎሹ ወደ ጎንደር ተመልሰው ከእቴጌ መነን የመቅረባቸውና የልጅ ልጃቸውን ተዋበችን እንዲያገቡ መጠየቃቸው[11] በራሳቸው መተማመናቸውንና የነገውን ማንነታቸውን ትራስ ያደረገ ነበር፡፡

“የንቀት ድርጊት ተፈጽሞብኛል” ብለውና አኩርፈው ከጎንደር ቤተ መንግሥት ወደ ቋራ ሲወርዱ በደምብያ ለነበረው የእቴጌ መነን ወታደር “የወደድኸኝ ተከተለኝ የጠላኸኝ አገሬን ልቀቅ”፣ ይደግፈኛል ላሉት ሕዝብ ደግሞ፣ “በክርስቶስ ኃይል መጥቻልሃለኹ” በማለት ዐዋጅ ያስነገሩት፣ በፊታቸው የተገኘውን የእቴጌ መነን ወታደር ነፍጡንና መሳሪያውን ያስገፈፉት[12] ስለ እሳቸው ቀድሞ የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም በማሰባቸው ነው፡፡ ይኽንንም በሉዊጂ ፉዜላ በታተመው የዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል በአንደበታቸው መናገራቸውን ቀጥለን እናነባለን፡፡

ልጅ ካሣ በፈጸሙት ድርጊት የተበሳጩት እቴጌ መነን ብዙ ሠራዊት ወደ ቋራ አዘመቱባቸው፡፡ ልጅ ካሣን ለመውጋት የዘመተው ጦር ቋራ መድረሱን እንዳወቁ ልጅ ካሣ “... ወደ ዱር ገብተው ጸሎት ሲያደርጉ በጉልበታቸው ተምበርክከው ከዛፉ ወርዳ ርግብ ተቀመጠችባቸው ይባላል እርሳቸው ተነስተው ምስጋና ይሁን ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ብለው ፊታቸውን ፫ ጊዜ አማትበው ወደ ምድር ፫ ጊዜ ሰገዱ እና፡፡ እንግዲህ ንግርቴ ደረሰ

---

[10]ደጅ አዝማች ክንፉ ልጅ ኀይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ወይዘሮ አትጠገብን ከማግባታቸው በፊት ከሌላ ሴት የሚወልዷቸው ናቸው፡፡ ደጃች ክንፉ ለደጅ አዝማች ካሣ የአባታቸው ልጅ ታላቅ ወንድማቸው ናቸው፡፡

[11]ልጅ ካሣ በሽፍትነት የሚኖሩትን የአቶ እንገዳ ወርቅን ልጅ አግብተው ነበር፡፡ ለእቴጌ መነን ስጦታ በላኩላቸው ጊዜ “ያቶ እንግዳ ወርቅን ልጅ ትተህ፣ የኔን ልጅ አግባ” ብለው ላኩባቸው (ሊትማን፣ 1902፤ 12)፡፡

[12]Fusella, (1958፡ 74)፡፡

ብለው ወደ ሰልፋቸው ተመለሱ" (Fusella, 1958፡ 75)፡፡ ስለኾነም፣ በሙገሳ ግጥሙ ደጅ አዝማች ካሣ ኢትዮጵያን እንዲመሩ ከአምላክ የተላኩ መኾናቸው የተነገረውም በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ይወራ የነበረውንና በደጅ አዝማች ካሣ ይታመንበት የነበረውን ትንቢት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ደጅ አዝማች ካሣ በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ሥልጣን የመጡበት ወቅት፣ ኢትዮጵያ መሪ ባስፈለጋት ጊዜ መኾኑን አዝማሪ አብተው በሚከተለው ግጥሙ ይገልጻል፡፡[13]

ብዙ ጊዜ ኾናት ደህና ባል ካጣች፣
አኹን ግን በታጠቅ[14] ይኸው ታፈረች፡፡

አዝማሪ አብተው በተጠቀሰው ቃለ ግጥሙ ለዋጭ ዘይቤን በመጠቀም ኢትዮጵያን ሴት እሷን የሚገዛውን፣ የሚመራውንና የሚያስተዳድረውን ደግሞ ባል[15] አድርጎ ገልጿል፡፡ ኢትዮጵያ በሴትነቷ የሚመራት፣ የሚያስተዳድራትና ጌታዋ የሚኾናት ባል ሳይኖራት ብዙ ጊዜ አሳለፈች፡፡ ብዙ ጊዜ የሚለውም የጎንደር ዘመነ መንግሥት ከተዳከመበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ዓመታት ይሸፍናል፡፡ ይኸም የኢዮአስ ሥልጣነ መንግሥት ካበቃበት ከ፲፯፻፵፯ ዓ. ም. ዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ነገሡበት ፲፰፻፵፯ ዓ. ም. ያለውን ከ፻፪ ዓመት በላይ ማለት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ባል ሳይኖራት ያሳለፈችው ጊዜም በዘመነ መሳፍንት የተለያዩ ክፍላተ ሀገርን ይገዙ በነበሩ መሳፍንት የተመራችበትን ጊዜ ያጠቃልላል፡፡ አኹን ግን፣ ታጠቅ የሚባሉ ኢትዮጵያን እንዲመሩ ከአምላክ አደራ የተሰጣቸው ንጉሥ፣ መሪ፣ አስተዳዳሪ አገኘታ ተከበረች፤ በማለት አዝማሪ አብተው ይገልጻል፡፡

ቋረኛው ካሣ ከዚኽ በላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በበርካታ ቃለ ግጥሞች ተሞግሰዋል፡፡ ከዚኽ በታች ከ፩ እስከ ፯ የተጠቀሱት የሚከተሉት ግጥሞች ቋረኛው ካሣ ከተሞገሱባቸው

[13]ይኽ ቃለ ግጥም በአዝማሪ አብተው ከተደረደሩትና በገሪማ (፲፱፻፷፪፤ ፶፯) ከተመዘገቡት በርካታ የሙገሳ ቃለ ግጥሞች መካከል አንዱ ነው፡፡

[14]ታጠቅ የሚለውን ቃል ቀድመው የተናገሩት ወይዘሮ ታዋበች የደጅ አዝማች ካሣ ሚስት ናቸው፡፡ ታሪኩም ደጅ አዝማች ካሣ የኮሶ መድኃኒት ጠጥተው "ምሳዬን" ብለው ለእቴጌ መነን ላኩ፡፡ ወይዘሮ መነንም ወርች ሥጋ ላኩላቸው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ የተላከላቸውን የወርች ሥጋ "ለክብሬ አይመጥንም" በማለት አዘኑ፡፡ ማዘናቸውን የተረዱት ተዋበች፣ በባላቸው ላይ በደረሰው ውርድት ተቆርቁረው "ሀገር የለህም? ታጠቅ እንሂድ ይልቅ" አሏቸው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣም ታጥቀው ሚስታቸውን ይዘው አገራቸው ቋራ ገብተው ሸፈቱ፡፡ ብዙ ሎሌ ገባላቸው፡፡ አባ ታጠቅ ተባሉ (ተክለ ኢየሱስ፣ 2008፤ 204-205)፡፡ ታጠቅ የሚለው ቃል ደጅ አዝማች ካሣ ዐፄ ቴዎድሮስ ተብለው ከነገሡ በኋላ የፈረስ ስማቸው ኾነ፡፡

[15] ሚስቶች ሆይ፣ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና፡፡ ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ፡፡ ባሎች ሆይ፣ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ ኤፌ ፭ ፣ ፳፪ - ፳፫)፡፡

የፉከራ[16] ግጥሞች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የሙገሳ ግጥሞቹም በገሪማ (፲፱፻፺፮፤ ፶፺) የተመዘገቡ ናቸው፡፡

፩) ቋረኛው ካሣ የኀይሉ ልጅ፣
አምላክ ከጠቡ አያድርስ አንጅ፡፡

፪) ሲጥል ሲሰረጅ ትግል ሲገጥም፣
ራስ ደጅ አዝማች ንጉሥ አይመርጥም፡፡

፫) ካሣ ካሣ ቋረኛው፣
የደን አንበሳ ሰርክ በየጎራው፡፡

፬) የሜዳ ነብር የጫካ አንበሳ፣
የኢትዮጵያ ባል ቋረኛው ካሣ፡፡

፭) የኢትዮጵያ ባል የመሸሻ አባት፣
የሚያቃጥለው ግንባሩ እንደ እሳት፡፡

፮) የዓለሜ ጌታ ደግሞም የገልሞ፣
የደከመ አገር አዳኝ አስታሞ፡፡

ቋረኛው ካሣ በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው ቃለ ግጥም የተሞገሱት፣ አንድም፣ በባሕርያቸውና በአሸናፊነት ድርጊታቸው ነው፡፡ አንድም፣ በአባታቸው በኀይሉ ማንነትና ታሪክ የታወቁ በመኾኑ ነው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣን ለማሞገስ ያበቃቸው የኀይሉ የጀግንነት ተግባር ወይም ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ምን እንደ ነበር በግጥሙ አልተገለጸም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ደጅ አዝማች ካሣ ጀግንነታቸውን ከአባታቸው የወረሱት ስለ መኾኑ "ቋረኛው ካሣ የኃይሉ ልጅ" በሚለው ስንኝ ተነግሯል፡፡

ቋረኛው ካሣ በኢትዮጵያ አስተዳዳሪነታቸው፣ በልጃቸው በመሸሻ፣ በአሽከሮቻቸው ባለሜና በገልሞ መኩራት እንደሚገባቸው በተራ ቀጥር ፬ በኹለተኛው ስንኝ፣ እንዲሁም በተራ ቁጥር ፭ እና ፮ የመጀመሪያዎቹ ስንኞች ተገልጿል፡፡ በእርግጥ፣ መሸሻ በአባታቸው፣ ዓለሜና ገልሞም በጌታቸው እንደሚኰሩ ከቃለ ግጥሞቹ መረዳት ይቻላል፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ የሚኰራበት አባት፣ ልጅና አሽከሮች ያላቸው መኾኑ አስሞግሷቸዋል፡፡

በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው በአዝማሪ በተዜመው ግጥም በመጀመሪያው ስንኝ ቋረኛው ካሣ በአባታቸው በኩል ዘራቸው ከቋራ አካባቢ እንደሚቆጠርና አባታቸውም ኃይሉ እንደሚባሉ ይነግራል፡፡ የአባታቸው ስም በግጥሙ መጠራቱ የሚኰራበት ዘር እንዳላቸው ይጠቁማል፡፡

[16]ፉከራ አንድ ሰው ስለ ፈጽመው ወይም ስለ ሚፈጽመው ጀብዱ እያነሣ ጀግንነትንና ወኔን በሚቀሰቅስ ድንፋታ መናገር ነው፡፡ ፉከራውም ድምፅን ከፍ በማድረግ በፍጥነትና በተቆጣ ስሜት በደስታና በኀዘን አጋጣሚዎች የሚቀርብ የሥነ ቃል ዓይነት ነው፡፡

የማይኰራበት አባት በአደባባይ መሞገሱ ቀርቶ በሹክሹክታ ለማንሣትም አይፈለግም፡፡ የኃይሉ ስም በሙገሳ ግጥሙ በመጠራቱ ማንነታቸውን እንድንጠይቅ እንገፋፋለን፡፡ አባታቸው ወልደ ጊዮርጊስ ኃይሉ (አጠራሩ በጎንደር የተለመደውን አባትን በማስቀደም መጥራትን የተከተለ ነው) የደጅ አዝማች ክንፉ አባት ናቸው፡፡[17] በዚኽ የዝምድና ስሌት ዐፄ ቴዎድሮስ በአባታቸው በኩል ከመሳፍንት ወገን ናቸው፡፡ ይኽም በዘመኑ የሞኮራበትና የሚሞገሱበት ነበር፡፡

“አምላክ ከጠቡ አያድረስ እንጅ” የሚለው ስንኝ ደጅ አዝማች ካሣ ሲጣሉ ምሕረትና ይቅርታ የማያደርጉ ጨካኝ እንደ ነበሩ ያስረዳል፡፡ እንዲኽ ዓይነት ባሕርያቸው ከሚገለጥበት ክፉ አጋጣሚ እግዚአብሔር እንዲጠብቅ አዝማሪው ተመኝቷል፡፡ በሉዊጂ ፉዜላ (Fusella, 1959, 64-65) የተመዘገበው የሚከተለው ግጥምም ዐፄ ቴዎድሮስ ቁጣቸው አስፈሪ፣ ቅጣታቸው ከባድ መኾኑን ያስረዳል፡፡

ፍቅሩን ጨርሶ ጠቡን ሲያመጣው፣
ሞላጫ ገደል ዝንጀሮ አይወጣው፡፡

ግጥሙ፣ የእንግሊዙን ቆንስል “ኬምሮንን” ንጉሡ ተቀብለው ምግብና መጠጥ በሚጋብዙበት አጋጣሚ የተገጠመ ነው፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ “አስተርጓሚ ቀርቦ ማለፍያ ማለፍያውን” ከእንግዳቸው ጋር ይጫወታሉ፡፡ አዝማሪውንም አጤ ቴዎድሮስ “አጫውተን” እያሉ ይስቁለታል፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ጨዋታ ሲጫወቱ ደስ ያሰኛሉ ሲቆጡ ቀን አያድርስ ይለዋል እንጅ፡፡ እሱም ሲያስቃቸው ትንሽ ነገር ያድጠዋል፡፡ በድርጊቱም ዐፄ ቴዎድሮስ በሚያስፈራ ግርማቸው ይቆጡታል፡፡ አዝማሪው ቶሎ ብሎ የተጠቀሰውን ግጥም በመግጠም ይቅርታ ይጠይቃል፡፡ ይቅርታም ይደረግለታል፡፡

በግጥሙ የዐፄ ቴዎድሮስ አስፈሪ ቁጣ የተነጻጻረው ዝንጀሮ ሊወጣው ከማይችለው ገደል ጋር ነው፡፡ የገደሉ አስቸጋሪነትና አስፈሪነት ኑሮውን በገደል ያደረገው ዝንጀሮም እንደማይወጣው መገለጹ የዐፄ ቴዎድሮስ ጠብ ከባድና ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትል መኾኑን ያስረዳል፡፡

---

[17]ደጅ አዝማች ክንፉ ቋራን፣ ደምቢያን፣ ጭልጋን እስከ መተማ ይገዙ ነበር፡፡ ከቱርክ ጋርም ይዋጉና ድልም ያደርጉ ስለ ነበር፣ እንዲኽም እየተባለ ይዘፈናል፡፡

የክንፉ ጎራዴ ጥቁር የነበረ፣
እየቀላ ኼደ ቱርክ እየመሰለ፡፡

አሽከራቸው ኹሉ ገዳይ፣ ቤታቸው የጥጋብና የዘፈን ቤት ነበር ይባላል፡፡

ኹሉም ባለ አጫዋች አዶ ነበር፡፡ አዳራሽ በተገኙ ቀን አሳላፊው አዶ አጫዋች አስሮ ብርሌ ከሰጠ ወዲያ አሸሸ ያለ እንደሆነ ዘፈን ይደባለቃል (Fusella, 1958፤ 69)፡፡ ኃይሉ እንዲኽ ዓይነት ክብረት በነበረው ልጃቸው የሚከበሩ፤ የሚኮሩ ተደርጎ ቀርቧል፡፡

የተጠቀሰው ባሕርይ ያላቸው ቋረኛው ካሣ በጠላትነት የፈረጇቸውን ሰዎች ገጥመው እንደሚያሸንፉ በተራ ቀጥር ፪ የተጠቀሱት ስንኞች ያስረዳሉ፡፡ በስንኞቹ እንደ ተገለጸው፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ካሣ የደጅ አዝማችነት፣ የራስነትና የንጉሥነት ማዕረግ የነበራቸውን ጠላቶቻቸውን አሸንፈዋል፡፡ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው፣ ጉራምባ ላይ ደጅ አዝማች ጎሹን፣ አይሻል ላይ ራስ ዓሊን አሸንፈዋል፡፡ በቃለ ግጥሙ ቋረኛው ካሣ ንጉሥ ማሸነፋቸው የተገለጸው ወደ ሸዋ ዘምተው በንጉሥ ኀይለ መለኰት ላይ ጥቃት ለመፈጸም ያደረጉትን እንቅስቃሴ ያስታውሳል፡፡ በታሪክ እንደሚታወቀው ንጉሥ ኀይለ መለኰት በጤና መታወክ ምክንያት ሲሞቱ ቋረኛው ካሣ ደግሞ፣ የንጉሡን ደጋፊዎች አሸንፈው ዐልጋ ወራሻቸውን ምኒልክን ማርከው ወስደዋል፡፡

ቋረኛው ካሣ በጦርነት አሸናፊነታቸው የተገለጸው፣ ባላንጣን ትግል ገጥሞ በመጣል መርታት የሚለውን ባህል መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ባላጋራውን ወይም ባላንጣውን ትግል ገጥሞ ለመጣል የፈለገ ሰው ከደረቱ አስጠግቶ በመያዝ አዘናግቶ በአንድ እግሩ የተጋጣሚውን ሰው እግር በመሰርጀት (በመጥለፍ)፣ ሚዛኑን ጠብቆ መሬት ረግጦ እንዳይቆም ያደርገዋል፡፡ የሰውነት ሚዛኑን ጠብቆ ለመቆም ያልቻለውን ተጋጣሚ ኃይሉን ተጠቅሞ በመገፍተር መሬት ላይ ይጥለዋል፡፡ ቋረኛው ካሣም የተለያዩ የጦር ሥልቶችን በመጠቀም ጠላቶቻቸው ራሳቸውን እንዳይከላከሉ በማድረግ ድል አድርገዋቸዋል፡፡

በተራ ቁጥር ፫ እና ፬ በተጠቀሱት ስንኞች የቋረኛው ካሣ ጀግንነትና ቁጡነት የተገለጸው በለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ በጠላቶቻቸው ላይ በሚያሳዩት ድፍረትና ጀግንነት "የደን አንበሳ" ተብለዋል፡፡ ለባላንጋራቸው በጣም ቁጡ ባሕርይ እንዳላቸው ደግሞ "የሜዳ ነብር" በሚል ተገልጸዋል፡፡ ኀበዝ፣ ቀልጣፋ፣ ንቁና ጮሌ መኾናቸው የተገለጸው "እንደ እሳት" በሚል ተነጻጻሪ ዘይቤ ነው፡፡ አንበሳ ከድመት ወገን ካሉት እንስሳት ኹሉ የሚበልጥ፣ በደን ውስጥ የሚኖር ኃይለኛና አስፈሪ የዱር እንስሳ ነው፡፡ እንደዚሁም፣ ነብር በጢሻ፣ በቋጥኝና በዋሻ ውስጥ የሚኖር ኃይለኛና ቁጡ አውሬ ነው፡፡ እነዚኽ የዱር አውሬዎች በኃይለኛነታቸውና በቀልጣፋነታቸው እንዲሁም በአሸናፊነታቸው እንደሚታወቁት ኹሉ ቋረኛው ካሣም በጠላቶቻቸው ዘንድ ተፈሪና አሸናፊ ጀግና ነበሩ፡፡ ጀግንነታቸውንም ጠላቶቻቸውን በመውጋትና በማሸነፍ አስመስክረዋል፡፡ ጀግንነት፣ ቁጡነትና ቀልጣፋነት የባሕርይ መገለጫዎቻቸው የኾኑት ቋረኛው ካሣ፣ የኢትዮጵያ መሪ፣ አስተዳዳሪና ገዢ መኾናቸው በተራ ቁጥር ፬ ኹለተኛ ስንኝና በተራ ቁጥር ፭ የመጀመሪያ ስንኝ ባል በሚል ቃል ተገልጿል፡፡ በእሳቸው ተሐድሶ ያገኘችውና የሚመሯት ኢትዮጵያ፣ የኰሰመነችና የጠፋች እንደ ነበረች "የደከመ አገር አዳኝ አስታሞ፡፡" በማለት ተገልጿል፡፡ ኢትዮጵያ ከህመሟ እንድታገግምና እንድትፈወስ ለማድረግም ያዳከሟትን መሳፍንት በመውጋት ለማሸነፍ ብዙ ደክመዋል፡፡ በስንኙ የተገለጸው ታሪካዊ እውነታ ይኸው ነው፡፡

ድል የቀናቸው ደጅ አዝማች ካሣ ራስ ዓሊን ድል ከመቱ በኋላ ከጎጃም የራስ ዓሊ መቀመጫ ወደ ነበረችው ደብረ ታቦር ከተማ ገሥገሡ፡፡ ከተማዋን ከተቆጣጠሩ በኋላ በደብረ ታቦርና አካባቢው ለሚገኘው ሕዝብ፣ "…ጉልት አለኝ የምትል የሴት ወይዘሮ የወንድ መኰንን በምን ተነቀልኩ እንዳትል ግባ የአባትህን ሰጥቻሃለሁ፡፡ ከራስ ዓሊ ጋር የሸሸህ ወታደር ምሕረት አድርጌልሀለሁ ግባ፡፡" የሚል ዐዋጅ አስነገረው፤ በደብረ ታቦር ከተማ ከረሙ፡፡ "አዋጁን

የሰማውና ትእዛዙን የተቀበለው የቤጌምድር፤ የዋድላና የደላንታ ሕዝብ እንዲሁም ከራስ ዓሊ ጋር ሸሽቶ የነበረው ሠራዊት ገባላቸው፡፡” (ገሪማ፣ ፲፱፻፺፮፤ ፷፩)

ደጅ አዝማች ካሣ ደብረ ታቦር እያሉ ደጅ አዝማች ውቤ እንዲገቡላቸው ጠየቁ፡፡ ፈቃደኛ ባለ መኾናቸው ደጅ አዝማች ውቤን ለመውጋት “ስሜን ስሜን እነግርሃለሁ” በማለት በ፲፰፻፵፯ ዓ. ም. ወደ ስሜን ዘመቱ፡፡ ደጅ አዝማች ውቤንም ድል አደርጉ፡፡ በደጅ አዝማች ውቤ ድል መኾን የሕዝቡ ስሜት ምን እንደ ነበር በደስታ (፲፱፻፹፪፤ ፪፻፵፫) የተጠቀሰው የሚከተለው የአዝማሪ ግጥም ያስረዳል፡፡

ሰብኣ በጌምድር ወልቃይት ጠገዴ፣ ሰሜን አርማጭኾ፣[18]
ለጎይለኛው ንጉሥ ተገዛን እንኾ፡፡

ስሙ ባልተገለጸ አዝማሪ የተገጠመው ይኽ ቃለ ግጥም፣ የንጉሡን አሸናፊነትና ከየአካባቢው ገዥዎች ጋር አብሮ አልገዛም ያለውን ሕዝብ ተሸናፊነት ይገልጻል፡፡ አዝማሪው በግጥሙ የጠራቸው በቅርብ የሚያውቃቸውን የደጅ አዝማች ውቤ ከፋላተ ግዛት ነው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ወደ ሰሜን ከመዝመታቸው በፊት ተደጋጋሚ ድሎችን አገኝተዋል፡፡ ወደ ሰሜን በመዝመትም በግጥሙ የተገለጹትን የደጅ አዝማች ውቤን ግዛቶች ወልቃይትን፣ ጠገዴን፣ ሰሜንንና አርማጭኾን የግዛታቸው አካል አደረጉ፡፡ በደጅ አዝማች ውቤ ታስረው የነበሩትን “ሰብአ ጋዲስ ካሣን”[19] ፈትተው የትግራይ ምስለኔነት ሾሙዋቸው (ሊትማን፣ ፲፱፻፪፤ ፴፫)፡፡ አዝማሪው እንደገለጸው ደጅ አዝማች ካሣ በአሸናፊነታቸው በራስ ዓሊ ምስለኔ ሥር የነበረውን ሰብአ በጌምድር (ኹሉንም የበጌምድር ሕዝብ) በማሸነፍ ጠቀለሉ፡፡ አዝማሪው ደጅ አዝማች ካሣን ያሞገሳቸው በሙገሳ ግጥሙ የተጠቀሱትን ቦታዎች ይገዙ የነበሩትን ደጅ አዝማች ውቤን ወግተው በማሸነፋቸው ነው፡፡

ደጅ አዝማች ካሣ ሰሜን ላይ ደጅ አዝማች ውቤን ድል አድርገው የካቲት ፲፩ ቀን ፲፰፻፵፯ ዓ. ም. በአቡነ ሰላማ ቅብዐ መንግሥት ተቀብተው በደረስጌ ማርያም ስመ መንግሥታቸውን “ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ” አሰኝተው ነገሡ፡፡

ደጅ አዝማች ካሣ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተብለው ከነገሡ በኋላም በተለያዩ ቦታዎች የነበሩ ተቀናቃኞቻቸው ማመፅ በመቀጠላቸው፣ ረጅም መንገድ እየተጓዙ ማጥቃታቸውን ቀጠሉ፡

[18]የደጅ አዝማች ውቤ ግዛቶች በገጣሚው የተጠቀሱት ቦታዎች ብቻ አልነበሩም፡፡ በትግራይ የነበሩ የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውን ወግተውና አሸንፈው መላ ትግራይን ይገዙ እንደ ነበር የተለያዩ የታሪክ ሰነዶች ያስረዳሉ (ኢኖ ልትማን፣ ፲፱፻፪)፡፡ በVidailhet (1904፤ 5) እንደ ተገለጸው ደጅ አዝማች ውቤ ቧሂት ላይ ደጅ አዝማች ካሣን የትግራይን ፹፬ ነጋሪት ጦር ይዘው መግጠማቸው ትግራይ ግዛታቸው ስለ ነበር ነው፡፡ ትግራይ የሚለው ግዛት ቀይ ባሕር ድረስ የነበረውን ቦታ ያጠቃልላል፡፡ ደጅ አዝማች ውቤም ከጎንደር አንስቶ እስከ ቀይ ባሕር ጠረፍ ድረስ ያለውን ግዛት ይገዙ ነበር (ገነት፣ 2009፤ 371)፡፡

[19]በታሪክ እንደሚታወቀው ሰባጋዲስ አባት ካሣ ልጅ ናቸው፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ የትግራይ ገዢ አድርገው የሾሙት ካሣ ሰባጋዲስን ነው፡፡ ሰባጋዲስ የሞቱት ደጅ አዝማች ውቤ በሥልጣናቸው እያሉ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ትግራይ ከመዝመታቸው በፊት ነው፡፡ ነገር ግን፣ የዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ጸሐፊ አባትን ልጅ፣ ልጅን ደግሞ አባት አድርጎ የመጥራትን የጎንደር ባህል ተጠቅሞ ስለጻፈው ሰባጋዲስ ቀድመው ተጠርተዋል፡፡

፡ ድል በማድረጋቸውም በአዝማሪ መሞገሳቸውን በታሪክ ሰነዶች ከተመዘገቡት ቃለ ግጥሞች እንገነዘባለን፡፡ የተሞገሱባቸውን ቃለ ግጥሞች በተራ ቁጥር ፫. ፪ በተገለጸው ንዑስ ርእስ ሥር ቀጥለን እንመከታለን፡፡

### ፬. ፪. ከንግሡ በኋላ ተቀናቃኞቻቸውን በማሸነፋቸው መሞገሳቸው

ደጅ አዝማች ካሣ ዳግማዊ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ከነገሡ በኋላ ወደ ወሎና ወደ ሸዋ ዘመቱ፡፡ የተቀናቀኗቸውን ኹሉ ወግተው ድል አደረጉ፡፡ ወሎ ላይ በተለይ ወረሂመኖ ላይ የገጠማቸውን ተቃውሞ በጦርነት ድል በማድረግ ጥፋተኛ ያሏቸውን ቀጥተዋል፡፡ ድል በማድረጋቸውና ተቀናቃኞቻቸውን በመቅጣታቸው አዝማሪ ያሞገሰበትን ግጥም አላገኘኹም፡፡

ወደ ሸዋ ዘምተው ድል በማድረጋቸው መሞገሳቸውን ከሚከተለው ግጥም እንረዳለን፡፡

ሺ ዳለች ሺ ቦራ ነበር የሸዋ ፈረስ፣
አንድ ጥርኝ ኾነ ቢዘልቅ ቴዎድሮስ፡፡

በሙገሳ ግጥሙ ሰም የተላለፈው መልእክት ዳለች (ቡላ ፀጉር ያለው ፈረስ) እና ቦራ (ግንባሩ ላይ ነጭ ፀጉር ያለው ፈረስ) መልክ ያለው የሸዋ ፈረስ ቁጥሩ ብዙ ነው፤ ኹለት ሺ ይኾናል፡፡ ነገር ግን፣ ብዛት ያለው የሸዋ ፈረስ ወደ አለበት ቴዎድሮስ ብቅ ሲል ወደ ጥርኝነት (ግራጫ ወይም ነጭና ጥቁር ፀጉር ወደ አለው ፈረስ) ተለወጠ፤ ብዙ የነበረው የሸዋ ፈረስ በቴዎድሮስ ፊት አንድ ብቻ ኾነ የሚል ነው፡፡

በወርቁ የተላለፈው የግጥሙ ዋና መልእክት ዐፄ ቴዎድሮስ የተሞገሱበት የሸዋ መሳፍንትና መኳንንት በዳለች ፈረስ የሚዋጋ አንድ ሺ ጦር፣ እንደዚሁም በቦራ ፈረስ የሚዋጋ አንድ ሺ ጦር በጠቅላላው ኹለት ሺ ፈረሰኛ ጦር ለውጊያ ተሰልፏል፡፡ ይኽን ያኽል ብዛት ያለው የሸዋ ፈረሰኛ ጦር ቴዎድሮስ በአንድ ጥርኝ ፈረሳቸው ሊወጓቸው ሲመጡ፣ በፍርሃት ርደው እፍኝ የማይሞሉ ትንሽ (ጥርኝ) ኾኑ፡፡ ክፍተኛ ቁጥር የነበረውና ያስፈራ የነበረው የሸዋ ጦር ከተገመተው በታች ተዋጋ፤ በቀላሉ በቴዎድሮስ ጦር ድል ተመታ ማለት ነው፡፡ ይኽም፣ የቴዎድሮስን ጀግንነት ከፍ ያደርጋል፤ የተቀናቃኞቻቸውን የሸዋ መሳፍንትና መኳንንት ያኰስሳል፤ ዝቅ ያደርጋል፤ ይሰድባል፡፡ በቃለ ግጥሙም ሙገሳና ኩሰሳ ተነግረውበታል፡፡ ሙገሳው ለዐፄ ቴዎድሮስ፣ ኩሰሳው ደግሞ በሸዋ ለነበሩ ተቀናቃኞቻቸው ነው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ የዘለቁት፣ ሽፍትነት ከጀመሩበት ከቋራ ተነሥተው በጎጃም፣ በበጌምድርና በሰሜን የነበሩ ተቀናቃኞቻቸውን ድል አድርገው ወሎን አስገብረው ነው፡፡ ሰፊ ቦታን ባካለለው ዘመቻ ድል ያገኙት በጀግንነታቸው በወንድነታቸው በመኾኑ አዝማሪ አብተው ማሞገሱን ገሪማ (፲፱፻፺፯፤ ፻፫) እንደሚከተለው ጠቅሰዋል፡፡

ከቋራ እስከ ወሎ እስከ ሸዋ ድረስ፣

በወንድ ወንድ አለበት ኧረ ተው ተመለስ፡፡

በግጥሙ እንደ ተገለጸው፣ ዐፄ ቴዎድሮስ በአባታቸው የትውልድ ቦታ በቋራ ሸፍተው፣ በርካታ ተከታዮችን አፍርተው ተቀናቃኞቻቸውን ድል ማድረግ የጀመሩበት ቦታ ቋራና አካባቢው ነው፡፡ ኃይላቸው ደርጅቶ ድል እየቀናቸው ሲኼድ የበላይነታቸውን በኃይል አሳምነው ለማስገበር ከዘመቱባቸው ቦታዎች መካከል በግጥሙ የተጠቀሱት ወሎና ሸዋ እንደ ነበሩ በታሪክ ይታወቃል፡፡ በእነዚኽ ቦታዎች የነበሩት መሳፍንትና መኳንንት በኃይላቸው ተመክተው ባሰለፉት ጦር ኰርተው፣ ጦር ሰብቀው፣ ዘገር ነቅንቀው ዐፄ ቴዎድሮስን ለመውጋት ሙከራ ቢያደርጉም፣ ዐፄ ቴዎድሮስ በጀግንነታቸው ድል አድርገዋቸዋል፡፡ ድል የማድረጋቸው ምሥጢርም፣ ወንድነታቸውና ጀግንነታቸው ከተቀናቃኞቻቸው በመብለጡ ነው፡፡ በሙገሳ ግጥሙ "በወንድ ወንድ አለበት" በማለት የተገለጸው ይኸው የዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነትና ድል አድራጊነት ነው፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ በትውልድ አካባቢያቸው በቋራ፣ እንዲሁም ወደ ወሎና ሸዋ ዘምተው ድል ያደረጉት በቃለ ግጥሙ በስም ያልተገለጹትን፣ በታሪክ ግን በስም የሚታወቁትን ተቀናቃኞቻቸውን ነው፡፡ በተጠቀሱት ቦታዎች የዐፄ ቴዎድሮስ የጀግንነትና የአሸናፊነት ተግባር የታወቀ ስለ ኾነ ለአመፅ መነሣት የሚያስከትለው ጉዳትን መኾኑን "ኧረ ተው ተመለስ" በማለት አዝማሪ አብተው መክሯል፤ አስጠንቅቋል፡፡

በወንድነትና በጀግንነት ዐፄ ቴዎድሮስን የሚወዳደር እንደሌለም አዝማሪ አብተው፡-

ሱሪህ አረንጓዴ ጎራዴህ ባለወርቅ፣
አምሮብኻል ካሣ አንተ ብቻ ታጠቅ፡፡

በማለት ማሞገሱን ገሪማ (፲፱፻፺፮፤ ፻፫) ገልጸዋል፡፡ በግጥሙ የተጠቀሰው ሱሪ ጀግንነትን፣ ወንድነትን፣ አሸናፊነትን ይገልጻል፡፡ የሱሪአቸው ቀለም አረንጓዴ መኾኑ፣ ለምለምነትን፣ ተስፋን፣ ወደፊት ሊገኝ የሚችልን መልካም ነገር ይጠቁማል፡፡ ይኽም የዐፄ ቴዎድሮስ ዓላማ በመሳፍንት የተከፋፈለችውን ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ የመግዛት ግብን ያመሰጥራል፡፡ በአዝማሪው የተደረደረው ግጥም ዓላማቸውን ለማሳካት የዘመኑን የጦር መሣሪያ ጎራዴን በመጠቀም ተቀናቃኞቻቸውን ድል ማድረጋቸውን፣ ማሸነፋቸውን ያስታውሳል፡፡ የጎራዴአቸው መጨበጫ በወርቅ መጌጡ መገለጹም ማኅበራዊ ክብራቸውን፣ ዘውድ ጭነው ለመንገሥ መብቃታቸውን ይዘክራል፡፡ ታጠቅ የሚለው የፈረስ ስማቸውም ወንድነታቸውን፣ ጀግንነታቸውን፣ ንቁና ጠርጣራ ማንነታቸውን፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ደረጃቸው ከፍተኛ መኾኑን ይገልጻል፡፡ በፈረስ ስም መጠራታቸው ከፍተኛ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ደረጃ ያላቸው መኾኑን የቃለ ግጥሙ ባህላዊ ዐውድ ያስረዳል፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ፣ ትኩረታቸውን በጎጃም፣ በወሎና በሸዋ በነበሩት ተቀናቃኞቻቸው ላይ በማድረጋቸው ወደ ትግራይ ፊታቸውን ሣያዞሩ ብዙ ወራት ቆዩ፡፡ በዚኹ ጊዜ በሰሜንና በትግራይ አካባቢ የነበሩ ተቃዋሚዎቻቸው ደጅ አዝማች ንጉሤና ወንድሙ ፊታውራሪ ተሰማ "ዐፄ ቴዎድሮስ ተከዜን አይሻገሩም፡፡ ተከዜን ከተሻገሩና ውሃውን ከጠጡ ይሞታሉ፤

የመንግሥታቸው ፍጻሜም ይኾናል” እያሉ ለአካባቢው ሕዝብ ሟርት ያስነግሩ ነበረ፡፡ በመካከሉ ዐፄ ቴዎድሮስ በሰሜን አድርገው ወደ ትግራይ ተጓዙ፡፡ ተከዜ ሲደርሱ በጎሽ ዋንጫ (ከጎሽ ቀንድ በተሠራ ዋንጫ) ከወራጁ ውኃ አስጠልቀው ከጠጡ በኋላ አዝማሪ አብተውን አስጠርተው በትግራይ የነበሩ ተቃዋሚዎቻቸው፡-

የዓባይነን ውኃ በቅል ይጠጡታል፤
የተከዜን ውኃ ለምን ይፈሩታል፡፡

ሲሉ የገጠሙባቸውን ለመተቸትና ሟርታቸው ከእውነት የራቀ መኾኑን ለማስረዳት የሚከተለውን ግጥም እንደ ሰጡት ገሪማ (፲፱፻፸፰፤ ፻፬) ጠቅሰዋል፡፡

ተከዜን ሲሻገር ይሞታል እያሉ፤
መጽሐፉ ታጠበ ያባይ ጠንቋይ ሁሉ፤
ወርሒን[20] ስንደግመው እንግዲህ ምን ይሉ፡፡

በቃለ ግጥሙ እንደ ተገለጸው በእሳቸው ላይ የተነገረው ሟርት መሠረተ እንደሌለው ለማስረዳት ዐፄ ቴዎድሮስ እንደ ዐባይ ውሃ ኹሉ፣ የተከዜን ውሃ በመሻገር ውሃውን ጠጥተዋል፡፡ ሟርቱን የሚናገረው “ዐዋቂ ነኝ” ባይ የሚጠቀምበት መጽሐፍ ማታለያ መኾኑን በተግባራቸው አረጋግጠዋል፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ከተከዜ አልፈው ወርሒ ወንዝን መሻገራቸው ዐባይ ጠንቋይ የሚጠቀምበት መጽሐፍ ልማድና የተሳሳተ እምነት የሚገለጸበት መኾኑን አጋልጠዋል፡፡ በግጥማቸውም ኅብረተ ሰቡ በዐባይ ጠንቋይ ማመንን እንዲጠራጠርና እንዲጠይቅ፣ ብሎም እንዲተው ተፅዕኖ የሚያደርግ ድርጊት ፈጽመዋል፡፡ ድርጊታቸው ለልማዳዊ እምነት የነበራቸውን አመለካከትም ያስረዳል፡፡

አዝማሪ አብተው የሚከተሉትን የምክርና የማስጠንቀቂያ ግጥሞች ጨምሮ ማዜሙን ገሪማ (፲፱፻፸፰፤ ፻፬) ገልጸዋል፡፡

፩) በቴዎድሮስ የለም ጋሻ፣
ማረስ ይሻላል በማረሻ፤

፪) ማረስ ይሻላል መገበር፣
እጅ እግርን ይዞ ለመኖር፤

፫) አላርስም ያሉ አልነግድ፣
ተመለመሉ እንደ ግንድ፡፡

በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ የተጠቀሱት ቃለ ግጥሞች፣ በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ሰዎች ማድረግ የሚገባቸውን በመንገር ይመክራል፡፡ ምክሩም፣ ከቅጣት ለመዳን ኑሮን በእርሻ ወይም በንግድ መመሥረትና ለንጉሡ መገበር ተገቢ መኾኑ ይነግራል፡፡ ለምክሩ ማጠናከሪያም፣ ከንጉሡ ሐሣብ ተጻራሪ ተግባር በፈጸሙ ሰዎች ላይ የደረሰባቸውን አስከፊ ቅጣት በተራ ቁጥር ፫

[20]“በትግሬ የሚገኝ አንድ ትልቅ ወንዝ ነው” (ገሪማ፣ ፲፱፻፸፰፤ ፻፬)፡፡

በተጠቀሰው ቃለ ግጥም በማስረዳት ከምክሩ ያፈነገጡ ሰዎች የሚደርስባቸውን ከባድ ቅጣት ይነግራል፡፡ ለዐፄ ቴዎድሮስ "አንገብርም" በማለት ነፍጥ ታጥቀው ጋሻ አንግበው "እንዋጋለን" የሚሉ ወይም እያረሱ ወይም እየነገዱ ከመገበር ይልቅ በዘረፋ የሚሰማሩ ሰዎች የሚፈጸምባቸው ቅጣትም፣ ዛፍ ቅርንጫፎቹ እንደሚመለመለው ኹሉ፣ እጅ እግራቸው መቆረጡን[21] ግጥሙ ይገልጻል፡፡ ግጥሙ በተነገረበት ዐውድ፣ በሰሜንና በትግራይ በሚኖሩ የዐፄ ቴዎድሮስ ተቀናቃኞች ላይ የሚወሰደው ቅጣት ምን ሊኾን እንደሚችል በመግለጽ ያስጠነቅቃል፡፡ ግጥሙ እንደሚያስረዳው አዝማሪ አብተው የገለጸው ቅጣት በደጅ አዝማች ንጉሤና በፊታውራሪ ተሰማ ላይ መፈጸሙን ታሪካቸው ያስረዳል፡፡ (ገሪማ፣ ፲፱፻፺፯)

ዐፄ ቴዎድሮስ የደጅ አዝማች ውቤን የእኅት ልጅ፣ ልጅ (በኋላ ደጅ አዝማች) ንጉሤንና ወንድሙን አገው ተሰማን (በኋላ ፊታውራሪ ተሰማ) እጅና እግር በመቁረጥ ቀጥተዋል፡፡ ለቅጣት ያበቃቸውም፣ ደጅ አዝማች ንጉሤ በዐፄ ቴዎድሮስ ላይ በመሸፈት የዐመፅ ተግባር መፈጸማቸው የጦር እርዳታ ለማግኘት ወደ ፈረንሳይ መንግሥት መልእክተኛ ልከው ጦር ማስመጣታቸው ነው፡፡[22] ቅጣቱ ፊታውራሪ ተሰማ ላይ የተፈጸመው የደጅ አዝማች ንጉሤ አባሪ ተባባሪ በመኾናቸው ነው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ ደጅ አዝማች ንጉሤን ለማጥቃት በ፲፰፻፶፫ ዓ. ም. በጥቅምት ወር ከጎንደር ተነሥተው ወደ ትግራይ ገሠገሡ፡፡ ተከዜን ተሻግረው ደጅ አዝማች ንጉሤና ወንድሙ ፊታውራሪ ተሰማ ሣህሉ ወደ አሉበት ቦታ ደርሰው አደጋ ጣሉባቸው፡፡ በጦርነቱ ደጅ አዝማች ንጉሤ ሲማረኩ፣ ወንድማቸው ፊታውራሪ ተሰማ አምልጠው ወደ አገራቸው ሲኼዱ ተምቤን ላይ ተማርከው እጅ እግራቸው ተቆርጦ ተሰቀሉ፡፡ ደጅ አዝማች ንጉሤም በፈጸሙት የአመፅ

[21]በዘመኑ ጥፋተኛ የተባለን ሰው ዐይን በማጥፋት ወይም እጅና እግር በመቁረጥ መቅጣት የተለመደ ነበር፡፡ ይኽ የቅጣት ዓይነት በዘመኑ በነበሩ መሳፍንት ይፈጸም እንደ ነበር ከሚከተለው ማስረጃ እንረዳለን፡፡ "ራስ ኃይሉ ነገረ ሠሪ የነገረውን ቂም አድርጎ የደጅ አዝማች ወልታን ፪ ዐይን የሌሎችንም መኳንንቶች ጨምሮ በፍላት አፍስሶ በገድ ዋሻ በመሰላል አስወርዶ አስሮ አኖረ፡፡ ከጥቂት ቀን በኋላ እውነትና ጢስ ይወጣበት አያጣ ሆኖ የደጅ አዝማች ወልታ ደህና ሰውነት ተገለጠ፡፡ ቀዳማዊ ራስ ኃይሉም ዓይኑን በማፍሰሱ አዘነ፡፡ በበገና እንዲህ ብሎ አለቀሰ፡፡

አዳምንና ሔዋንን እንዳሳሳታቸው ሰይጣን፣
እኔም ፩ ቀን ባጠፋሁ እኖራለሁ ሳዝን፡፡

ራስ ኃይሉ በሠራው ስህተት በበገና ከማልቀሱም በላይ ደጅ አዝማች ወልታንም በገድ ዋሻ ከታሠረበት አውጥቶ ለቤቱ መካር አደረገው፡፡ ሊበንን ማደሪያ ሰጠው፡፡ ብዙ ጉልት ጨመረው፡፡ የዚህን ጊዜ ደጅ አዝማች ወልታ በራስ ኃይሉ አዳራሽ መኳንንቱ በተሰበሰበበት መብልና መጠጥ፣ ደስታና ጨዋታ በሆነበት አዝማሪ አስነሣ፡-

ሁለት ጊዜ በላሁ ከዚህ ቤት ገብቼ፣
ፊትም በወራሪ አሁን ተመርቼ፡፡

በል ብሎ ግጥም ገጠመ" (ተክለ ኢየሱስ፣ 2008፤ 181)፡፡

እንደዚሁም፣ ደጅ አዝማች ተድላ ከደጃች ቆለኛ ጋር ተዋግቶ ድል ካደረገ በኋላ "ምርኮኛውን አስገብቶ ቀኝ ቀኝ እጁንና ግራ ግራ ጆሮውን እየቆረጠ ሰደደው፡፡ በዚህ ጊዜ የደጅ አዝማች ተድላ ወታደር፡-

ሠርጉድ ሠርጉድ ብሎ ሠርጉድ መነመነ፣
ቀኝ እጁን ገብሮ በግራው ለመነ፡፡"

በማለት በቆለኛ ላይ ዘፈነ (ተክለ ኢየሱስ፣ 2008፤ 211)፡፡

[22]ከፈረንሳይ የመጣው ጦር ከዐፄ ቴዎድሮስና ደጋፊዎቻቸው የሚሰነዘርበትን ጥቃት ፈርቶ ከደጅ አዝማች ንጉሤ ጋር ሳይገናኝ ወደ ምፅዋ ተመለሰ፡፡ (ገሪማ፣ ፲፱፻፺፯)

ተግባር እጅ እግራቸውን ተቀጥተው[23] በስቅላት ተቀጡ (ገሪማ፣ ፲፱፻፺፪፤ ፻፶፱ - ፻፷)፡፡ የአዝማሪ አብተው የሙገሳ ግጥም ዐፄ ቴዎድሮስ በወሎና በሸዋ በነበሩ ተቃዋሚዎቻቸው ላይ የፈጸሟቸውን ቅጣቶችም ያስታውሳል፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ወሎ ዘምተው "የወሎ ሕዝብ ግባ ብትገባ ይሻልሃል፡፡ ያለዚያ እጅና እግርህን ታጣለህ፡፡ ከቅጣቱ በተጨማሪ ወንዱን እጅና እግሩን፤ ሴቱን ጡቱን እንዲቆረጥ አዝዣለሁ፡፡ ነፍስ የገደልክ ቋንጃ የቆረጥክ ምሕረት አድርጌልሃለሁና ግባ፡፡ አልገባም ብትል ለአካልህ እዘንለት፡፡ ሹም ሰጥቸሃለሁ፡፡ በሹምህ ታዘዝ" የሚል ዐዋጅ አስነግረዋል (ገሪማ፣ ፲፱፻፺፪፤ ፹፱)፡፡ በዐዋጁ ያልተረጋጋው የወሎ ሕዝብ፤ ሽፍታና ወያኔ እየኾነ ለወረራ የኼደውን ወታደር እየገደለ ቢያስቸግራቸው በየቀኑ በሚደረገው ግጭት የተማረኩትን ወሎዬዎች ኹለት ኹለት እጃቸውን እየቆረጡ፣ የተቆረጡትን እጆች በገመድ ከዐንገታቸው ላይ እያሰሩ ለመቀጣጫ ለቀቋዋቸው፡፡ ይኽን ድርጊት ያየ የወሎ ሰው አጥብቆ ተሸበረ፤ ተንቀጠቀጠ (Fusella, 1958: 12-13፤ ደብተራ ዘነብ፣ 19-22፤ አለቃ ወልደ ማርያም፣ 8-10)፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ ሸዋ ዘምተው አቤቶ ሰይፉን ወግተው ድል ካደረጉ በኋላ ምርኰኛውን ሰብስበው ቀኝ እጁንና ግራ እግሩን አስቆረጡት፡፡

"በሺ፰፻፶፯ ዓ. ም. በዘመነ ማቴዎስ በሰኔ ፳፬ ቀን ሌሊት ምኒልክ ከመቅደላ ዐምባ አምልጠው ኼዱ፡፡ የምኒልክ ከመቅደላ ዐምባ ማምለጥ እንደታወቀ ጧት በወረሂመኖ በ[የ]ነፍጥ ተኩስ እንደ ግባት ተሰማ፡፡ የነፍጡም ተኩስ ከሰፈር በተሰማ ጊዜ አጼ ቴዎድሮስ የወረሂመኖ ሰው መጥቶ ምኒልክን የተቀበለ መስሏቸው በዚህ ነገር ተበሳጭተው መቅደላ ታስረው የነበሩትን የወሎንና የወረሂመኖን ይማማውን፣ መኳንንቱንም እጃቸውንና እግራቸውን እየቆረጡ ገደል ሰደዷቸው" (ገብረ ሥላሴ፣ ፲፱፻፶፱፤ ፶፫)፡፡ የተገለጹት የቅጣት ዓይነቶች በተቀናቃኝ ላይ መፈጸማቸው አሸናፊነትንና ጀግንነትን የሚገልጽ ተግባር ተደርጎ በመቆጠሩ ዐፄ ቴዎድሮስ ተሞግሰውባቸዋል፡፡

አዝማሪ አብተው በቃለ ግጥሙ ሰዎች እያረሱ፣ እየነገዱና እየገበሩ በሰላም ሕይወታቸውን በመምራታቸው የሚያጋጥማቸው ችግር አለመኖሩን ይነግራል፤ ይመክራል፡፡ ከዐፄ ቴዎድሮስ ዐዋጅና አመራር የሚያፈነግጡ ሰዎች ግን ከፍተኛ ቅጣት እንደሚደርስባቸው የተፈጸመን ቅጣት መሠረት በማድረግ ያስረዳል፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስን ያስሞገሳቸው ከእሳቸው ዓላማ ያፈነገጡ ሰዎችን ማሸነፍና በእጃቸው ጨብጠው፣ በእግራቸው ረግጠው መቅጣት በመቻላቸው ነው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ በተለያዩ መሳፍንት የተከፋፈለችውን ኢትዮጵያን በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር እንድትመራ የማድረግ ዓላማቸውን በመተግበራቸው፡-

[23]"ደጃዝማች ንጉሤ አጼ ቴዎድሮስ እጅና እግር በመቁረጥ የሚቀጡ መሆናቸውን ስለሚያውቅ ይህን አፈጻጸም ለማጸየፍ ሲል ከፍ ያለ በደል የፈጸመ ወንጀለኛ ተይዞ ሲቀርብ "እባክህ ወዳጄ እጅና እግር በዝናብ አይበቅልም ግረፍና ልቀቀው" ይል ነበር እንጅ አይቆርጥም አይሰቅልም ነበር" (ገሪማ ታፈረ፣ ፲፱፻፺፪ ፤ ፻፷)፡፡

የሸዋ የጎዣም ተበትኖ ከብቱ፣
የወሎ የትግሬ ተበትኖ ከብቱ፣
ገዛው አባ ታጠቅ ሰብስቦ በሀብቱ፡፡

በማለት መሞገሳቸውን ማኅተመ ሥላሴ (፲፱፻፷፩፣ ፪፻፶፫) ገልጸዋል፡፡ ግጥሙ በሰሙ አባ ታጠቅ የሸዋን፣ የጎጃምን፣ የወሎንና የትግራይን ከብት በሙሉ በገንዘባቸው ገዙ፤ ጠቀለሉት፣ የተጠቀሱት ቦታዎች ላምና በሬ የሚገኘው ከእሳቸው ቤት ብቻ ነው በማለት በሀብታቸው ያሞግሳቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በታሪክ እንደሚታወቀው ዐፄ ቴዎድሮስ በተጠቀሱት ግዛቶች የነበሩትን ላምና በሬ የራሳቸው ሀብት በማድረግ አይታወቁም፡፡ እሳቸው የሚታወቁት ጎንደርን፣ ጎጃምን፣ ትግራይን፣ ወሎንና ሸዋን ከመሳፍንቱ አስለቅቀው አንድ አድርገው በመግዛትና በማስገበር ነው፡፡ የእነዚኽን ቦታዎች ገዥዎች በመውጋትና በማሸነፍ የኢትዮጵያን አንድነት መሠረት በመጣል ነው፡፡ በምርምር ቅኔ አባ ታጠቅ በግጥሙ የተሞገሱት በሀብታቸው ሳይኾን የተጠቀሱትን ግዛቶች በጦር ኃይል አሸንፈው በመያዛቸው፣ በማስገበራቸው፣ በማስተዳደራቸው፣ በመምራታቸው፤ ጠቅልለው በመግዛታቸው አንድነትን በመፍጠራቸው ነው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ በመሳፍንት የተከፋፈለችውን ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ የመግዛት ዓላማቸውን የሚያሞካሽ ሐሣብ ሲነገሯቸው ከፍተኛ ደስታ ይሰማቸው ነበር፡፡ ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (ገጽ 151) እንደ ገለጹት ዐፄ ቴዎድሮስ የሚከተለውን የአዝማሪ ግጥም ሰምተው ተደስተዋል፡፡

ቴዎድሮስን ባል ብሎ ማን አምኖ ይቆርባል፤
ሴሰኛውን ጎበዝ ያራቱን ማእዘን ባል፡፡[24]

ማንነቱ በስም ባልተገለጸ አዝማሪ የተዜመላቸው ይኽ ቃለ ግጥም በሰሙ ዐፄ ቴዎድሮስን ይሰድባል፡፡ ስድቡም ዐፄ ቴዎድሮስ ዘማዊ በመኾናቸው በኹሉም አቅጣጫዎች (በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅና በምዕራብ አቅጣጫዎች) ቁባት/ሚስት አላቸው የሚል ነው፡፡ በየአቅጣጫው መቆበታቸው ወይም ከአንድ በላይ ሚስት ማግባታቸው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ቀኖና ተቃራኒ ተግባር ፈጽመዋል፡፡ የትዳር ሕይወትን በቁርባን ወይም በሥጋ ወደሙ ለመወሰን፣ ከትዳር በላይ ማመንዘርን መተው ግድ የሚለውን ተግባር አልፈጸሙም፡፡ ይኽ የአመንዝራነት ባሕርይ እያለባቸው በአንድ የትዳር ጓደኛ የመወሰን ተግባር ለመፈጸምና ከእሳቸው ጋር በቁርባን ለመወሰን አይቻልም፡፡ ቁባቶች ወይም ሚስቶች ካሏቸው ዐፄ ቴዎድሮስ ጋር ለመቁረብ የእምነቱ ቀኖና አይፈቅድም፡፡ ከእንዲህ ዓይነት ድርጊታቸው ታቅበዋል ቢባል እንኳ፣ "የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማእድ" እንደሚባለው ዐፄ ቴዎድሮስ ቁባት የመቆበት ባሕርያቸውን አይተውም የሚል ሥጋት ይፈጥራል፡፡ የሴሰኝነት ባሕርይ ካለባቸው ዐፄ ቴዎድሮስ ጋር መቁረብ አይታሰብም በማለት ቃለ ግጥሙ በሰሙ ይገልጻል፡፡ ይኽም የዐፄ

[24]ዐፄ ቴዎድሮስ ኹሉም የሸዋ መኳንንት እርሳቸው ዘንድ እንዲቀርቡ ትእዛዝ ያስተላልፋሉ፡፡ አቦዬም ለዐፄ ቴዎድሮስ ግብር ይዞ ኼደ፡፡ በዛብህ ግን አገር እንዲጠብቅ እንዲቀር ተደረገ፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስም "እሾማለሁ" በማለት ለኼደው መኳንንት ታላቅ ግብር አገቡ፡፡ በግብሩ ላይም አዝማሪ የተጠቀሰውን ግጥም ደረደረ፡፡

ቴዎድሮስን ሰብእና፣ ዝቅ የሚያደርግ፣ የሚያዋርድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ አዝማሪው ገድሎ ማዳን በሚሉት ዘዴ ዐፄ ቴዎድሮስን በወርቁ አሞግሷል፡፡

በቃለ ግጥሙ ዐፄ ቴዎድሮስ የተሞገሱት ሴሰኛ፣ ማዕዘንና ባል በሚሉት ቃላት አማካኝነት ነው፡፡ ሴሰኛ የሚለው ቃል ዐፄ ቴዎድሮስ እንደ ዘመነ መሳፍንት ገዢዎች ግዛታቸውን በአንድ ቦታ አለመወሰናቸው በሰሙ የተጠቀሱትን ግዛቶች ኹሉንም ጠቅልለው የመግዛት ፍላጎት ያላቸው መኾኑ ነው፡፡ ሴሰኛ የሚለው ቃል በግጥሙ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም የሚያመሰጥረው ማመንዘርን፣ መሽርሞጥን ሳይኾን፣ አንድን ነገር ለመፈጸም፣ ለማከናወን ከፍተኛ ፍላጎት፣ ጉጉት ማሳየትን፣ በአንድ ነገር አለመርካትንና አለመወሰንን ነው፡፡ የዐፄ ቴዎድሮስ ከፍተኛ ፍላጎት፣ ጉጉት መሳፍንቱን ወግተውና አሸንፈው ሀገርን አንድ አድርጎ መምራት ነው፡፡

ማዕዘን የሚለው ቃል በግጥሙ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም በኢትዮጵያ በምሥራቅ፣ በምዕራብ፣ በሰሜንና ደቡብ አቅጣጫዎች የሚገኙ ግዛቶችን ያመለክታል፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ከቋራ (ከምዕራብ) ተነስተው ወደ ምሥራቅ በመኼድ በጌምድርን፣ ላስታንና ወሎን ጠቅልለዋል፡፡ ወደ ደቡብ ዘምተው ጎጃምን፣ ዳሞትን ከዚያም አልፎ ሸዋን አስገብረዋል፡፡ ወደ ሰሜን ዘምተው ደጅ አዝማች ውቤን ወግተውና አሸንፈው ግዛታቸው የነበሩትን ሰሜንን፣ ትግራይን እስከ ቀይ ባሕር ድረስ (የዛሬዋን ኤርትራን በከፊል) ጠቅልለዋል፡፡

ባል የሚለው፣ የበላይነትን፣ የአሸናፊነትን፣ የአዛዥነትንና የገዥነትን ተግባር ይገልጻል፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ባል የመባላቸው ምክንያትም፣ በተጠቀሱት ግዛቶች የነበሩትን መሳፍንት (ገዥዎች) ኹሉንም አሸንፈው ግዛቶቻቸውን አንድ አድርገው በበላይነት ማስተዳደራቸው፣ መግዛታቸው፣ መምራታቸው፣ ፍትሕና ርትዕ መስጠታቸው ነው፡፡ የአራቱም ማዕዘን ባል በማለት የተሞገሱትም፣ በተለያዩ አቅጣጫዎች በዘመነ መሳፍንት ተከፋፍላ የነበረችውን ኢትዮጵያን አንድ በማድረጋቸው፣ በበላይነት በመምራታቸውና በማስተዳደራቸው ነው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ በተለያዩ ግዛቶች የነበሩትን መሳፍንት ወግተው ድል በማድረጋቸው ከተሞገሱባቸው ቃለ ግጥሞች መካከል፡-

፩) የኢትዮጵያ መሳፍንት ቅስና ቢያምራቸው፣
ካሣ ጳጳስ ሆኖ ሁሉን ባረካቸው፡፡

፪) ወይዘሮ አትጠገብ ምናል ብትሸጥ ኰሶ፣
ሐበሻን የሚያሽር መልሶ መላልሶ፡፡

፫) የኰሶ መድኃኒት ካሣ ቢያጠጣቸው፣
የኢትዮጵያ መሳፍንት ሁሉ አስቀመጣቸው፡፡

የሚሉት በገሪማ (፲፱፻፺፮፤ ፻፹፯) ተጠቅሰዋል፡፡ የግጥሞቹ መልእክቶች የቀረቡት በቀላሉ መረዳት በሚቻለው በሰሙ ነው፡፡ ዝርዝሩን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

በተራ ቁጥር ፩ የተመዘገበው ቃለ ግጥም ሰማዊ ፍቺ በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የነበሩ መሳፍንት “የቅስና መዕረግ ማግኘት በመፈለጋቸው” “ጳጳሱ ዐፄ ቴዎድሮስ” እጃቸውን በመሳፍንቱ ራስ ላይ ጭነው ፈቅደውና ባርከው አቀሰሏቸው፤ የቤተ መቅደስ አገልጋይ፣ ባራኪ፣ ቀዳሽ፣ ናዛዥ፣ የነፍስ አባት እንዲኾኑ መንፈሳዊ ሥልጣን ሰጧቸው ማለት ነው፡፡ መንፈሳዊ ሥልጣን መስጠት የቻሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከኤጲስቆጶስ በላይ ከሊቀጳጳስ በታች የኾነ መንፈሳዊ አባትነት ሥልጣን ስለ አላቸው፣ ጳጳስ በመኾናቸው ነው፡፡

ደጅ አዝማች ካሣ በታሪክ የሚታወቁት በመንፈሳዊ አባትነት ባለመኾኑ በሰሙ የተገለጸው ተግባር የእሳቸውን እውነተኛ ማንነት አይገልጽም፡፡ እሳቸው የሚታወቁት ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ለመግዛት መሳፍንቱን ወግተው በማሸነፍ ሀገራዊ አንድነትን በመመሥረት ነው፡፡ የቃለ ግጥሙ መልእክትም ይኸው ነው፡፡

በሰሙ ተደብቆና ተሸፍኖ ደጅ አዝማች የተሞገሱበት የግጥሙ ምሥጢር የተነገረው ባረከ በሚለው ቃል ነው፡፡ ባረከ የሚለው ቃል በቁሙ አረደ፣ ዐንገት ቆረጠ፣ ገደለ የሚል ፍቺ አለው፡፡ የቃሉ ዐውዳዊ ፍቺ ማሸነፍ፣ ድል ማድረግ የሚል ነው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ለመሞገስ ያበቃቸውም ኢትዮጵያን ከፋፍለው ይገዙ የነበሩትን መሳፍንት ወግተው ድል ማድረጋቸው፣ መግደላቸው ነው፡፡ ድል አድራጊው ደጅ እዝማች ካሣ ከእግዚአብሔር በታች ከመሳፍንቱ በላይ በመኾን የኢትዮጵያ ሕዝብ እረኛ ጠባቂ መኾናቸውን የሙገሳ ግጥሙ ይገልጻል፡፡

በ፪ኛው ተራ ቁጥር የዐፄ ቴዎድሮስ እናት ወይዘሮ አትጠገብ አጥተው ነጥተው ኮሶ መሸጣቸውን መልካም ተግባር አድርጎ ይገልጻል፡፡ ይኸም “የኰሶ ሻጪ ልጅ” በማለት ደጅ አዝማች ካሣን ይንቁና ይሰድቡ የነበሩ ሰዎች የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ “የኰሶ ሻጪ ልጅ” በማለት የሰደቧቸውን ደጅ አዝማች ወንድይራድንና ፊታውራሪ ጠምሬን ኰሶ አጠጥተው መግደላቸው ይታወቃል፡፡(ተክለ ኢየሱስ፣ 2008፤ 206፤ ገሪማ፣ ፲፱፻፺፪፤ ፺፯) የደጅ አዝማች ካሣ እናት የኮሶ ፍሬ ይሸጡ እንደ ነበር መናገር ቅጣት እንደሚያስከትል እያወቀ አዝማሪው በግጥሙ መግለጹ ሊያሞግሳቸውና ከፍ ከፍ አድርጎ ሊገልጻቸው ዓልሞና ወስኖ እንጂ ሊሰድባቸው ደፍሮ አይደለም፡፡ ሙገሳውም፣ የኮሶ መድኃኒት ፈዋሽነትና የኢትዮጵያን ችግር መፍታት ተመሳሳይ መኾኑን በማነጻጸር የቀረበ ነው፡፡ የደጅ አዝማች ካሣ እናት ወይዘሮ አትጠገብ የሚሸጡት የኰሶ ዛፍ ፍሬ ተወቅጦና ተበጥብጦ ሲጠጣ እየመረረ ኰሶ የተባለውን ትል ከኾድ ውስጥ በመግደል፣ በማስወጣት ሰውን ከሕመሙ እንደሚፈውሰው፣ እንደሚያሽረው ኹሉ፣ ከእሳቸው አብራክ የተገኙት ደጅ አዝማች ካሣም የ“ሐበሻን” ሕዝብ ከገጠመው የመከፋፈል ችግር ታድገዋል፡፡ የደጅ አዝማች ካሣ ርምጃም በመሳፍንቱ ላይ መራራ ሽንፈትን አስከትሏል፡፡ የኰሶ መድኃኒት ግለሰቦችን ሲፈውስ የደጅ አዝማች ድል ማድረግ ኢትዮጵያን ፈውሷል ማለት ነው፡፡ ዐጼ ቴዎድሮስ የተሞገሱትም የኢትዮጵያን ችግር መፍታት በመቻላቸው ነው፡፡

በ፫ኛው ተራ ቁጥር በተጠቀሰው ቃለ ግጥም የተነገረው ሙገሳ በ፩ኛው እና በ፪ኛው ተራ ቁጥሮች በተጠቀሱት ቃለ ግጥሞች ከተሞገሱባቸው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ባህላዊው የኰሶ

መድኃኒት ተወቅጦና ተበጥብጦ ሲጠጣ ይመራል፤ ተቅማጥም ሊያስከትል ይችላል፡፡ በዚኽም ምክንያት ኮሶን ሰዎች ፈቅደውና ወደው የሚጠጡት ሳይኾን ከኾዳቸው ያለውን ትል ማስወጣት ግድ ስለሚኾንባቸው ነው፡፡ መራራውን የኮሶ መድኃኒት ካልጠጡ የኮሶው ትል ጉዳት ያስከትልባቸዋል፡፡ ኢትዮጵያን የከፋፈሉት መሳፍንት በኃይል ካልተወገዱ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ችግር ያስከትላሉ፡፡ ችግሩን ለመፍታት በመሳፍንቱ ላይ ጦርነት በመክፈት ማሸነፍ የታሪክ ግዴታ ነው፡፡ የታሪክ ግዴታውን የተቀበሉት ደጅ አዝማች ካሣ በመሳፍንቱ ላይ ጦርነት ከፍተው ድል በማድረግ ኢትዮጵያን ከገጠማት ችግር እንድትገላገል አድርገዋል፡፡ አዝማሪው በጦርነት ማሸነፋቸውንም ኮሶ በመጠጣት ከበሽታ መፈወስ ጋር አነጻጽሮበታል፡፡ አዝማሪው የኮሶ መድኃኒት የጠጣ ሰው እንደሚያስቀምጠው ኹሉ ዐፄ ቴዎድሮስ ጥቃት የሰነዘሩባቸው መሳፍንት በፍርሃት ርደውና ኾዳቸው ቀጥኖ እንዳስቀመጣቸው በመግለጽ ጀግንነታቸውን አሞግሷል፡፡ ተቀናቃኞቻቸው እንዲፈሯቸው ያደረገው የአሸናፊነትና የጀግንነት ዝናቸው በጠላቶቻቸውም በመሰማቱና በመታወቁ ነው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ መሳፍንቱን በማሸነፍ በፈጸሙት የጀግንነት ተግባር ከተሞገሱባቸው ግጥሞች መካከል የሚከተሉት በገሪማ (፲፱፻፹፯፤ ፪፻፯ - ፪፻፰) ተመዝግበዋል፡፡

፩) አባ ታጠቅ ካሣ ሱሪ መስፋት ሲያውቁ፣
ገጣጥመው ሰፉና ኹሉን አስታጠቁ፡፡

፪) ሁሉ ታጥቆ ነበር እስከ ቁርጭምጭምቱ፣
ያባ ታጠቅ ሱሪ ተባቱ ተባቱ፡፡

በተራ ቁጥር ፩ ደጅ አዝማች ካሣ የተጠሩት በፈረስ ስማቸው አባ ታጠቅ ተብለው ነው፡፡ አባ[25] የሚለውም የታጠቅ ባለቤት፣ የታጠቅ ጌታ ማለት ነው፡፡ ግጥሙ ከፈረስ ስማቸው ጋር አጣምሮ በመጥራት የደጅ አዝማች ካሣን ጀግንነት ይገልጻል፡፡ የግጥሙ ሰም ደጅ አዝማች ካሣ ሱሪ የመስፋት ችሎታ ስለ አላቸው ሰፍተው ብዙ ሰዎችን ማልበሳቸውን ይነግራል፡፡

በግጥሙ ሱሪ የሚለው ቃል ወንድነትን፣ ጀግንነትን በመግለጹ ዐፄ ቴዎድሮስ ተሞግሰውበታል፡፡ ከዚኹ ጋር ቀጥታ ግንኙነት አለው፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ በጀግንነትና በወንድነት ተግባራቸው ተበታትና የነበረችውን ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ለመምራት የነበራቸውን ዓላማ በማሳካታቸውና በፈጸሙት ጀግንነት ደጋፊዎቻቸውን በማኩራታቸውና በማስደሰታቸው ተሞግሰዋል፡፡ ግጥሙ በወርቁ የሚገልጸው ይኸንኑ ነው፡፡

በ፪ኛው ተራ ቁጥር በተጠቀሰው ቃለ ግጥም አዝማሪው በሰሙ የገለጸው የአባ ታጠቅ ሱሪ ከወገብ እስከ ባት የሚሸፍን መኾኑን ነው፡፡ የደጅ አዝማች ከሣ አለባበስ የተነጻጸረው እሳቸውን ይቀናቀኑ ከነበሩት የክፍላተ ግዛቱ መሳፍንት ከወገብ እስከ ቁርጭምጭሚት አለባበስ

[25]የኢትዮጵያን ነገሥታት ዐፄ ቴዎድሮስን፣ አባ ታጠቅ፤ ዐፄ ዮሐንስን፣ አባ በዝብዝ፤ ዐፄ ምኒልክን፣ አባ ዳኘው፤ ዐፄ ኃይለ ሥላሴን፣ አባ ጠቅል ብሎ መጥራት የተለመደ መኾኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

ጋር ነው፡፡ በግጥሙ የተጠቀሱትን የሱሪ ዓይነቶች መልበስ የሚችለው ኢኰኖሚያዊና ማኅበራዊ ደረጃው ከፍ ያለ ሰው ነው፡፡ እስከ ባት የሚደርስ ሱሪ ከለበሰው ሰው እስከ ቁርጭምጭምቱ የለበሰው ሰው ኢኰኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ደረጃው ከፍ ያለ ነው፡፡ እስከ ቁርጭምጭምት የሚለበሰውን ሱሪ የለበሱት ኢትዮጵያን ተከፋፍለው ይገዟት የነበሩት መሳፍንት ናቸው፡፡ ይኸ አለባበሳቸውም ክብራቸውን ከፍ አድርጎና ከደጅ አዝማች ካሣ የበለጠ እንደ ነበር ፍንጭ ይሰጣል፡፡ በግጥሙ እንደተገለጸው ተቀናቃኞቻቸው እስከ ቁርጭምጭምታቸው የሚሸፍን ሱሪ ሲለብሱ ደጅ አዝማች ካሣ ግን የታጠቁት እስከ ባታቸው[26] ድረስ ነው፡፡ ይኸም በጊዜው አባ ታጠቅ አቅማቸው ጎልብቶ ተቀናቃኞቻቸው የነበሩትን መሳፍንት ከማሸነፋቸው በፊት የነበራቸውን ኢኰኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ደረጃን ይገልጻል፡፡ አዝማሪው በቃለ ግጥሙ ሰም የገለጸውም ይኸንኑ ባህላዊ አለባበስ መሠረት ያደረገውን ኢኰኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ደረጃ ነው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ የተሞገሱበት የግጥሙ ዋናው መልእክት በትግላቸው የመጀመሪያ ምዕራፍ ከእሳቸው የጎለበቱና "አንቱ" ይባሉ የነበሩትን መሳፍንት ያሸነፉ ወንድ፣ ጀግና ናቸው በሚል ነው፡፡ ጀግንነታቸው የተገለጸውም "ተባቱ"[27] በሚለው ቃል ነው፡፡ ቃለ ግጥሙ በገባበት ዐውድ ተባቱ የሚለው ቃል በወርቃዊ ፍቺው ወንድነትን፣ ጀግንነትን መግለጹ የዐፄ ቴዎድሮስ ማንነት ከፍተኛ መኾኑን ይገልጻል፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በአዝማሪ የተሞገሱት በተለያዩ አካባቢዎች ሸፍተው ችግር የፈጠሩባቸውን ወግተው ማሸነፋቸው ብቻ አይደለም፡፡ በታሪክ የኢትዮጵያ ግዛት ነበሩ ያሏቸውን ምፅዋንና ስናርን ወደ ግዛታቸው ለመጠቅለል፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ተከታዮች እንደ ቅዱስ ቦታ በመቁጠር የሚሳለሙትን ኢየሩሳለምን ከቱርክ ነፃ ለማውጣት መዛታቸው በአዝማሪ አስሞግሷቸዋል፡፡ ይኸንንም በተራ ቁጥር ፫. ፫ በተገለጸው ንዑስ ርእስ እንመከታለን፡፡

### ፬. ፫. ከግዛታቸው የራቁ ቦታዎችን ነፃ ለማውጣት መመኘታቸው እንደ አስሞገሳቸው

የዐፄ ቴዎድሮስ ምኞት የመሳፍንቱን ግዛቶች አንድ አድርጎ በመግዛት ብቻ የተገደበ አልነበረም፡፡ በመሳፍንቱ ግዛት ሥር ያልነበሩትንና የኢትዮጵያ ግዛት አካል ናቸው ያሏቸውን ምፅዋንና ስናርን የግዛታቸው አካል ለማድረግ ምኞት እንደ ነበራቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች

---

[26]ደጅ አዝማች ካሣ ባታቸው ድረስ መልበሳቸውን ግጥሙ ይገልጻል፡፡ ይኸ ዓይነቱ ሱሪም ባት ተኹለት ተብሎ ይጠራል፡፡ ሱሪውም፣ "ከጉያና ከጭን አካባቢ ሰፊ ሆኖ ወደ ታች ጠበብ እያለ ይወርድና ባት ላይ" በመቆም ከላይኛው የባት ክፍል ጀምሮ እስከ ወገብ ያለውን የሰውነት ክፍል ይሸፍናል፡፡ ሱሪው ባትን ከኹለት በመክፈሉ ምክንያት ባት ተኹለት ይባላል፡፡

[27]ተባቱ የሚለው ቃል የተገኘው ተባእት ከሚለው ስም ነው፡፡ ወንዴ ፆታን የሚገልጸው ተባእት "እ" የሚለውን ምዕላድ በመጉረድ "ተባት" የሚል ቃል ተገኘ፡፡ ይኸው ቃል "ኡ" የሚል ድኅረ ቅጥያ በመጨመር ተባቱ የሚለውን ቃል አስገኘ፡፡ ቃሉም እሱ/እርሱ የሚል ሦስተኛ መደብ ተባእታይ ፆታ ነጠላ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስምን ይጠራል፡፡

በአንደበታቸው ይገልጹ ነበር፡፡ ከኢትዮጵያ ተቆርሶ በቱርክ የተያዘውን ምፅዋን ለማስለቀቅ ነበራቸውን ምኞትም "አሁን ምጥዋን አክ ብዬ እንትፍ ልበልበት[?]"[28] በማለት ይዝቱና ያስፈራሩ ነበር፡፡ ይኽን ምኞታቸውን የተገነዘበው አዝማሪ አብተው፡-

> ፩) ሥርዶ አልግጥም[29] አለ የካሣ ፈረስ፣
> የምፅዋ አሻቦ ሳይነሰነስ፡፡
>
> ፪) ለባሕር ማዶ ሰው መቆያ ድግስ፣
> ዳግማዊ ካሌብ መጣ ቴዎድሮስ፡፡

በማለት ያሞግሳቸው እንደ ነበር ገሪማ (፲፱፻፺፮ ፤ ፻፹፮) ገልጸዋል፡፡

በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው ቃለ ግጥም ሰውኛ ዘይቤን በመጠቀም የዐፄ ቴዎድሮስ ፈረስ ከምፅዋ ጨው መጥቶ በሚግጠው ሣር ላይ ካልተነሰነሰ አልግጥም ማለቱ ተገልጿል፡፡[30] ይሁን እንጂ፣ በዐፄ ቴዎድሮስ የሥልጣን ዘመን ምፅዋ በቱርክ መንግሥት ቁጥጥር ነበር፤ ከዚኽ ቦታ ለፈረሳቸው አሻቦ (ጨው) ለማምጣት ከቱርክ መንግሥት ጋር የንግድ ግንኙነት ማድረግ ወይም በጦር ኃይል ቦታውን ማስለቀቅ ይጠይቃል፡፡ አዝማሪ አብተው ቃለ ግጥሙን ያዜመው ደጅ አዝማች ካሣ በቱርክ የተያዘውን ቦታ በኃይል በማስለቀቅ ስለ መኾኑ በተራ ቁጥር ፪ ከተመዘገበው ቃለ ግጥም መልእክት መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸውም፣ ባሕር ተሻግሮ በመጣው የቱርክ መንግሥት ደጅ አዝማች ካሣ የጦር ድግስ እንዳዘጋጁለት ግጥሙ ይገልጻል፡፡ አዝማሪ አብተው የዐፄ ቴዎድሮስ ፈረስ በሚግጠው ሣር ላይ ከምፅዋ ጨው መጥቶ እንዲነሰነስለት ይፈልጋል ማለቱም ንጉሡ ምፅዋን የመያዝ ፍላጎት አላቸው የሚል ፍንጭ ይሰጣል፡፡

የዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት ንቡር ጠቃሽ ዘይቤን በመጠቀም ከዐፄ ካሌብ ጋር ተመሳስሏል፡፡ በቀይ ባሕር የሚደረገው የንግድ እንቅስቃሴ ተፅዕኖ በማድረግ የአክሱም ሥልጣኔ በማሽቆልቆል ላይ በነበረበት ወቅት ዐፄ ካሌብ በ525 (እ.ኢ.አ) ቀይ ባሕርን ተሻግረው ደቡብ

---

[28]ዐፄ ቴዎድሮስ የእንግሊዝ ንግሥት "ቢክቶሪያ" መድፍ፣ ጠበንጃና ሌላም የጦር መሣሪያ እንዲሁም ሠራተኛ እንዲልኩላቸው ጠይቀው ባለመላካቸው ተቆጥተው ቆንስላቸውን ኬምሮንን ያስሩታል፡፡ የታሰሩትን ቆንስላቸውን እንዲፈቱላቸው ንግሥት "ቢክቶሪያ" በመልእክተኛቸው በስፒዲ በኩል ለዐፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ ይልካሉ፡፡ ደብዳቤው ሲደርሳቸው ዐፄ ቴዎድሮስ ይቆጣሉ፡፡ ንግሥቲቱ "የጠየኩትን አለመላካቸው ብትንቀኝ ነው" ብለው ይገምታሉ፡፡ "ይህ[ን] ሁሉ የምታደርገው ባሕር ተማምና ነው እንጅ ከሜዳ ወጥታ አትገጥመኝም" በማለት የተጠቀሰውንና ሌላም ፉከራ አሰሙ (Fusella, 1959፡ 68)፡፡

[29]ጋጠ የሚለው ቃል ፍች በመሬት ላይ የበቀለን ሣር በጥርስ በመንጨት ወይም በመቁረጥ በላ የሚል ነው፡፡ መሬት ላይ የበቀለን ሣር በጥርስ እየነጩ ከሚበሉት የቤት እንስሳት መካከል ፈረስና በቅሎ ይጠቀሳሉ፡፡ በቅሎ ወይም ፈረስ ታጭዶ በሚቀርብለት ሣር ላይ አሻቦ (ጥሬ ጨው) ጨምሮ መስጠት ሣሩን ደፍሮ እንዲበላ ያደርገዋል፤ ውኃም ያስጠጣዋል፤ ለጤናውም መልካም ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በሰፊ ቦታ ወይም በመሬት ወይም በሜዳ ላይ በበቀለ ሣር ላይ ጨው ነስንሶ ፈረስን ወይም በቅሎን ማብላት ብክነትን ስለሚያስከትል የተለመደ አይደለም፡፡

[30]ከዚኽም በላይ፣ የዐፄ ቴዎድሮስ ፈረስ ታስሮ ጥራጥሬ (ሽምብራ፣ ባቄላ፣ ገብስ ወይም ሌላ) ይቀርብለታል እንጂ ሜዳ ተለቅቆ ሣር እንዲግጥ እንደማይደረግ ልብ ይሏል፡፡

ሳውዲ ዐረቢያን (የዛሬዋ የመንን?) ወግተው አስገብረዋል (Ministry of Education, 2005)፡፡ (ለኢየሩሳሌም አይቀርብም ሐሣቡ)

ዐፄ ቴዎድሮስ ይገዙት ከነበረው ቦታ በቅርብ ርቀት የሚገኘውን ሥናርን[31] የመያዝ ምኞት እንደ ነበራቸው በገሪማ ታፈረ (፲፱፻፶፮፤ ፻፹፪ - ፻፹፫) የተጠቀሰው የሚከተለው የአዝማሪ አብተው ግጥም ያስረዳል፡፡

ፈረሱ አባ ታጠቅ ሚስቱ ተዋበች፤
አሽከሩ ገብርየ በቅሎው አማረች፤[32]
ፊቷን ወደ ስናር ዙራ ታያለች፡፡

በቃለ ግጥሙ አባ ታጠቅ ፈረሳቸው፣ አማረች በቅሏቸው፣ በማንኛውም እንቅስቃሴአቸው ከጎናቸው የማይለዩት የሚወዷት ሚስታቸው ተዋበችና የሚያምኑት የጦር ፊታውራሪያቸው ገብርየ ተጠርተዋል፡፡ ስናር የተባለው ቦታም ዛሬ ሱዳን ተብሎ በሚጠራው ሀገር ውስጥ ይገኛል፡፡ በቅሏቸው ፊቷን ወደ ስናር አዙራ ማየቷ መገለጹ፣ ጌታዋ ተቀምጠውባት አዘውትራ የምትኼድበትን የለመደችውን አቅጣጫ ይልቁንም በኀይል ሊቆጣጠሩትና የግዛታቸው አካል ሊያደርጉት የፈለጉትን ቦታ ይገልጻል፡፡ ይኸንን የዐፄ ቴዎድሮስ ፍላጎት የተረዳው አዝማሪ በተጠቀሰው ቃለ ግጥም አሞግሷቸዋል፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ተከታዮች ኢየሩሳሌምን ለመሳለም ሲኼዱ ከሚደርስባቸው ጥቃት ይታደጋሉ ተብሎ መታመኑን የሚከተለው በገሪማ (፲፱፻፶፮፤ ፻፹፪) የተጠቀሰው የአዝማሪ አብተው ግጥም ያስረዳል፡፡

ምእመናኑ ኹሉ እንኳን ደስ አላችሁ፣
ወደ ኢየሩሳሌም ደርሷል መኼጃችሁ፤
ታጠቅ ስለኾነ ማረፊያ ጥላችሁ፡፡
እንደዚህ ቀደሙ ማንም አይዛችሁ፡፡

ቃለ ግጥሙ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ምእመናን መልካም ዜና በማብሰር ይጀምራል፡፡ የምሥራቹም ምእመናኑ ወደ ኢየሩሳሌም በሚያደርጉት ጉዞ ከሚደርስባቸው ጥቃት ዐፄ ቴዎድሮስ ይታደጓቸዋል ተብሎ መታመኑ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ምእመናን ወደ ኢየሩሳሌም በሚያደርጉት ጉዞ፣ መንገድ ላይ

[31] ስናር የቦታ ስም ነው፡፡ ይኸም፣ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ተመልምለው ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት መሳፍንት አንዱ የሆነው ሄት ሤመተ ሀገሩ "ከተከዜ ወራጅ እስከ ፈለገ ግዮን መሻገሪያ ድረስ ነው፡፡ በስተቀኝም ከወምበራ እስከ እናሪያ ድረስ ባለው ቋራ፤ በለያ፣ ሰባት ቤት አገው፣፤ ጋዝጌ፤ አቸፈር፤ ወለጋ፤ ጓጉሣ፤ ዝብለት፤ ሶሪት፤ አካኮ የግዛቱ ወሰን እስከዚህ ሲሆን የመናገሻ ከተማዎቹ ከሰላ፤ በለው፣ ስናር ናቸው፡፡" (ገሪማ፣ ፲፱፻፶፮፤ ፳ - ፳፩) (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡ ከተዘረዘሩት ቦታዎችና ከተማዎች አንዳንዶቹ ዛሬ የት እንደሚገኙ አይታወቅም፡፡ በአኹኑ ጊዜ ስናር የሚገኘው በምዕራብ አርማጭሆ ውስጥ ነው፡፡ በዚኹ ስም የሚጠራ ቦታ ሱዳን ውስጥም አለ፡፡ የዐፄ ቴዎድሮስ ምኞትም በሱዳን የሚገኘውን ስናርን ነው፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ይኸንን ቦታ ለመያዝ ለምን እንደተመኙ ተመኙ ለመረዳት አልተቻለም፡፡

[32] ንጉሡ በቅሎን በሰላም ጊዜ ለመጓጓዣ፣ ፈረስን ለጦርነት ይጠቀሙ እንደ ነበር ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

ይያዙና ይንገላቱ ነበር፡፡ ኢየሩሳሌም ከደረሱ በኋላም ቦታውን በያዙት የእስልምና እምነት ተከታዮች ጥቃትና ጉስቁልና ይደርስባቸው ነበር፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያውያን ምእመናን ኢየሩሳሌምን ለመሳለም በሚያደርጉት ጉዞ ከሚደርስባቸው ጥቃት "የሚታደጉ ጀግና ናቸው" ተብሎ በመታመኑ አስሞግሷቸዋል፡፡ የሙገሳ ግጥሙ መነሻ ዐፄ ቴዎድሮስ በአንደበታቸው ያሰሙት በነበረው ፉከራ ምኞታቸውን ወይም ፍላጎታቸውን መግለጻቸው ነው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ቅዱስ ቦታ ተደርጋ የምትቆጠረውን ኢየሩሳሌምን ከእስልምና እምነት ተከታዮች ቁጥጥር ነፃ የማውጣት ምኞታቸውን በየዕለቱ ሲፈነድቁ "መይሳው ካሣ የኢትዮጵያ ባል የኢየሩሳሌም ዕጮኛ" በማለት ይገልጹ ነበር፡፡ (ገሪማ፣ ፲፱፻፶፯ ፤ ፻፹፯) "የኢትዮጵያ ባል ነኝ" ማለታቸውም ኢትዮጵያን ማስተዳደር፣ የሕዝቡን ሰላም ማስጠበቅ፣ ፍትሕና ርትዕ እንዲሰፍን ማድረግ፣ ኢትዮጵያን ከወጭ ወራሪ ጥቃት መጠበቅ፣ በአጠቃላይ ዘመኑ የሚጠይቀውን የሀገር መሪነት ኃላፊነት መወጣት ዋናው ተግባራቸው መኾኑን ይገልጻል፡፡ "የኢየሩሳሌም እጮኛ ነኝ" ማለታቸው ደግሞ፣ ወደውና ፈቅደው ኢሩሳሌምን ከቱርክ ነፃ ለማውጣት ማቀዳቸውንና "ተጨማሪ ኃላፊነት አለብኝ" ማለታቸውን ያስረዳል፡፡ ይኽንኑ ዕቅዳቸውንም ሲቆጡ "የሐበሻ ባል የኢየሩሳሌም ውሽማ" (Fusella, 1959፡ 68) በማለት ይፎክሩ እንደ ነበር በዜና መዋዕላቸው ተገልጿል፡፡ "የኢየሩሳሌም ውሽማ ነኝ" ማለታቸውም ኢየሩሳሌምን ከቱርክ ነፃ በማውጣት የክርስትና እምነት ተከታዮች በነፃነት ጸሎት የሚያደርሱባት ቅድስት ቦታ እንድትኾን የማድረግ ጠንካራ ፍላጎት እንደ ነበራቸው ይገልጻል፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ሲቆጡ የሚያሰሙት ፉከራም በአዝማሪ አስሞግሷቸዋል፡፡

የዐፄ ቴዎድሮስ ዕቅድ ወይም ፍላጎት ኢየሩሳሌምን በያዙት ቱርኮች ዘንድ እንደ ታወቀ ፍርሐት እንደ አደረባቸው የሚከተለው የአዝማሪ አብተው የሙገሳ ግጥም ይገልጻል፡፡

> ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም፤
> ዐርብ ዐርብ[33] ይሸበራል ኢየሩሳሌም፡፡[34]

በየሳምንቱ ዓርብ ዓርብ በኢየሩሳሌም ከተማ የእስልምና እምነት ተከታዮች ለጸሎት ሲሰበሰቡ የሚታውን እንቅስቃሴ ነው፡፡ ዐርብ ዐርብ ለጸሎት የሚሰበሰቡት ምእመናን ብዙ በመኾናቸው ምክንያት እንቅስቃሴአቸው ትርምስና ሽብር የተሞላበት እንደሚመስል በግጥሙ ሰም ተገልጿል፡፡ አዝማሪ አብተው በወርቁ ዐፄ ቴዎድሮስን ያሞገሰው ኢየሩሳሌምን ለማስለቀቅ ያላቸው ፍላጎት በተቆጣጠሯት ዐረቦች [እስላሞች] ዘንድ በመታወቁ ፍርሃትና ሽብር ነግሧል የሚል ነው፡፡ "ዐፄ ቴዎድሮስ ጥቃት ይሰነዝሩብናል" የሚል ሥጋት በቱርኮች ዘንድ መፍጠር

---

[33] "ዐርብ ዐርብ በያመቱ የስቅለት በዓል በሚከበርበት ጊዜ ለማለት ይሆን?" በማለት ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ (1981፤ 270) በጥያቄ መልስ ያሉትን አቅርበዋል፡፡ ይኹን እንጂ፣ ግጥሙ በጊዜው በቱርክ ተይዛ የነበረችውን ኢየሩሳሌም ከተማን ስለሚጠራ ከስቅለት ጋር የተገናኘ ፍቺ የለውም፡፡

[34] ቃለ ግጥሙ በማኅተመ ሥላሴ ()፣ በተክለ ጻድቅ (1981፤ 269) እና በገሪማ (፲፱፻፶፯ ፤ ፻፹፯) ተጠቅሷል፡፡ ማኅተመ ሥላሴና ተክለ ጻድቅ ለዐፄ ቴዎድሮስ መገጠሙን እንጂ በማን እንደ ተገጠመ አልገለጹም፡፡ በአዝማሪ አብተው መዜሙን የገለጹት ገሪማ ናቸው፡፡

መቻላቸው በአዝማሪ አብተው አስሞግሷቸዋል፡፡ በሙገሳ ግጥሙ የዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት ተጋንኖ፣ ኢየሩሳሌምን ይገዙ የነበሩት ቱርኮች ማንነት ደግሞ ኰስሶ ተገልጿል፡፡

ኢየሩሳሌምን የሚቆጣጠሩት ቱርኮች ወታደራዊ አቅማቸው ከዐፄ ቴዎድሮስ የጎለበተ ስለ ነበር ባሕር ተሻግረው ምፅዋን ይገዙ ነበር፡፡ ተክለጻድቅ (1981፤ 269) እንዳሉት "በመርከብና በምድር ጦርም ለደረጁት ለመስኮብና ለፈረንሳይ እንኳን ያልተበገረውን የቱርክን ኃይል ተዋግቼ ኢሩሳሌምን ነፃ አወጣለሁ የሚለው ምኞታቸው" የተጋነነ ነበር፡፡ "መርከብ ሥራ ሳይጀመር፣ ፍረሰኛ ጦራቸውን ይዘው ባሕር ተሻግረው በመዝመት ቱርክን ለመውጋት" የሚያስችል ወታደራዊ አቅም አልነበራቸውም፡፡ ቱርኮች በነበራቸው ወታደራዊ ጉልበት ሌሎች ሀገሮችንም ወርረው ይዘው የነበረ ሲኾን፣ ባሕር ተሻግረው ምፅዋን ይገዙ ነበር፡፡ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያም ከደጅ አዝማች ክንፉና ከደጅ አዝማች ብሩ ጋር ባደረጓቸው ውጊያዎች ወታደራዊ አቅማቸው ጠንካራ እንደ ነበር ይታወቃል፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስም በወጣትነት ዘመናቸው ከቱርክ ጦር ጋር ተዋግተው ተሸንፈዋል፡፡[35] ቱርኮች ዘራቸው ዐረብም አይደሉም፡፡ አዝማሪ አብተው ኢየሩሳሌምን የሚገዙትን ቱርኮች ዐረብ ብሎ መጥራቱ የእስልምና እምነት ተከታዮች በመኾናቸውና እምነቱን ከዐረቦች ጋር በማዛመዱ ምክንያት በተፈጠረው ስህተት ነው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ በጀግንነታቸው ከሞቱ በኋላም በአዝማሪ ይሞገሱ ነበር፡፡ ለዚኽም፣ በማኅተመ ሥላሴ (፲፱፻፵፩፤ ፷፻፸፷) የተመዘገበው የሚከተለው የሐሰን አማኑ[36] ግጥም አስረጅ ነው፡፡

የቋራው ካሣ ልበልኽ አንዴ፣
የለኽም ዘመድ ያለ ጎራዴ፡፡

አንሡ ካላችሁ እናንሣ ወንድ፣
የቋራው ካሣ አባ ሞገድ፡፡

መቼ ሞተና መቼ ተረሳ፣
መቅደላ ያለው የቋራው ካሣ፡፡

---

[35]ልጅ ካሣ ወይዘሮ ተዋበችን ባገቡ በኹለተኛው ዓመት የኢትዮጵያን ወሰን ለማስከበር በአባቶቻቸው የተለመደውንና እንደ ትልቅ ተግባር የሚቆጠረውን ለመፈጸም ወደ ምዕራብ ዘመቱ፡፡ ገዳሪፍ ላይ "በጦር ትምህርት ከሠለጠነውና በጠራ የጦር መሣሪያ ከደረጀው ከቱርክ መንግሥት ጦር ሠራዊት ጋር ጦርነት ገጥመው በጀግንነት ተዋጉ፡፡ " የሥልጠናና የጦር መሣሪያ ብልጫ የነበረው የቱርክ ጦር የልጅ ካሣን ጦር ድል አድርጎ መለሰው፡፡ በጦርነቱም ልጅ ካሣ ቆሰሉ (ገሪማ፣ ፲፱፻፺፯ ፤ ፵፪)፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ቱርክን ለመውጋት ድጋሜ ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዘምተው ጦራቸው ተጎድቶ የድንኳናቸው ተራዳ በመድፍ ተመትቶ ሸሽተው እያዘኑ ተመለሱ (ገሪማ፣ ፲፱፻፺፯ ፶፩)፡፡

[36]ሐሰን አማኑ መጀመሪያ የዐፄ ዮሐንስ ፬ኛ፣ እሳቸው ከሞቱ በኋላ ደግሞ፣ የራስ (በኋላ ንጉሥ ሚካኤል) አጫዋች ነበሩ፡፡ ሐሰን አማኑ ለዐፄ ቴዎድሮስ፣ ለዐፄ ዮሐንስ፣ ለዐፄ ምኒልክ፣ ለንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ፣ ለልዑል ራስ መኮንን፣ ለራስ ጎበና፣ ለራስ ተሰማ፣ ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፣ ለፊታውራሪ ገበየሁ፣ ለደጃዝማች ባልቻ፣ እንዲሁም በስም ላልተገለጹ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን የደረደሯቸው ግጥሞች በማኅተመ ሥላሴ (፲፱፻፵፩፤ ፷፻፸፷ - ፷፻፹፯) ታትመዋል፡፡

ይኽ ዐፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ የተገጠመላቸው የሙገሳ ግጥም ስለ መኾኑ በ፰ኛው ስንኝ የተገለጸው ሐሣብ ያስረዳል፡፡ ቋራና መቅደላ የተባሉት ቦታዎች ከዐፄ ቴዎድሮስ የሕይወት ታሪክ ጋር ባላቸው የጠበቀ ቁርኝት የቃለ ግጥሙ መልእክት ማስተላለፊያ ኾነዋል፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ የተወለዱት "ከጎንደር ከተማ ደቡባዊ ምሥራቅ ዐሥራ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው ዳዋ ከተባለችው ቅርብ ገጠር ይወለዱ" (ገሪማ፣ ፲፱፻፺፪፤ ፲፱) እንጂ፣ የሚጠሩት ግን በአባታቸው በልጅ ኃይሉ የትውልድ ቦታ በቋራ ነው፡፡ ከዚኽም በተጨማሪ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ በእቴጌ መነንና በራስ ዓሊ ላይ አምጸው የሸፈቱት በቋራ ነው፡፡ ብዙ የጦርነት ውሎዎችን ያሸነፉት በቋራ አካባቢ ነው፡፡ በቋራ አካባቢ ያገኙዋቸው ድሎች ወደ ሥልጣን ባደረጉት ጉዞ ወሳኝ ምዕራፎች ናቸው፡፡ ቋራ የሥልጣን ዘመናቸው የመጀመሪያ ምዕራፍ ሲኾን መቅደላ ተራራ ደግሞ፣ ሕይወታቸው ያለፈበትና አፅማቸው ያረፈበት፣ የሥልጣን ዘመናቸው የተደመደመበት ነው፡፡ ኹለቱ ቦታዎች ሲጠሩ የዐፄ ቴዎድሮስን የሕይወት ታሪክ በአእምሯችን ለማሰስ እንገፋፋለን፡፡ ሕይወታቸው ከቋራና ከመቅደላ ተራራ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው በመኾኑ ቃለ ግጥሙ የሕይወት ታሪካቸውን በአጭሩ ይገልጻል ማለት ይቻላል፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሥልጣን የመጡት በጀግንነታቸውና በአሸናፊነታቸው መኾኑንና በሥልጣን በቆዩባቸው ጊዜያት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በታሪክ መታወስ እንዳለባቸውና መረሳት እንደሌለባቸው፣ "መቼ ሞተና መቼ ተረሳ" የሚለው ስንኝ ይገልጻል፡፡ አዝማሪው ዐፄ ቴዎድሮስ ከመሞታቸው ጀግንነታቸውና አሸናፊነታቸው ከምኔው ተረሳ? በማለት መጠየቁ ጀግንነታቸው ሊረሳ እንደማይገባው ሲያሳስብ ነው፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ በሽፍትነትም ኾነ በሥልጣን ዘመናቸው ተቀናቃኞቻቸውን ካጠቁባቸው የጦር መሣሪያዎች አንዱ ጎራዴ ነው፡፡ ጎራዴአቸውን ዘመድ አድርገው "አሻፈረኝ" ብለው የሸፈቱት ዐፄ ቴዎድሮስ ተቀናቃኞቻቸውን ድል አድርገው የንጉሥነት ሥልጣን ይዘዋል፡፡ በአሸናፊነታቸውም ጎበዝ፣ ጀግና ተብለዋል፡፡ ሥልጣን ይዘው ብዙ የትግልና የድካም ሕይወት ካሳለፉ በኋላ መሞታቸው መገለጹ የሕይወት ታሪካቸው መዘከሩን ያስረዳል፡፡

ደጅ አዝማች ካሣ (ዐፄ ቴዎድሮስ) ከዚኽ በላይ በተጠቀሱት ቃለ ግጥሞች በአዝማሪዎች የተሞገሱት በጦር ሜዳ ውሏቸው በፈጸሟቸው የጀግንነት፣ የድል አድራጊነትና የአሸናፊነት ተግባሮቻቸው ነው፡፡ አዝማሪዎች ደጅ አዝማች ካሣን (ዐፄ ቴዎድሮስን) ያሞገሱት ሊያጠቋቸው ጦር ያዘመቱባቸውንና በሥልጣን የተቀናቀኗቸውን ድል ሲያደርጉ በማየታቸው ወይም በመስማታቸው እንዲሁም፣ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ላይ ወደ ፊት ሊያደርጉት የሚፈልጉትንና የሚመኙትን በአንደበታቸው የገለጹትን፣ በፉከራ ያሰሙትን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ጦርነት ለማካኼድ እንቅስቃሴ በሚደረግበት ጊዜ የዐፄ ቴዎድሮስ ተቀናቃኞችም ኾኑ የዐፄ ቴዎድሮስ ወገኖች የቅስቀሳ ግጥሞችን ይደረድራሉ፡፡ አዝማሪዎች ግጥሞችን በመደርደር የሚደግፉትን ወገን እንዴት ይቀስቅሱ፣ የሚቃወሙትን ደግሞ እዴት ያኮስሱ ይሰድቡ እንደ ነበር ቀጥሎ በሚቀርበው ንዑስ ርእስ እንመለከታለን፡፡

## ፰. ማጠቃለያ

አዝማሪዎች ደጅ አዝማች ካሣን/ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ያሞገሱት በወታደራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴአቸው ባገኙዋቸው ስኬቶች ነው:: በሙገሳ ግጥሞቻቸው ጀግንነታቸውንና ዘራቸውን አሞግሰዋል:: መሳፍንቱ ያዘመቱባቸውን ጦር መክተው ድል በማድረጋቸው፣ ተቀናቃኞቻቸውን አሸንፈው በማስገበራቸው፣ የኢትዮጵያውያንን ጥቅም ለማስከበር በቅርበትና በርቀት ያሉ ቦታዎችን የሚገዙ ሰዎችን ለመውጋት ማሰባቸው በአዝማሪ አስሞግሷቸዋል:: አዝማሪዎች የዐፄ ቴዎድሮስን ድሎች በማሞገስ በተለያዩ አጋጣሚዎች ለሕዝብ ያሰሙ ነበር:: በጽሑፍ የተመዘገቡትና ለዚኽ ጥናት በመረጃነት ያገለገሉት በአዝማሪ የተደረደሩ የሙገሳ ግጥሞች በጊዜው አዝማሪዎቹ ግጥሙን ባቀረቡበት አጋጣሚ ላይ በመገኘት የተመዘገቡ አይደሉም:: የዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉ ሰዎች በአዝማሪ መዜማቸውን በመግለጻቸው በመረጃነት የተወሰዱ ናቸው::

ዐፄ ቴዎድሮስ የተሞገሱባቸው ግጥሞች ጀግንነታቸውን መሠረት ያደረጉ ናቸው:: የሙገሳ ግጥሞቹም በሦስት የስኬታቸው ምዕራፎች ላይ ያተኩራሉ:: የመጀመሪያው፣ ደጅ አዝማች ካሣ ከተባሉ በኋላ በእቴጌ መነን "ተገቢው ክብር አልተሰጠኝም" በማለት አኩርፈው ከቤተ መንግሥቱ መራቃቸው፣ ወደ ቋራም ወርደው መሸፈታቸው ነው:: ማመጻቸው የጀግንነት ተግባር እንደፈጸሙ ተቆጥሮ አስሞግሷቸዋል:: በማመጻቸው የተከፉት እቴጌ መነን ጦር አዘመቱባቸው:: ይሁን እንጂ፣ ደጅ አዝማች ካሣ ያልተገመተ ድል አገኙ:: ያዘመቱት ጦር በደጅ አዝማች በመሸነፉ የተበሳጩት እቴጌ መነን ጦር መርተው ዘመቱባቸው:: የድል በር የተከፈተላቸው ደጅ አዝማች ካሣ፣ በእቴጌ መነን የተመራውን ጦርም ድል አድርገው እሳቸውንም ማረኩ::

በእናታቸው መሸነፍና መማረክ የተበሳጩት ልጃቸው ራስ ዓሊ፣ በጊዜው በጀግንነታቸውና በወታደራዊ አቅማቸው በግንባር ቀደምነት የሚጠሩትን የዳሞቱን ጎሹን አዘመቱባቸው:: ድሉ የደጅ አዝማች ካሣ ከሞኾኑም በላይ ደጅ አዝማች ጎሹ ተገደሉ፤ ጉልበታም የነበሩትን የደጅ አዝማች ጎሹን ልጅ ብሩ ጎሹንም ማረኩ:: አይሻል ላይ አማታቸውን ራስ ዓሊን ድል አድርገው አባረሩ:: በጎጃም ላይ የአባትና ልጁ ባላንጣ የነበረውን ተድላ ጓሉን ሾሙ:: ደጅ አዝማች ካሣ ወደ ሰሜን ዘምተው ደጅ አዝማች ውቤን ድል አድርገው ነገሡ:: ደጅ አዝማች ካሣ በጉር ዐምባና በአይሻል ከፍተኛ ድሎችን አገኙ:: አመጽ ከጀመሩበት ከቋራ ተነስተው፣ በጎጃምና በሰሜን ኀይለኛነታቸውንና አሸናፊነታቸውን በማሳየታቸው በአዝማሪዎች ተሞገሱ::

ዐፄ ቴዎድሮስ የተሞገሱባቸው በሕይወታቸው ኹለተኛ ምዕራፍ በኾነው የንግሥና ዘመናቸው ነው:: ደጅ አዝማች ውቤን አሸንፈው ከነገሡ በኋላ ፊታቸውን በወሎና በሸዋ በነበሩ መሳፍንት ላይ አደረጉ:: ወሎን በኀይል አስገበሩ:: ለመከከላል የሞከሩትን የንጉሥ ኃይለ መለኮት ደጋፊዎች አሸንፈው ሸዋን እንዲገብር አደረጉ:: እሳቸው ወሎንና ሸዋን ለማስገበር በዘመቱበት ጊዜ ደጅ አዝማች ውቤን ወግተው የግዛታቸው አካል ባደረጉት ቦታ ጋረድ፣ ደጅ አዝማች ንጉሤና

ፊታውራሪ ተሰማ ሸፍተው ሕዝቡን አሳመጹባቸው፡፡ እሳቸውም ከሸዋ ወደ ሰሜንና ወደ ትግራይ በመዝመት ያመጹትን ወግተው ድል አደረጓቸው፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ፊታቸውን ወደ አንድ አቅጣጫ አዙረው ተቀናቃኞቻቸውን ለመውጋት ሲዘምቱ ባቀኑትና ባስገበሩት ክፍለ ግዛት ለአመጽ የሚነሣሱትን ኹሉ እየተመላለሱ ወግተው ድል በማድረጋቸው ተሞግሰዋል፡፡ የመሳፍንቱን ግዛቶች ጠቅልለው ኢትዮጵያ የምትባል አገርን በመምራታቸው አዝማሪዎች አሞግሰዋቸዋል፡፡

የዐፄ ቴዎድሮስ ፍላጎት ያሸነፏቸውን የደጅ አዝማች ጎሹን፣ የራስ ዓሊን፣ የደጅ አዝማች ውቤን፣ የወርቂትንና የጎይለ መለኮትን ግዛቶች ጠቅልሎ በመያዝ የተገደበ አልነበረም፡፡ በቱርክ ግዛት ሥር የነበረውን ምፅዋን፣ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ይገኝ የነበረውን ስናር፣ የክርስትና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ለመንፈሳዊ ተግባር በየጊዜውን የሚጎበኟትንና የሚሳለሟትን ኢየሩሳሌምን ከቱርክ ነፃ ለማውጣት ፍላጎት እንዳላቸው የሚያውቁ አዝማሪዎች አሞግሰዋቸዋል፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ አንድ አካባቢ ዘምተው ከመውጋታቸው በፊት ሕዝቡ በሰላም አርሶና ነግዶ እንዲበላ ዐዋጅ ያስነግራሉ፡፡ እንደዚሁም፣ የአመጸውን ወግተው ድል ካደረጉና ተባባሪዎቹን ከቀጡ በኋላ ሕዝቡን የሚያረጋጋ ዐዋጅ ያውጃሉ፡፡ ለምሳሌ፣ የጋረድን ሠራዊት ደብድበው ከጨረሱ በኋላ ከደባርቅ ወደ ጎንደር ከመነሣታቸው አንድ ቀን ቀደም ብሎ፡- “አራሽ እረስ ነጋዴም ነግድ፡፡ ሽፍታ ወምበዴ ተው ግባ ይሻልሀል ተዚህ ቀደም የበደልኽ ቋንጃ የቆረጥህ ነፍስ የገደልህ ምሬሀ አለሁ በዱር በገደል ያለህ ግባ አልገባም ብለህ አዋጀን ያለፍህ ግን ለአካልትህ እዘንለት” የሚል ዐዋጅ አስነገሩ (ገጽ 91)፡፡ እንዲኽ ዓይነት ዐዋጆች በደጋፊዎቻቸው እንዲሞገሱ፣ በጠላቶቻቸው እንዲፈሩ አድርጓቸዋል፡፡

### መረጃ ጽሑፎች


ሊትማን፣ ኢኖ፡፡ ፲፱፻፪፡፡ *የቴዎድሮስ ታሪክ* ፡፡ ፕሪንስቶን፤ ሻርልስ ስክሪብኔር ልጆች፡፡

ሐረገወይን ሸዋረጋ፡፡ 2004፡፡ “በባህር ዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፡፡

መንገሻ አማረ፡፡ 1992፡፡ “የወገል ጤና አዝማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ቃልግጥሞች፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፡፡

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፡፡ ፲፱፻፵፭፡፡ *አማርኛ ቅኔ ከነ መፍቻው ተሻሽሎና ታክሎበት የተሰናዳ፡፡* አዲስ አበባ፤ እሌኒ ማ. ኃ. የ. ግ. ማ.፡፡

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፡፡ ፲፱፻፵፭፡፡ *ዝክረ ነገር*፡፡ አዲስ አበባ፤ ሴንተራል ማተሚያ ቤት፡፡

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፡፡ *ዳግማዊ ምኒልክ የአጼሱ ሥልጣኔ መሥራች*፡፡ (የታተመበት ቦታ፣

ማተሚያ ቤቱና ዓመተ ምሕረቱ አልተገለጸም) ፡፡

ቤተልሔም አለምሰገድ፡፡ 2005፡፡ "የቃል ግጥም ክዋኔ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ አዝማሪ ቤቶች፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፡፡

ባሕሩ ዘውዴ፡፡ 1999፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከ1847 እስከ 1983*፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፡፡ ፲፱፻፶፩፡፡ ከሣቴ *ብርሃን ተሰማ፡፡ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት*። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ፡፡ 2008፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፡፡* (ሐተታ በሥርግው ገላው) አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡ 1981፡፡ *ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት* ፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት (ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት)፡፡

ኑርሁሴን ሙሐመድ፡፡ 1986፡፡ "በፎገራ አካባቢ የሚሰሙ የአዝማሪ ግጥሞች ይዘት ትንተና፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፍ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፡፡

አልማዝ አበበ፡፡ 1974፡፡ "አዝማሪና ግጥሞቹ በየጁ አውራጃ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፡፡

አስቴር ሙሉ፡፡ 2007፡፡ "ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኰሚዩኒኬሽን ኰሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል (ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)፡፡

አበበ ማለደ፡፡ 2002.፡፡ "በጎንደር ዙሪያ ወረዳ በብርቧክስ ቀበሌ የአዝማሪነት ሙያና የዘፈን ግጥሞች፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሕፍ ትምህርት ክፍል፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሕፍ፡፡

አንለይ ሙሉ፡፡ 1995፡፡ "የአዝማሪ ታደለ የሕይወት ታሪክና ቃላዊ ግጥሞቹ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ - ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፡፡

አዳነች አበራ፡፡ 2001፡፡ "የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ ታሪክ መጻሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኰሚዩኒኬሽን ኰሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል (ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ ፳፻፡፡ *የመጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*፡፡ አዲስ አበባ (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡፡ ፲፱፻፺፫፡፡ *ኣማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ይድነቃቸው ተሰማ፡፡ ፲፱፻፸፫፡፡ *ሰምና ወርቁ ተሰማ እሸቴ*፡፡ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ደርጅት፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ ፲፱፻፷፪፡፡ *አዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ገሪማ ታፈረ፡፡ ፲፱፻፺፪፡፡ *አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ*፡፡ (ኹለተኛ እትም) አዲስ አበባ፤ Finfinne

Printing and Publishing S. C.

ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ (ጸሓፊ ትእዛዝ) ። ፲፱፻፶፱፡፡ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ* ፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ገነት አየለ አንበሴ (ተርጓሚ)፡፡ 2009፡፡ *በኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች ቆይታዬ*፡፡ (የታተመበት ቦታ አልተገለጸም)፤ Graphic Pronters.

Abraham Girmay Hagos. 2015. "Socioliguistics Aspects of the Asho (Azmari) Argot Speakers in Tigray," in *Asian Journal of Multidisplinary studies*. Vol. 3, Issue 2, PP. 100- 109.

Ashenafi Kebede. 1975. "The "Azmari", Poet-Musician of Ethiopia." In፡ *the Musical Quarterly*. Vol. 61, No. 1, PP. 47-57.

Ashenafi, Kebede. 1971. "The Music of Ethiopia: its Development and Cultural Settings." Wesleyan University: PhD Dissertation.

Bolay, Anne. 2002. "The Azmari: Voice of Ethiopian Memory." Ethiopian Studies at the End of the Second Millennium - Proceedings of the 14th International Conference of IES, Addis Ababa University, Institute of Ethiopian Studies, Vol. I, Pp.75-83.

Bruce, James. 1730-1794. *Travels to discover the Source of the Nile*. In *the years 1768 -1773, Book VI.*

Chadwick, H. Munro and Chadwick, N. Kershaw. 1940. *The Growth of Literature*. Cambridge: Cambridge University Press.

Fusella, Luigi. 1959. "La Cronaca dell' Imperatore Teodoro II di Etiopia in un manoscritto amarico," *Annali dell' Instituto Universitario Orientali di Napoli*. Nuóva serie, volume VII, Pp. 63- 89.

Fusella, Luigi. 1958. "La Cronaca dell' Imperatore Teodoro II di Etiopia in un manoscritto amarico," *Annali dell' Instituto Universitario Orientali di Napoli*. Nuóva serie, volume VII, Pp. 69- 94.

Girma Getahun (translator). 2014. *The Goǧǧam Chronicle by Aläqä Täklä Iyäsus WaqGera*. Oxford University Press: The British Academy.

Kawase, Itsushi. 2010. "Intercultural Dialogue on the Visualization of Local Knowledge: Films on Hereditary Singers in Ethiopia." **In**: *African study Monographs*, supp l.41:101-109.

___________ .2008. "The Transformation of Musical Activities and Self-imposed Group Markers of *Azmari* in Ethiopia." In *Cultures Sonoresd'Afrique IV*. publie'sous ladirection de Junzo KAWADA,

*Institut de Rechrches sur les Cultures Populaires du Japan.* University' Kanagawa: Yokohama, (Japan).

___________ .2005. "Musical Performance and Self-Designation of Ethiopian Minstrels: *Azmari*". Graduate School of Asian and African Area Studies, Kyoto University, Sakyo-Ku, Kyoto, 606-8501, Japan.

Kefyalew Azeze. 1998. "Minstrels in Addis Ababa: a Study in the Social Life of Gonderian Inzatas". Addis Ababa University: Department of Social Anthropology MA Thesis.

Kimberlin, Cynthia T. 1983. "The Music of Ethiopia." In *Musics of many cultures: an introduction.* USA, Paperback Printing.

Kimberlin, Cynthia Mei-Ling. 1976. "Masinqo and the Nature of *Qaññat*." A Dissertation Submitted in Partial Satisfaction of the Requirements for the Degree Doctor of Philosophy in Music, University of California, Los Angels.

Leslau, Wolf and Ken L. Thomas. 2001. *Amharic Cultural Reader*. Harrassowitz. Verlago. Wiesbaden.

Leslau, Wolf. 1952. "An Ethiopian Minstrel's Argot." In *Journal of the American Oriental Society*. Vol. 72, No, 3, PP. 102- 109.

Mesganaw Andualem. 2010. "Change and Continuity in the Lives of Birbuax Azmaris." Addis Ababa University: Department of Social Anthropology MA Thesis.

Ministry of Education. 2005. History of Students' Text Book Grade 9. Addis Ababa: Mega Publishing Enterprise.

Mittwoch, Mitgeteilt von Eugen Problem aus amharischem Volksmunde Pp. 33-35

Pankhurst, Richard and Asfaw, Girma-Selassie. 1985. "AN AMHARIC WAR- SONG OF EMPEROR TEWODROS'S SOLDIERS." In *Journal of Ethiopian Studies*. Vol. 18, Pp. 51-62.

Pankurst, Sylvia. 1959. Ethiopia: *A Cultural History*. London: Lalibela House Woodford Green Essex.

Teclehaimanot Gebere Selase. 1986. "A brief Survey Study of the Azmareis in Addis Abeba." *Proceedings of the international Symposium on*

*the Centerary of Addis Ababa*. Addis Ababa, Institute of Ethiopian Studies, November 24 -25, Pp.161 -172.

Tigist Girma. 2010. "Major Themes and Performance Styles of *Azmari* Lyrics in Gondar." Addis Ababa University: Institute of Language Studies Department of Foreign Languages and Literature (MA Thesis Submitted to the Department of Foreign Languages and Literature in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Masters of Arts in Literature).

Timkehet, Teffera. 2009. "One-Stringed Fiddle *Masinqo*: Its Function and Role in the Contemporary Ethiopian Music and its Future".Accessed on 27 February 2018, at: http://addisconnexion. com/index.php/ Music/The Masinqo.html. 01/07/2013 11:00.

Vidailhet, Mondon C. 1904. *Chronique Theodoros II Roi des Rois d'ethipie (1853- 1863) d'apres un Manuscript Original Text Abyssin (Amharique)*. (No place of publication and printing press)